አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

# የነገደ ወይጦ ማህበረሰብ ቃላዊ ዝርው ተረኮችና ባህላዊ ስርዓቶች ጥናት

በ
ከሁሉም በላይ

መስከረም 2004 ዓ.ም
አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

# የነገደ ወይጦ ማህበረሰብ ቃላዊ ዝርው ተረኮችና ባህላዊ ስርዓቶች ጥናት

በ

ከሁሉም በላይ

በሰብአዊ ሳይንስ ፋኩልቲ የኢትዮጵያ ስነጽሁፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት የአርት ማስተርስ ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉት ነጥቦች ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ

መስከረም 2004 ዓ.ም

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

# የነገደ ወይጦ ማህበረሰብ ቃላዊ ዝርው ተረኮችና ባህላዊ ስርዓቶች ጥናት

በ

ከሁሉም በላይ

በሰብአዊ ሳይንስ ፋኩልቲ የኢትዮጵያ ስነጽሁፍ እና ፎክሎር ክፍል ትምህርት
የአርት ማስተርስ ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉት ነጥቦች ከፊሉን ለማሟላት
የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ

አማካሪ

አብርሃም አለሙ

መስከረም 2004 ዓ.ም

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

# የነገደ ወይጦ ማህበረሰብ ቃላዊ ዝርው ተረኮችና ባህላዊ ስርዓቶች ጥናት

በ

ከሁሉም በላይ

በሰብአዊ ሳይንስ ፋኩልቲ የኢትዮጵያ ስነጽሁፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት
የአርት ማስተርስ ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉት ነጥቦች ከፊሉን ለማሟላት
የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ

የፈተና ቦርድ አባላት

አማካሪ ፊርማ

ፈታኝ ፊርማ

# ማውጫ

ርዕስ ገፅ

ምስጋና ....................................................i
የኢትዮጵያና የአማራ ክልል ካርታ ....................................................iii
የጣና ሀይቅና የባህር ዳር ካርታ ....................................................iv
አጠቃሎ ....................................................v
ምዕራፍ አንድ ....................................................1
መግቢያ ....................................................1
1.1. የጥናቱ ዳራ ....................................................2
1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ....................................................4
1.3. የጥናቱ ዓላማ ....................................................4
1.4. የምርምር ጥያቄዎች ....................................................5
1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ ....................................................5
1.6. የጥናቱ ወሰን ....................................................5
1.7. የመረጃ አሰባሰብ እና የአጠናን ዘዴዎች ....................................................6
1.7.1. የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ ....................................................6
1.7.1.1. ቃለመጠይቅ ....................................................7
1.7.1.2. ምልከታ ....................................................7
1.7.1.3. ተተኳሪ የቡድን ውይይት ....................................................8
1.7.2. የመረጃ አቀባዮች የናሙና አመራረጥ ዘዴ ....................................................8
1.7.3. የጥናቱ አተናተን ዘዴ ....................................................9
1.8. ለጥናቱ የተደረገ ቅድመ ዝግጅትና የመስክ ክንውን ....................................................10
1.8.1. ቅድመ ዝግጅት ....................................................10
1.8.2. የመስክ ክንውን ....................................................10
1.9. ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ የመፍትሔ አቅጣጫዎች ....................................................16
ምዕራፍ ሁለት ....................................................19
የነገደ ወይጦ ማህበረሰብ ማህበረ-ባህላዊ ዳራ ....................................................19
2.1. የነገደ ወይጦ ጥንተ አመጣጥ ....................................................19
2.2. አስተዳደራዊ ሁኔታን በተመለከተ ....................................................21
2.3. ኢኮኖሚያዊ ሁኔታን በተመለከተ ....................................................22
2.4. ማህበራዊ ግንኙነትን በተመለከተ ....................................................23
2.5. ባህላዊ ግንኙነትን በተመለከተ ....................................................25
ምዕራፍ ሦስት ....................................................26
ክለሳ ድርሳን ....................................................26
3.1. የንድፈ ሀሳቦች ቅኝት ....................................................26

3.1.1. ቃላዊ ዝርው ተረክ ....................................................26
3.1.2. ባህላዊ ሥርዓቶች ....................................................28
3.1.3. ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ (Functional Approach) ..........................31
3.2. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ....................................................33
3.2.1. በነገደ ወይጦ ማህበረሰብ ላይ በመመስረት የተሰሩ ..........................34
3.2.2. በየማህበረሰቡ ማህበራዊና ባህላዊ ፋይዳ ላይ የተጠኑ ......................35
3.2.3. ቃላዊ ዝርው ተረኮችን በአውዳዊ አገባባቸውና በዘውግ በመመደብ ያጠኑ 37
ምዕራፍ አራት ....................................................41
ከነገደ ወይጦ ማህበረሰብ ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ቃላዊ ዝርው ተረኮች ትንተና .....41
4.1. ከነገደ ወይጦ ማህበረሰብ ስያሜ ጋር የተያያዙ ተረኮች ..........................41
4.1.1. ከአመጋገብ ስርዓት አንፃር የተሰጠ ስያሜ ..........................41
4.1.2. ከነገዱ ስም በመነሳት የተሰጠ ስያሜ ..........................44
4.1.3. ከስራ ባህላቸው አንፃር የተሰጠ ስያሜ ..........................45
4.1.4. በአካባቢው ካለ የእህል ፍሬ ጋር በተያያዘ የተሰጠ ስያሜ ............45
4.2. ከነገደ ወይጦ ማህበረሰብ አመጣጥ ጋር የተያያዙ ተረኮች ..........................46
4.2.1. ነገደ ወይጦና ጡሊ (ቅምጫና ቅል) ..........................47
4.2.2. ነገደ ወይጦና ነብዩ ሙሴ (ሙሳ) ..........................48
4.2.3. ነገደ ወይጦና ግብፅ ..........................49
4.2.4. ነገደ ወይጦ፣ ንግስተ ሳባና አፄ ፋሲል ..........................50
4.2.5. ነገደ ወይጦና የአካባቢው የቦታ ስያሜዎች ..........................51
4.3. ነገደ ወይጦና ሼህ ጅብሪል ..........................52
4.4. ነገደ ወይጦና አቢናዝ ..........................53
4.5. ነገደ ወይጦና ባህር ዳር ..........................56
4.6. ነገደ ወይጦና የታንኳ እና የወፍጮ ስራ ..........................57
4.7. ነገደ ወይጦና እርግማን ..........................58
4.8. ነገደ ወይጦና ውሃ ..........................60
ምዕራፍ አምስት ..........................62
የነገደ ወይጦ ማህበረሰብ የሚያከብሯቸው ባህላዊ ስርዓቶች ገለፃ ..........................62
5.1. አቢናዝ ..........................62
5.2. የግርዛት ስርዓት ..........................67
5.3. የጋብቻ ስርዓት ..........................71
ምዕራፍ ስድስት ..........................78
ማጠቃለያ ..........................78
ዋቢ ጽሁፎች ..........................80
አባሪዎች ..........................i
አባሪ አንድ፣ የተረኮች ስብስብ ..........................i
አባሪ ሁለት፣ የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር ..........................xix
አባሪ ሦስት፣ የፎቶግራፎች ዝርዝር ..........................xxii

# ምስጋና

ከርዕስ መረጣ ጀምሮ ከጎኔ በመሆን የጥናት ስራው እስኪጠናቀቅ ድረስ በቅንነት ለረዱኝ ውድ አማካሪዬ አቶ አብርሃም አለሙ ላደረጉልኝ ሁሉ ከልብ አመሰግናለሁ።

በአባሪ ሁለት ላይ የሰፈራችሁ መረጃ አቀባዮቼ በሙሉ ለዚህ ጥናት የሚያስፈልጉኝን መረጃዎች ባትሰጡኝ ኖሮ ይህ የጥናት ስራ እዚህ መድረስ ባልተቻለው ነበር። እናም ሁላችሁን በጣም አመሰግናለሁ። በተለይ ደግሞ አቶ ሰሎሞን አህመድ፣ እማ ሙሉ ልብሞኝና አቶ ሙሀመድ አንተነህ ታደርጉልኝ የነበረውን ሁሉ መቼም አልረሳውም።

እናንተ ውዶቼ ምን ብዬ እንደማመሰግናችሁ አላውቅም የንጉዬ፣ ጋሽዬ፣ ትጊ፣ ዳኒ፣ አሜክስና ጆሲ ለእኔ እዚህ መድረስ ከእኔ በላይ የእናንተ እጅ ከፍተኛውን ቦታ ይይዛል፤ እግዚአብሄርም የእኔን ደካማነት አውቆ ይመስለኛል በእናንተ መሀል እንድፈጠር ያደረገኝ እና ምን ብዬ ላመስግነው እናንተን ለሰጠኝ ጌታ፤ አንችናሉ አንችም ከጎኔ አብረሽኝ ነበርሽና በጣም አመሰግናለሁ።

ተባባሪ ፕሮፌሰር ዘሪሁን አስፋው፣ ዶ/ር ሞገስ ይገዙ፣ አቶ ገዛኸኝ ጌታቸው፣ ፕ/ር አንድርያስ እሸቴ እና ዶ/ር ባይለዬኝ ጣሰው ለአንድ አመት ነፃ የትምህርት እድል እንዳገኝ በቅንነት ስለረዳችሁኝ ከልብ አመሰግናለሁ።

አቶ ምህረት ተስፋዬ እና አቶ ዋልተንጉስ መኮንን እንደሁለተኛ አማካሪ በመሆን ብዙ ነገር እረድታችሁኛልና ከምስጋና በላይ ምን ልበል።

የተለያዩ ማቴሪያሎችን በመስጠት ለተባበራችሁኝ አቶ መስለ አሰፋ፣ አቶ ወንድወሰን አዳነ፣ አቶ ሙሀመድ አሊ፣ አቶ ሻረው እርቅይሁን፣ አቶ ጌታሁን መስለ፣ አቶ በሀይሉ ጀማነህ፣ አቶ ሞገስ ገብረዮሀንስ እና ሀፍታይ ገብረእግዚአብሄር ስላደረጋችሁልኝ ሁሉ በጣም አመሰግናለሁ።

ይህን ጥናት ለማሳካት እንድችል በገንዘብ ለረዳችሁኝ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ መላከ ኃይል ለይኩን አበጀ (ያንተ ድጋፍ በሁሉም ነውና ምን ልበልህ ውድ ወንድሜ)፣ ወ/ሮ

ቅድስትና አቶ ወርቁ መኮንን፣ አቶ ሚኪሌ ኢዛቅ እና አቶ ተስፋሰም ፀጋዬ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡


ባህር ዳር ከተማ የምትኖሩት ቤተሰቦቼና ጓደኞቼ በቆይታዬ ወቅት ላደረጋችሁልኝ መስተንግዶ እና አቀባበል ሁላችሁንም ከልብ አመሰግናለሁ፡፡ በተለይ መላኩ ወርቁ እንደካሜራ ማን በመሆን እና ቦታ በማሳየት በፀሀይ በብርዱ አብረኸኝ ተንከራተሃልና ውለታህን መቼም አልረሳውም፤ ክፍሌ ዮሀንስ፣ የኔንድ እስቲበል እና አዩዋ (ገነት አርአያ) ውለታችሁ ከባድ ነውና ምን እንደምላችሁ አላውቅም፤ አበ የመስከ ቆይታዬ እንዳይሰለቸኝ በማድረግ በኩል ትልቁን ድርሻ ወስደሃልና ምን ልበልህ፡፡

ባህር ዳር ከተማ ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ የመንግስት መስሪያ ቤትና ድርጅት ኃላፊዎችና ሰራተኞች ላደረጋችሁልኝ መልካም አቀባበል እና ቅን ትብብር ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

በሀሳብና በማቴሪያል ለረዱኝ ጓደኞቼ ብርሃኑ ቦጋለ፣ ዮናስ ወልዴ፣ ቤተልሄም ኃይሉ፣ አስቴር ሙሉ፣ ሊያ መዝገቡ፣ አለምሰገድ እሸቱ፣ ሄለን ኤፍሬም፣ ሙሉቀን ንጋቱ፣ ፀጋዬ ለገሰ፣ ወይንሸት ወልደአብ፣ መልካም ሽባባው፣ ተስፋዬ ሞላ፣ ሰሎሞን ታደለና ደነቀ አበረ በጣም አመሰግናለሁ፡፡ የአይ.ኤል.ኤስ እና የአይ.ኢ.ኤስ ቤተመፃህፍት ሰራተኞች በተለይ ዝናሽና ገነት እንዲሁም የሶሳ ቤተመፃህፍት ሰራተኛ አቶ ተስፋዬ ታደርጉልኝ ለነበረው ሁሉ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ፀሀፊዎች የትባዬንና አይኔአበባ ስለቅን ትብብራችሁ በጣም አመሰግናለሁ፡፡


ፕሪንት በማድረግ ለተባበራችሁኝ ወ/ሮ ትዕግስት መንግስቱ እና ወ/ሪት ስንዱ ተገኝ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

## የኢትዮጵያና የአማራ ክልል ካርታ




ምንጭ፣ ማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ

## የጣና ሀይቅና የባህር ዳር ካርታ




ምንጭ፣ ከDarmon የጥናት ስራ የተወሰደ

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት በነገደ ወይጦ ማህበረሰብ ቃላዊ ዝርው ተረኮችና ባህላዊ ስርዓቶች ላይ የተካሄደ ነው፡፡ በጥናቱ ከቤተመፃህፍት መረጃዎች በተጨማሪ ጥናቱ ስለሚካሄድበት አካባቢና ማህበረሰብ አጠቃላይ ገፅታ፣ በማህበረሰቡ ስለሚነገሩ ቃላዊ ዝርው ተረኮችና ስለሚፈፀሙ ባህላዊ ስርዓቶች በቃለመጠይቅና በምልከታ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

ለጥናቱ አስራ ስምንት መረጃ አቀባዮች የተሳተፉ ሲሆን፣ ከእነዚህ መካከል ዘጠኙ ቁልፍ የመረጃ አቀባዮች ናቸው፡፡ መረጃዎቹም በመቅረፀ ድምፅ፣ በፎቶ ካሜራ፣ በቪዲዮ ካሜራና በማስታወሻ ተይዘዋል፡፡ እነዚህን መረጃዎችም በገላጭ የምርምር ስልትና በተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ (Functional Approach) ለመመርመር ተሞክሯል፡፡ ከጥናቱ ጋር ተዛምዶ ያላቸው አስራ ሦስት የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ፅሁፎችም ተቃኝተዋል፡፡

በጥናቱ በዋናነት የማህበረሰቡን ስያሜ፣ አመጣጥ፣ አምልኮ፣ የስራ ፈጠራ ወይም ባህል፣ እርግማንና ከውሃ ጋር ያላቸውን ግንኙነት የሚያሳዩ አርባ ስምንት ቃላዊ ዝርው ተረኮች ለማየት ተሞክሯል፡፡ ተረኮቹን እንደሚያነሱት ርዕሰ ጉዳይ ተመሳሳይነት በይዘት ለመመደብ ጥረት ተደርጓል፡፡ ባህላዊ ስርዓቶቹ ደግሞ የማህበረሰቡ አምልኮታዊ ስርዓት የሆነው የአቢናዝ፣ የግርዛትና የሰርግ በማለት ከፋፍሎ ለማሳየት ተሞክሯል፡፡

በውጤቱም ቃላዊ ዝርው ተረኮቹ የማህበረሰቡን ስያሜ፣ አመጣጥ፣ አምልኮ፣ የስራ ባህል እና ድህነታቸውን አስመልክቶ የአካባቢው ማህበረሰብ ለሚያደርስባቸው ተፅዕኖ ወይም መገለል ምላሽ የሚሰጡ፣ የማህበረሰቡ አባላት በማንነታቸው እንዲኮሩ እና በራሳቸው ፀንተው እንዲኖሩ የሚያደርጉ ሆነው ተገኝተዋል፡፡

ባህላዊ ስርዓቶቹ ደግሞ አምልኮን፣ ግርዛትንና ሰርግን የተመለከቱ ሲሆኑ፣ አምልኮው የማህበረሰቡ ኑሮ የተመሰረተው ከውሀ ጋር በመሆኑ፣ በውሀው ላይ እንደማይሰምጡ ከውሀው ጅን ጋር ስምምነት መደረሱን በመንገር ያለፍርሃት ስራቸውን እንዲያከናውኑ እንደሚያደርግ እና ከአቢናዝ ድጋፍ ይደረግልናል ብለው እንደሚያምኑ ለማየት ተችሏል፡፡

የግርዛት ስርዓቱ የሚፈፀመው ተገራዡ ልጅ ጀግና፣ አዳኝ፣ መከታ ወይም ደም መላሽ ይሆናል ከሚል አስተሳሰብ እና የሰርግ ስርዓቱ ደግሞ በማህበረሰቡ መካከል መረዳዳት ወይም መተጋገዝ ባህላቸው እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል፡፡

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

ማንኛውም ማህበረሰብ የራሱ የሆነ ባህል፣ ታሪክና ቋንቋ አለው፡፡ በእነዚህ እሴቶቹ አማካይነትም የራሱን ህልውና ያስጠብቅበታል፣ ማንነቱን ይገልፅበታል፣ አመለካከቱንም ያንፀባርቅበታል፡፡ ይህም በመሆኑ በየዘርፉ ያሉ ምሁራን የየማህበረሰቡን አመለካከት፣ እምነትና ማንነት ለማወቅ የጥናት ትኩረታቸው በየማህበረሰቡ ባህል፣ ታሪክና ቋንቋ ላይ ይሆናል፡፡

ለዚህ ጥናት ከተመረጠው የነገደ ወይጦ ማህበረሰብ ጋር ተያይዞም በውጭና በአገር ውስጥ ተመራማሪዎች ጥቂት የጥናት ስራዎች ተካሂደዋል፡፡ ጥናቶቹ በጥቅሉ የሚያተኩሩት ስለወይጦ ማህበረሰብ ኬትመጣ፣ የማህበረሰቡ አባላት በአካባቢያቸው ካለው ማህበረሰብ ጋር ስላላቸው ባህላዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት፣ ስለአመጋገብ ስርዓታቸው፣ በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ ስለሚደርስባቸው መገለል፣ ስለባህላዊ የአስተዳደር ስርዓታቸውና ስለባህላዊ የግጭት አፈታታቸው ነው፡፡

ሆኖም የማህበረሰቡን ቃላዊ ዝርው ተረኮቻቸውንና ባህላዊ ስርዓቶቻቸውን በመመርመር የሚኖራቸውን ማህበራዊ ፋይዳ በተመለከተ አንድም ጥናት አልተካሄደም፡፡ ከዚህ በመነሳት ይህ ጥናት የነገደ ወይጦ ማህበረሰብን ቃላዊ ዝርው ተረኮችና ባህላዊ ስርዓቶች በመመርመር፣ እነዚህ የፎክሎር ሀብቶች በማህበረሰቡ አኗኗር ውስጥ ያላቸውን ፋይዳ ለመተንተን ይሞክራል፡፡

ይህ ጥናት በስድስት ምዕራፎች የተደራጀ ሲሆን፣ በመጀመሪያው ምዕራፍ ውስጥ የጥናቱን አጠቃላይ አቅጣጫ የሚያስተዋውቁ ስምንት ንዑሳን ርዕሶች ተካተዋል፡፡ እነዚህም የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ ዓላማ፣ የጥናቱ ጠቀሜታ፣ የጥናቱ ወሰን፣ የመረጃ አሰባሰብና የአጠናን ዘዴዎች፣ ለጥናቱ የተደረገ ቅድመ ዝግጅትና የመስክ ክንውን፣ ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ የመፍትሔ አቅጣጫዎች ናቸው፡፡

በምዕራፍ ሁለት ጥናቱ የተካሄደበት ማህበረሰብ አካባቢ፣ የማህበረሰቡ ኬትመጣ (Origin)፣ ባህላዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ተካተዋል፡፡ በምዕራፍ ሦስት ደግሞ ክለሳ ድርሳን የቀረበ ሲሆን፣ በዚህ ስርም ሁለት ንዑስ ርዕሶች ተካተዋል፡፡ እነዚህም ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝትና የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት የሚሉ ናቸው፡፡ ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት በሚለው ስር ቃላዊ ዝርው ተረኮችንና ባህላዊ ስርዓቶችን በሚመለከት የተለያዩ ምሁራን ያነሷቸው ንድፈ ሀሳቦች የቀረቡ ሲሆን፣ የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት በሚለው ስር ደግሞ ከዚህ ጥናት ጋር የሚቀራረቡ ጥናቶች ዳሰሳን ይዟል፡፡

በምዕራፍ አራት የወይጦ ማህበረሰብ ቃላዊ ዝርው ተረኮች ያላቸውን ማህበራዊ ፋይዳ ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ በምዕራፍ አምስት ደግሞ የማህበረሰቡን ባህላዊ ስርዓቶች ለመተንተን ጥረት ተደርጓል፡፡ በመጨረሻው ምዕራፍም የጥናቱ ማጠቃለያ፣ የዋቢ ዕሁፎች ዝርዝር እና አባሪዎች ተካተዋል፡፡

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

ማንኛውም ማህበረሰብ ወይም ቡድን የራሱ የሆነ ቃላዊ ዝርው ተረኮችና ባህላዊ ስርዓቶች ይኖሩታል፡፡ እነዚህ የፎክሎር ንዑስ ዘርፎችም ከሌሎች መሰል ዘውጎች ጋር በመጣመር የዚያን ማህበረሰብ ወይም ቡድን ህልውና ያስጠብቃሉ፤ ቀጣይነት እንዲኖረው በማድረግ በኩልም የበኩላቸውን ድርሻ ይወጣሉ፡፡

ከዚህም በመነሳት ቃላዊ ዝርው ተረኮች የአንድን ማህበረሰብ ወይም ቡድን የአኗኗር ስርዓት፣ የአበላል፣ የአጠጣጥ፣ የአለባበስ፣ የአቀማመጥ፣ የአነጋገርና የአካሂያድ ስርዓት ያስተምራሉ (ፈቃደ፣1991፣20)፡፡ በዚህም ምክንያት በማህበረሰቡ ዘንድ ህልውናቸው ተጠብቆ እንዲቆዩ ሆኗል፡፡

ቃላዊ ዝርው ተረኮች ጥልቅ የሆነ መልዕክት የሚያስተላልፉ፣ በአንድ ማህበረሰብ አባላት መካከል የእርስ በርስ ትስስር እንዲኖር የሚያደርጉ ወይም የማህበረሰቡ አባላት በአንድ ገዥ በሆነ አስተሳሰብ ጥላ ስር እንዲገኙ የሚያስችሉ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ ይህን በተመለከተ Bascom ቃላዊ ዝርው ተረኮች ላይ ላዩን ያላቸውን ትርጉም ብቻ በማየት የሚተው ሳይሆን የአንድን ማህበረሰብ ወይም ቡድን አይነኬ ባህል እና ልማድ በነበሩበት ፀንተው እንዲቆዩ በማድረግ፣ የሰዎችን ቁጣ ወይም ንዴት በማብረድ፣ የተፈጥሮንና

የፍጥረታትን ምንነት በመግለፅ፣ በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው ምግባሮች ወደ ቀጣዩ ትውልድ በማስተላለፍ ረገድ ከፍተኛ ሚና እንደሚጫወቱ ይናገራሉ[1] (1969፡21)፡፡ በአጠቃላይ ቃላዊ ዝርው ተረኮች የአንድን ማህበረሰብ ልማድ፣ ባህል፣ እምነት፣ ኬትመጣ ወይም ማንነት፣ አመለካከት፣ ወዘተ. ይገልፃሉ ማለት ይቻላል፡፡

በሌላ መልኩ ባህላዊ ስርዓቶች በአንድ የታሪክ አጋጣሚ የተፈጠሩና በጊዜ ዑደት የራሳቸውን ሙሉ ቅርፅ እየያዙ የመጡ (Ochs,2010:6) ያለፈውን፣ የአሁኑንና የወደፊቱን ማህበረሰባዊ ክስተቶች የሚያስተሳስሩ ሲሆኑ፣ በጊዜና በቦታ የተወሰኑ፣ በህይወትና በሞት ጊዜ የሚቀርቡ ከመሆናቸውም በተጨማሪ ሰዎች ከመለኮታዊ ኃይል ጋር የሚገናኙበት አንዱ መንገድ እንደሆኑ ይታመናል (Berkowitz,2010:14)፡፡

ከዚህም የተነሳ ሰዎች ባህላዊ ስርዓቶቻቸውን ዕለት ከዕለት ከሚያከናውኗቸው ተግባራት በተለየ ራሱን የቻለ ጊዜና ቦታ ሰጥተው፣ ከተለመደው ወይም ከዕለት ተዕለት ህይወት ወጣ ባለ መንፈስ ሲያካሂዱ ይታያሉ፡፡ እነ Sims ባህላዊ ስርዓቶች እንዴት እንደሚካሄዱ ሲገልፁ፣

> ሰዎች አብዛኛዎቹን ባህላዊ ስርዓቶች የሚያካሂዱት በልደት፣ ለአካለ መጠን በሚደርሱ ጊዜ፣ በጋብቻና በሞት ጊዜ በተወሰኑ ሰዎች አማካይነት ሲሆን፣ ጥቂት ባህላዊ ስርዓቶች ግን አንድን ማህበረሰብ ባላጠቃለለ ወይም የተወሰነ መልክዓ ምድራዊ ክልልን ባላቀፈ መልኩ ተመሳሳይ ባህል ባላቸው ቡድኖች መካከል ነው (2005:105)፡፡

በማለት ባህላዊ ስርዓቶች ሲካሄዱ የሚኖራቸውን መልክዓ ምድራዊ ገፅታ፣ የተሳታፊዎችን ብዛትና ተዘውትረው ሊካሄዱባቸው የሚችሉባቸውን አጋጣሚዎች ለማሳየት ሞክረዋል፡፡ ጠቅለል ባለመልኩ ሲታይ ባህላዊ ስርዓቶች በተለየ ጊዜ፣ ቦታና መንፈስ የሚካሄዱ፣ የአንድ ማህበረሰብ ወይም ቡድን ልማድ፣ ባህል፣ አመለካከት፣ እምነት ወዘተ መገለጫ ይሆናሉ ማለት ነው፡፡

ከዚህ በመነሳት ቃላዊ ዝርው ተረኮችና ባህላዊ ስርዓቶች የአቀራረባቸው መንገድ ይለያይ እንጂ የማህበረሰቡን ልማድ፣ ባህል፣ አመለካከትና እምነት በማስተላለፍ በኩል

---

[1] በዚህ ጥናት የተጠቀሱ የውጭ አጥኚዎች በሙሉ በአንቱታ ቀርበዋል፤ ይህም የሆነበት ምክንያት በአብዛኛው የውጭ አጥኚዎችን በፆታ ለይቶ ለማስቀመጥ ስለሚያስቸግር ነው፡፡

ተመሳሳይ፣ ተደጋጋፊ ወይም ተያያዥ ናቸው ማለት ይችላል። የዚህ ጥናት ትኩረትም የተጠኝ ማህበረሰቡን ቃላዊ ዝርው ተረኮችና ባህላዊ ስርዓቶች ማህበራዊ ፋይዳ መመርመር ይሆናል።

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ይህን ጥናት ለማድረግ ያነሳሳኝ ምክንያት ባህር ዳር ከተማ ተወልጄ በማደጌ በከተማዋ ውስጥ ከሚገኙት የአካባቢው ማህበረሰቦች ተነጥለው የሚኖሩት የነገደ ወይጦ ማህበረሰብ አባላት በመካከላቸው የነበረው አንድነት፣ መተጋገዝ፣ አንድነታቸውን የሚጠብቁበት መንገድ፣ ተካፍሎ የመኖር ልማዳቸው በአጠቃላይ የአኗኗር ስርዓታቸውና ህይወታቸው ብዙ ጥያቄዎችን ያጭርብኝ እና ትኩረቴን ይስቡት ስለነበር ወደዚህ የትምህርት ክፍል ገብቼ በምማርበት ጊዜ የመመረቂያ ፅሁፌን በማህበረሰቡ አባላት ላይ እንድሰራ አነሳሳኝ።

በመሆኑም በማህበረሰቡ ላይ ለመስራት ከወሰንኩ በኋላ ከምን አንፃር ልሰራ እንደምችል ለመምረጥ በማህበረሰቡ ዙሪያ የተሰሩ ጥናቶችን በመዳሰስ ያልተሰራበትን እና ያለውን ክፍተት ለመሙላት እንድችል ከመምህራኖቼ ጋር በመመካከር በርዕሱ ዙሪያ የተሰራ ጥናት ባለመኖሩ ለመስራት ምክንያት ሆኖኛል።

## 1.3. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የነገደ ወይጦ ማህበረሰብ ቃላዊ ዝርው ተረኮችና ባህላዊ ስርዓቶች ለማህበረሰቡ አባላት ያላቸውን ማህበራዊ ፋይዳ መመርመር ይሆናል። ይህን ዋና ዓላማ ለማሳካትም ጥናቱ የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች ይኖሩታል።

- በማህበረሰቡ ውስጥ በሚነገሩት ቃላዊ ዝርው ተረኮች የማህበረሰቡ ስያሜ፣ አመጣጥ፣ የስራ ባህልና አምልኮ እንዴት እንደተገለፁ ለማሳየት ይሞከራል።
- የነገደ ወይጦ ማህበረሰብ ቃላዊ ዝርው ተረኮቹንና ባህላዊ ስርዓቶቹን ለአዲሱ ትውልድ የሚያስተላልፍበት ምክንያት ይመረመራል።
- በቃላዊ ዝርው ተረኮቹና በባህላዊ ስርዓቶቹ የሚተላለፉ ጉዳዮች ይተነተናል።
- የማህበረሰቡ አባላት በባህላዊ ስርዓቶቹ ላይ ያላቸው አመለካከት ይፈተሻል።

## 1.4. የምርምር ጥያቄዎች

የጥናቱን ዋና እና ዝርዝር ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ በጥናቱ ሂደት የሚከተሉት ጥያቄዎች ይመለሳሉ፡፡

- በማህበረሰቡ ውስጥ በሚነገሩት ቃላዊ ዝርው ተረኮች የማህበረሰቡ ስያሜ፣ አመጣጥ፣ የስራ ባህልና አምልኮ እንዴት ይገለፃሉ?
- ማህበረሰቡ ቃላዊ ዝርው ተረኮቹንና ባህላዊ ስርዓቶቹን ለቀጣዩ ትውልድ ለምን ምክንያት ያስተላልፋቸዋል?
- የቃላዊ ዝርው ተረኮቹና ባህላዊ ስርዓቶቹ ዋነኛ ጉዳይ ምንድንነው?
- ማህበረሰቡ ባህላዊ ሥርዓቶቹን እንዴት ይመለከታቸዋል? የሚሉት ናቸው፡፡

## 1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ

ጥናቱ ከአላማው የመነጩ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይገመታል፡፡

- ወደፊት የቃላዊ ዝርው ተረኮችንና ባህላዊ ስርዓቶችን በተናጠልም ሆነ አጣምሮ ለሚያጠና የፎክሎር አጥኚ በተወሰነ ደረጃ የመነሻ ሀሳብ ይሰጣል፣
- በማህበረሰቡ ዙሪያ ጥናት ለማድረግ ለሚፈልጉ አጥኚዎች የመረጃ ምንጭ ሆኖ ያገለግላል፣
- ቃላዊ ዝርው ተረኮችና ባህላዊ ስርዓቶች ያላቸውን ተያያዥነት በማሳየት ረገድ የበኩሉን አስተዋፅኦ ያደርጋል፣
- የማህበረሰቡን ቃላዊ ተረኮችና ባህላዊ ስርዓቶች በማጥናት የማህበረሰቡን አመለካከት፣ እምነትና ማንነት በማወቅ ረገድ ጠቀሜታ እንዳለው ለአንባቢዎችና ለአጥኚዎች ተጨማሪ ግንዛቤ ይፈጥራል፡፡

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በነገደ ወይጦ ማህበረሰብ ቃላዊ ዝርው ተረኮችና ባህላዊ ስርዓቶች ላይ በመመስረት ለማህበረሰቡ አባላት የሚያበረክቱትን ማህበራዊ ፋይዳ የሚመረምር ሲሆን፣ እንደ Bascom አገላለፅ ቃላዊ ዝርው ተረኮች በሦስት ይከፈላሉ፤ ተረት (Folktale)፣

አፈ-ታሪክ (Legend) እና ሚት (Myth) በመባል (1965:3)፤ ሆኖም በዚህ ጥናት ውስጥ ሀገረሰባዊ ተረቶችን ለማካተት የተለያዩ ተረቶች የተሰበሰቡ ቢሆንም፣ የማህበረሰቡን አባላት ማህበራዊ ፋይዳ የሚያሳዩ ሆነው ባለመገኘታቸው በጥናቱ ውስጥ አልተካተቱም፡፡ የማህበረሰቡ አባላት የተለያዩ ባህላዊ ስርዓቶችን የሚፈፅሙ ቢሆንም፣ በዚህ ጥናት የሚተነተኑት ግን የአቢናዝ አምልኮታዊ ስርዓት፣ የግርዛት እና የሰርግ ስርዓት ናቸው፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት እነዚህ ስርዓቶች ማህበረሰቡ ከሌሎች የአካባቢው ኗሪዎች ተለይቶ ለብቻው የሚያከብራቸውና እስከአሁንም ድረስ የሚከውናቸው በመሆኑ ነው፡፡

የነገደ ወይጦ ማህበረሰብ በጎጃምና በጎንደር የተለያዩ አካባቢዎች የሚኖሩ ሲሆን፣ በጎጃም ባህር ዳር ከተማና አቸፈር፤ በጎንደር ደግሞ አለፋ ጣቁሳ፣ ፎገራ፣ ደንቢያ፣ ሊቦ ከምከም አካባቢዎች ተበታትነው ይገኛሉ (Solomon,2006:33)፡፡ ሆኖም ከቦታ አንፃር የዚህ ጥናት ትኩረት የሚሆነው ባህር ዳር ውስጥ በሚገኙት የማህበረሰቡ አባላት ላይ ብቻ ነው፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያትም በአጠቃላይ በጎጃምና በጎንደር ከሚኖሩት የማህበረሰቡ አባላት ውስጥ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በከተማዋ ውስጥ የሚገኙ በመሆናቸው (ዝኒ ከማሁ፣ገፅ 34) እና ለመረጃ አሰባሰብ ምቹ በመሆኑ ነው፡፡

## 1.7. የመረጃ አሰባሰብ እና የአጠናን ዘዴዎች

### 1.7.1. የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ

ይህ ጥናት ዓላማዎቹን ለማሳካትና የምርምር ጥያቄዎችን ለመመለስ ቀዳማይና ካልዓይ የመረጃ ምንጮችን ተጠቅሟል፡፡ በካልዓይ ምንጮች ከጥናቱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው የታተሙና ያልታተሙ ፅሁፎች እና ጥናቶች ከቤተመፃህፍት እንዲሁም ከኢንተርኔት የተሰበሰቡ ሲሆን፣ በቀዳማይ የመረጃ ምንጮች ደግሞ ለዚህ ጥናት ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎች ለመሰብሰብ በዋናነት ቃለመጠይቅ (Interview)፣ ምልከታ (Observation) እና ተተኳሪ የቡድን ውይይት (Focus Group Discussion) የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች ተግባራዊ ሆነዋል፡፡

#### 1.7.1.1. ቃለመጠይቅ

ለዚህ ጥናት የሚሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ በዋናነት የተመረጠው ዘዴ ቃለመጠይቅ ሲሆን፣ በዚህ ዘዴ ቃላዊ ዝርው ተረኮችን እና ባህላዊ ስርዓቶችን ጠንቅቀው ያውቃሉ የተባሉ የመረጃ አቀባዮችን በመምረጥ፣ ቀጠሮ በማስያዝ እና የታቀዱ ጥያቄዎችን በመጠየቅ መደበኛ ቃለመጠይቅ የተካሄደ ሲሆን፣ የተለያዩ አጋጣሚዎችን በመጠቀም ደግሞ ኢመደበኛ ቃለመጠይቅ በማድረግ መረጃ ተሰብስቧል። እንዲሁም የተሰበሰቡትን መረጃዎች ትክክለኛነት ለማረጋገጥ እንዲረዳ ተደጋጋሚ ቃለመጠይቅ በማካሄድ እና አንድን ጥያቄ የተለያዩ ሰዎችን በመጠየቅ በ19 የቴፕ ካሴቶች መረጃዎችን ለመሰብሰብ ተችሏል። በዚህም አርባ ስምንት ቃላዊ ዝርው ተረኮችን እና ሦስት ባህላዊ ስርዓቶችን ከዘጠኝ ቁልፍ የመረጃ አቀባዮችና ከዘጠኝ ቁልፍ ያልሆኑ መረጃ አቀባዮች ለጥናቱ ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎች ተሰብስበዋል።

#### 1.7.1.2. ምልከታ

ይህን ጥናት ከግብ ለማድረስ በተወሰነ መልኩ የምልከታ ዘዴ ተግባር ላይ ውሏል። በዚህ ዘዴ የማህበረሰቡን የአኗኗር ስርአት እና በመስክ ቆይታ ወቅት የተፈፀሙ ባህላዊ ስርዓቶች፡- የግርዛት፣ የሰርግና የለቅሶ ስርዓት ላይ በመገኘት የማህበረሰቡን አጠቃላይ ገፅታ፣ የስራ ሁኔታ፣ እርስ በእርስ ያላቸውን ግንኙነት ለመረዳት ተችሏል። በዚህ ዘዴም በፎቶ ካሜራ፣ በቪዲዮ ካሜራ እና ማስታወሻ በመያዝ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ተሞክሯል። ሆኖም በግርዛትና በሰርግ ስርዓቱ ላይ ፎቶግራፍ ለማንሳትና ቪዲዮ ለመቅረፅ ፈቃደኞች ባለመሆናቸው በፎቶም ሆነ በቪዲዮ ቀርፆ ለማስቀረት አልተቻለም።

በፎክሎር ጥናት ከመስክ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ሦስት አይነት መቼቶች (አውዶች) እንዳሉ፤ እነሱም ተፈጥሯዊ (Natural Setting)፣ ቅንብር ተፈጥሯዊ (Induced Natural Setting) እና አርቲፊሻል መቼቶች (Artificial Setting) እንደሆኑ (Goldstein,1974,80-90;ፈቃደ፣1991፣122-124) ይገልፃሉ። በዚህ ጥናትም እንደ አስፈላጊነታቸው ሦስቱ የመቼት አይነቶች ተግባር ላይ ውለዋል። ቃላዊ ዝርው ተረኮችን በቅንብር ተፈጥሯዊና በአርቲፊሻል መቼት የተሰበሰቡ ሲሆን፣ ባህላዊ ስርዓቶቹን ደግሞ በተፈጥሯዊና በአርቲፊሻል መቼት ለመሰብሰብ ተችሏል።

#### 1.7.1.3. ተተኳሪ የቡድን ውይይት

በቃለመጠይቅና በምልከታ የተሰበሰበውን መረጃ ይበልጥ ለመረዳትና ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ተኳኳሪ የቡድን ውይይት ለማካሄድ ተሞክሯል። በቡድን ውይይቱ አስር መረጃ አቀባዮች ተሳትፈዋል። ከእነዚህ ውስጥ ሰባቱ ቁልፍ የመረጃ አቀባዮች ሲሆኑ፣ ቀሪዎቹ ደግሞ ቁልፍ ያልሆኑ የመረጃ አቀባዮች ናቸው። በዚህ ዘዴም መረጃዎችን ለመሰብሰብ መቅረፀ ድምፅ፣ ፎቶ ካሜራና ቪዲዮ ካሜራ አገልግሎት ላይ ውለዋል።

### 1.7.2. የመረጃ አቀባዮች የናሙና አመራረጥ ዘዴ

የናሙና አመራረጡ ከማህበረሰቡ አባላት ውስጥ ስለማህበረሰቡ አጠቃላይ ሁኔታ በቂ እውቀት አላቸው ተብሎ የሚታመንባቸውን ሰዎች በማጠያየቅ እና ኢየሩሳሌም የህፃናትና ማህበረሰብ ልማት ድርጅት ከአማራ ብዙሃን መገናኛ ኤጀንሲ ጋር በመተባበር ያሰራውን ዶክመንተሪ ፊልም ከተመለከትኩ በኋላ ለእኔ ጥናት ይጠቅሙኛል የምላቸውን መረጃ አቀባዮች ዝርዝራቸውን በመያዝ እንዲሁም አቶ ሰሎሞን አጥናፉ የተባሉት አጥኚ በፃፉት ጥናታዊ ፅሁፉ፣ ቁልፍ የመረጃ አቀባዮች ብለው ከዘረዘሯቸው ውስጥ የማህበረሰቡ አባላት በሚኖሩበት አካባቢ እየተዘዋወረ መረጃውን የሰበሰበላቸውን እና ብዙ መረጃ እንዳለው የተነገረኝን ሰው በማፈላለግ መረጃ አቀባዮቹን ለመምረጥ ችያለሁ።

በዚህ መንገድ የተመረጡት መረጃ አቀባዮች በፆታ፣ በእድሜ፣ በትምህርት ደረጃ፣ በስራ/በኢኮኖሚ ደረጃቸው እና ማህበረሰቡ ውስጥ ባላቸው ማህበራዊ ደረጃ ሁሉንም ለማሳተፍ ጥረት አድርጌያለሁ። ከፆታ አንፃር ከቁልፍ መረጃ አቀባዮቹ ውስጥ ሁለት ሴቶች የተካተቱ ሲሆን፣ ቁጥራቸው ከዚህ በላይ መሆን ያልቻለው ቃላዊ ዝርው ተረኮቻቸውንና ባህላዊ ስርዓቶቻቸውን በተመለከተ ሴቶቹ በአብዛኛው በቂ መረጃ ስለሌላቸው ነው። ከሁለቱ ሴቶች አንደኛዋ አባቷ በማህበረሰቡ ውስጥ ከፍተኛ ዝና ያለው አዳኝ ስለነበር ታሪኩን ከቤተሰቦቿ እየሰማች በማደጉ እንዲሁም ሁለተኛዋ ሴት በማህበረሰቡ ውስጥ በእየሩሳሌም ድርጅት ተመርጣ የምትሰራና ስለማህበረሰቡ በቂ መረጃ ያላት በመሆኑ ነው። በተጨማሪም ሁለቱ ሴቶች ከእድሜ አንፃር የድሮውንና የአሁኑን ትውልድ ሊወክሉ የሚችሉ በመሆናቸው ነው።

ሌሎቹ ወንድ የመረጃ አቀባዮች በእድሜ አዛውንት፣ ጎልማሳ እና ወጣት በሚለው ምድብ ውስጥ የሚካተቱ ሲሆን፣ በትምህርት ደረጃቸው ስናይ ደግሞ ዘመናዊ ትምህርት የተማሩ፣ የሀይማኖት ትምህርት የተማሩ እና ምንም ትምህርት የሌላቸው በሚለው ይመደባሉ። በማህበረሰቡ ውስጥ ያላቸውን ማህበራዊ ደረጃ ስናይ የመስጊድ አስተዳዳሪ፣ ማህበረሰቡ ውስጥ በሚፈጠሩ ጉዳዮች ላይ በሽምግልና የሚያገለግሉና ከፍተኛ ቦታ የሚሰጣቸው አዛውንቶች የተካተቱበት ሲሆን፣ ከሚተዳደሩበት ሙያ አንፃር ደግሞ በቀን ስራ የሚተዳደሩና የመንግስት ሰራተኞች ናቸው።

ከእነዚህ የመረጃ አቀባዮች ውስጥ ዘጠኙ ቁልፍ የመረጃ አቀባዮች ሲሆኑ፣ ቁልፍ ተብለው የተመረጡበት ምክንያትም ለጥናቱ ግብዓት የሚሆኑ አስፈላጊ እና ብዙ መረጃዎችን በመስጠታቸው ነው። ሌሎቹ ዘጠኝ የመረጃ አቀባዮች ደግሞ ቁልፍ የመረጃ አቀባዮች ከሰጡኝ መረጃዎች ጋር የሚዛመዱ ተጨማሪ መረጃዎችን በመስጠት የተባበሩኝ ናቸው።

በዚህ መንገድ ከተመረጡት ቁልፍ የመረጃ አቀባዮች በቃለመጠይቅ አማካይነት መረጃውን ለመሰብሰብ ተችሏል።

### 1.7.3. የጥናቱ አተናተን ዘዴ

ለዚህ ጥናት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ከላይ በተጠቀሱት ዘዴዎች ከተሰበሰቡ በኋላ በመስክ ቆይታ ወቅት ጥሬ መረጃውን ለመተንተን ጥረት ተደርጓል። በዚህም በተሰበሰቡት መረጃዎች ላይ የታዩትን ክፍተቶች ለመሙላት ተችሏል። ተጨማሪ መረጃዎችንም በቃለመጠይቅ የተካሄደ ሲሆን፣ በመቅረፀ ድምፅ የተሰበሰቡትንና በማስታዎሻ ደብተር የተያዙትን ከመፃህፍት ጋር በማገናዘብ ትንታኔ ተሰጥቷል።

በዚህ ጥናት ባህላዊ ስርዓቶቹን ለመተንተን የተመረጠው የትንተና ስልት ገላጭ የምርምር ስልት ሲሆን፣ ይህም የተመረጠበት ምክንያት ማህበረሰቡ ባህላዊ ስርዓቶቹን እንዴት እንደሚያካሂዳቸው ለማሳየት የሚረዳ በመሆኑ ነው። በተጨማሪም ጥናቱ ትኩረት ያደረገባቸው ቃላዊ ዝርው ተረኮችና ባህላዊ ስርዓቶች ለጥናቱ ለተመረጠው ማህበረሰብ ያላቸውን ፋይዳ ለመመርመር ደግሞ ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ /Functional Approach/ ቅርበት ያለው ሆኖ በመገኘቱ በዚህ ጥናት እንደ ዋና የመተንተኛ ቴዎሪ ተመራጭ ሆኗል።

## 1.8. ለጥናቱ የተደረገ ቅድመ ዝግጅትና የመስክ ክንውን

ማንኛውም የመስክ ስራ በዘፈቀደ የሚመራ ሳይሆን፣ ተግባራቱ ታቅደው፣ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች ተለይተውና እንዴት ሊፈቱ እንደሚችሉ እስትራቴጂ ተቀይሶ መያዝ አለበት፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥም እነዚህ ሀሳቦች ትኩረት ተሰጥቷቸው እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

### 1.8.1. ቅድመ ዝግጅት

ከቀዳማይ ምንጮች ለጥናቱ ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ወደ መስክ ከመወጣቱ በፊት ስለነገደ ወይጦ ማህበረሰብ ታሪክ፣ ባህልና ከሌሎች አጎራባች ማህበረሰቦች ጋር ስላላቸው ግንኙነት በተያያዘ የተፃፉ ፅሁፎችን፣ መፅሀፎችንና ጥናታዊ ስራዎችን ከቤተመፃህፍት፣ ከኢንተርኔት እና ከግለሰቦች እጅ ለማሰባሰብ ተሞክሯል፡፡ እንዲሁም በርዕሱ ዙሪያ የተሰሩ ስራዎችን በመዳሰስ አስፈላጊ መረጃዎችን ለማጠናቀር ተችሏል፡፡ በተለይም ለጥናቱ የሚያግዙ ቃለመጠይቆችን ለማዘጋጀት ከጥናቱ ጋር ተያያዥነት ካላቸው ጥናቶች ባሻገር በማህበረሰቡ ዙሪያ እውቀት አላቸው ከተባሉ ሰዎች ጋር ለመወያየት ጥረት ተደርጓል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም በመስክ ቆይታ ወቅት መረጃዎችን ለመሰብሰብ የሚያስችሉና በቆይታ ወቅት የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች ግዥና ዝግጅት በማድረግ ሁሉም ነገር እንዲሟላ ጥረት ተደርጓል፡፡

### 1.8.2. የመስክ ክንውን

ቅድመ መስክ ዝግጅቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ሚያዝያ 23 ቀን 2003 ዓ.ም እለተ እሁድ ጉዞዬን ከአዲስ አበባ ወደ አማራ ክልል ዋና ከተማ ባህር ዳር አደረግኩ፡፡ ባህር ዳር ከተማ ከአዲስ አበባ በየብስ ትራንስፖርት 565 ኪ.ሎ ሜትር ርቀት ላይ ትገኛለች፡፡ ባህር ዳር ከተማ የገባሁት 11 ሰዓት አካባቢ ስለነበር እና በጣም ስለደከመኝ ያን ቀን ምንም ማድረግ ስለማልችል የማርፍበት ቦታ በመሄድ እረፍት አደረግኩ፡፡ በማግስቱ ሰኞ ሚያዝያ 24 ቀን 2003 ዓ.ም ጠዋት ተነስቼ ከትምህርት ክፍሉ በሚያዝያ 12 ቀን 2003 ዓ.ም የተፃፈልኝን የድጋፍ ደብዳቤ በመያዝ ወደ አማራ ክልል ባህልና ቱሪዝም

ቢሮ ሄድኩ። ቢሮው ውስጥ ለሚገኙ የሚመለከታቸው አካላት የመጣሁበትን ጉዳይ አስረድቼ በማህበረሰቡ ዙሪያ የተሰሩ ጥናቶች ወይም ፅሁፎች ካሉ እንዲያውሱኝ ስጠይቃቸው፣ በእነርሱ ቢሮ ምንም የተሰራ ጥናታዊ ፅሁፍም ሆነ ሌላ የፅሁፍ መረጃ መኖሩን እንደማያውቁ እና መረጃ ሊኖረው ይችላል የተባለው የቢሮው ሰራተኛ በቀጣዩ ቀን እንደሚገባ ስለነገሩኝ ለቀጣዩ ቀን ቀጠሮ አስይዤ ወደ ባህር ዳር ከተማ አስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ሄድኩ። ከዚያም ምንም የተሰራ ስራ እንደሌለና በክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ሊኖር እንደሚችል በጠቆሙኝ መሰረት ወደ ቢሮው ሄድኩ። ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ አቶ ታፈሰ ካሳ የሚባል ሰው በማህበረሰቡ ዙሪያ በ1978 ዓ.ም ያዘጋጀው የጥናት ፅሁፍ መኖሩን በቤተመፃህፍቱ ካታሎግ ላይ በማግኘቴ ጥናታዊ ፅሁፉን ተውሼ ፎቶ ኮፒ በማድረግ ከመለስኩ በኋላ ሰዓቱ እየመሸ ስለነበርና ቢሮዎች ስለሚዘጉ ወደ ማረፊያዬ ተመለስኩ።

ማክሰኞ ሚያዝያ 25 ቀን 2003 ዓ.ም ጠዋት ወደ አማራ ክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮ በመሄድ አቶ ይርጋን አገኘኋቸውና የመጣሁበትን ጉዳይ ሳስረዳቸው፣ በ1975 ዓ.ም የታተመ ውቢቱ ባህር ዳር የሚል መፅሄት ላይ ስለማህበረሰቡ የተወሰነ ነገር እንዳለ ነግረውኝ መፅሄቱ ከቤታቸው በመሆኑ በቀጣዩ ቀን ደውዬላቸው በሚኖሩበት ሰዓት ሄጄ ፎቶ ኮፒ አድርጌ እንድመልስላቸው ተስማምተን ተለያየን። ከዚያም በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት ውስጥ መረጃ ካገኘሁ በሚል ወደ ጽ/ቤቱ በመሄድ አቶ ምስክር ከሚባሉ ሰው ጋር ተገናኘሁ፤ እሳቸውን በማነጋግርበት ጊዜ በቢሯቸው ውስጥ ማህበረሰቡን በተመለከተ የተሰራ ፅሁፍ እንደሌለና ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ውስጥ ይሰራ የነበረ ሰው በማህበረሰቡ ዙሪያ አንድ ጥናታዊ ፅሁፍ ማዘጋጀቱን ገልፀውልኝ፤ ሰውዬውን አፈላልገው መረጃውን ለመቀበል እንደሚሞክሩ ነግረውኝ፤ ሞባይላቸውን ወስጄ እየደወልኩ ልጠይቃቸው ተስማምተን ወደ አማራ ብዙሀን መገናኛ ኤጀንሲ ሄድኩ። አማራ ብዙሀን መገናኛ ኤጀንሲ ስደርስ ስራ አስኪያጁ ስብሰባ ላይ መሆናቸውን እና እሳቸው ደብዳቤውን ካልመሩልኝ ቤተመፃህፍት ውስጥ መጠቀም እንደማልችል ስለተነገረኝ የደብዳቤዬን ኮፒ ለፀሀፊዋ ሰጥቼ ተመለስኩ።

ረቡዕ ሚያዝያ 26 ቀን 2003 ዓ.ም ለአቶ ይርጋ ደውዬላቸው መረጃውን ለመቀበል ሄድኩ። ውቢቱ ባህር ዳር መፅሄት እና የአማራ ህዝብ ባህልና ቋንቋ የሚለውን መፅሀፍ ሰጥተውኝ ፎቶ ኮፒ አድርጌ መለስኩላቸው። ከዚያም ወደ ኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት

በመሄድ አቶ ምስክርን ሳናግራቸው መረጃ አለው የተባለውን ሰው ለማፈላለግ በራሳቸው ስልክ የተለያየ ቦታ ቢደውሉም የሰውዬውን አድራሻ ማግኘት ስላልቻሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ውስጥ የጥናት ወረቀቱ ካለ በሚል የተለያዩ ሰዎች ጋር ሲደውሉ የተባለው ሰውዬ የፃፈውን ጥናት የሚያውቅ ሰው ባለመኖሩ ለሌላ ጊዜ አፈላልገው ካገኙት እንደሚደውሉልኝ ቃል ገብተውልኝ ወደ አማራ ብዙሃን መገናኛ ኤጀንሲ ሄድኩ፡፡ እዚያም ስራ አስኪያጁ ደብዳቤዬን መርተውልኝ ስለነበር የቤተመፃህፍት ሰራተኛው በነገደ ወይጦ ላይ የተሰራ አንድ ጥናታዊ ፅሁፍ መኖሩን ነግሮኝ የአቶ ምስጌ ቢራራን ፅሁፍ ኮፒ አድርጌ መለስኩ፡፡ ከዚህ ሌላ በኢየሩሳሌም ድርጅትና በአማራ ብዙሀን መገናኛ ኤጀንሲ ትብብር የተሰሩ ዶክመንተሪ ፊልሞች እንዳሉ ተነግሮኝ የሚመለከታቸውን ሰዎች ሳነጋግር የአርበኞችን በዓል ለማክበር ልዩ ዝግጅት በመኖሩ ሰሞኑን ከላይብረሪ የተሰሩትን ፊልሞች ለመፈለግና ፊልሙን ለማየት የሚያስችሉት መሳሪያዎች ስለሚያዙ በሚቀጥለው ሳምንት እንድመለስ ተነጋግረን ተለያየን፡፡

ሀሙስ ሚያዝያ 27 ቀን 2003 ዓ.ም መስሪያ ቤቶች ዝግ ስለሆኑ የማህበረሰቡን አባላት ለመተዋወቅ እና ለመግባባት እንዲያመቸኝ ከሰኞ እስከ ረቡዕ በነበሩት ቀናቶች ሳጠያይቅ የአማራ አቀፍ ልማት ማህበር ከእነሱ ጋር የልማት ስራ እንደሚሰራና ያንን የልማት ስራ ከሚያስተባብሩት ውስጥ አንዱ የቅርብ ዘመዴ እንደሆነ ተነግሮኝ ስለነበር ረቡዕ ማታ አግኝቼ ሁሉንም ተነጋግረን ለዛሬ ሊያስተዋውቀኝ የማህበረሰቡ አባላት ሴቶች መሶብ እየሰፉ የሚሸጡበት ቦታ ለማየት እና እንደ ረዳት መስከኛ የሚያገለግለኝን የማህበረሰቡን አባል ሊያስተዋውቀኝ በተቀጣጠርነው መሰረት ተገናኘን፡፡ ከዚያም ከኡስማን ጋር ተዋወቅንና ስለጥናቱ በተወሰነ መልኩ ካስረዳሁት በኋላ ሙሉአለም አዳራሽ አጠገብ ከሚገኘው የመሶብ መሸጫ ቦታ ወስደውኝ የየኔጓድ እህት እንደሆንኩና የምፈልገውን መረጃ እንዲሰጡኝ ኡስማንና የኔጓድ አስተዋወቁኝ፡፡ እኔም ከተዋወቅሁ በኋላ ከእነ ኡስማን ጋር ትንሽ አውርተን መረጃ ለመሰብሰብ የሚመቸው እሁድ ጠዋት እንደሆነና በሌላ ቀን የማህበረሰቡ አባላት በተለያየ የጉልበት ስራ የሚተዳደሩ በመሆኑ ማግኘት እንደማልችል ኡስማን በነገረኝ መሰረት እሁድ ጠዋት የማህበረሰቡ አባላት በአብዛኛው በሚገኙበት ቀበሌ 16 ከ.ዳነ ምህረት ጀርባ ልንገናኝ ተቀጣጥረን ተለያየን፡፡ እኔም ተመልሼ መሶብ ወደ ሚሸጡት ሴቶች በመሄድ ለመግባባት ያክል አብሬያቸው ሳወራ እግረ መንገዴንም አንዳንድ ነገር ስጠይቃቸው ውዬ እሁድ ስፈራቸው እንደምመጣ ነግሬያቸው ተመለስኩ፡፡

አርብ ሚያዝያ 28 ቀን 2003 ዓ.ም የአማራ ክልል ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ እና ሌሎች በማህበረሰቡ ዙሪያ መረጃ ይኖራቸዋል ወደ ተባልኩበት ቢሮ እየሄድኩ መጠየቅ ጀመርኩ። ሆኖም በፊት ካገኘኋቸው ፅሁፎች ውጭ ምንም ነገር አላገኘሁም። በመጨረሻም አቶ ሰሎሞን አጥናፉ የሚባል ሰው አክሽን ኤይድ ኢትዮጵያ ድጋፍ አድርጎለት በማህበረሰቡ ዙሪያ ጥናት እንዳደረገ ተነገረኝና የሴቶች ጉዳይ ቢሮ እንደሚሰራ ስለጠቆሙኝ እኔ ያሰሁበትና የተባለው ቢሮ የሚገኝበት አካባቢ ስለሚራራቁ ሰኞ ለመሄድ ወሰንኩ።

ቅዳሜ ሚያዝያ 29 ቀን 2003 ዓ.ም ለኡስማን ደወልኩለትና በዚያን ቀን ከተገናኘን በኋላ የምፈልገውን መረጃ ይሰጡኛል ብሎ የሚያስባቸውን ሰዎች እንዲመርጥልኝና እሁድ ጠዋት የማህበረሰቡ አባላት በሚሰበሰቡበት የእድር እና የእቁብ እንዲሁም የቡና መጠጣት ስርዓት ላይ ተገኝቶ እንዲያግባባልኝ ተስማምተን ተለያየን። እኔም ለቀጣዩ ቀን ጠዋት መረጃ ለመሰብሰብ የሚያስፈልጉኝን ቁሳቁሶች አዘጋጅቼ አጠናቀቅሁ።

እሁድ ሚያዝያ 30 ቀን 2003 ዓ.ም በጠዋት ተነስቼ ፎቶ እንዲያነሳልኝና ቪዲዮ እንዲቀርፅልኝ ከእኅቱ ልጅ ጋር በመሆን ወደ ቀበሌ 16 ሄድን። የማህበረሰቡ አባላት እሁድ እሁድ ጠዋት በ12 ሰዓት አካባቢ ተሰባስበው የሚጠጡት የቡና ስርዓት አላቸው፤ ከዚያ ሲወጡ እድርና እቁብ ይጥላሉ። በየሁለት ሳምንቱ ደግሞ የማህበረሰብ ውይይት ሲያደርጉ ስለሚያካሂዱ እስከ 6 ሰዓት ይሰበሰባሉ። ከእኅቱ ልጅ ጋር ስፈራቸው ስንደርስ በአካባቢው ምንም ሰው ባለማግኘቴ ኡስማን ጋር ደወልኩለት። ከዚያ መጥቶ እድር እና እቁብ ጨርሰው ወደ ስብሰባ ሊገቡ ስለሆነ 7:30 አካባቢ እንድንመጣ ነገረን። እኛም ቆይተን በተባልነው ሰዓት ደረስን። ሁሉንም ሰብስቦ ጠበቀን። በእማ ሙሉ ቤት ቡና በማስፈላት ሼህ ጅብሪል ሰማኸኝ፣ ኡስማን መሀመድ፣ አንሻ ያረጋል፣ ሰጡ የኔሁን፣ ምሳዬ ያሲን እና ዘይንዬ አንተነህ በመሆን ቡና እየጠጣን የመተዋወቂያና የመግባቢያ እንዲሁም በየመሀሉ አንዳንድ መረጃዎችን እየጠየቅሁ የምፈልጋቸውን መረጃዎች ስሰበስብ ዋልኩ፤ ተመልሼ እንደምጠይቃቸው ተስማምተን ተሰነባበትን። ከዚያም አንድ ሌላ ዘመዴ በጠቆመኝ መሰረት እነ ሼህ ቸርነት ዘሪሁን ቤት በመሄድ አባ ይመር ሙጩዬንና ሼህ ቸርነትን አነጋግሬ ተመለስኩ።

ሰኞ ግንቦት 1 ቀን 2003 ዓ.ም ጠዋት ወደ ብዙሀን መገናኛ ኤጀንሲ ሄድኩ። ላይብረሪ ውስጥ ፊልሞቹ ሲፈለጉልኝ ዋሉ። ሁለቱ ተገኝተው አንዱ በመጥፋቱና የሚያሳዩበት መሳሪያ ቤጋስ የሚባለው ስለተያዘ በቀጣዩ ቀን እንድመጣ ቀጠሩኝ። እኔም አቶ

ሰሎሞንን ለማግኘት ሴቶች ጉዳይ ቢሮ ብሄድ ተቀይሮ ወደ ደሴ እንደሄደ ነገሩኝ። የሞባይሉን ቁጥር ተቀብዬ ስደውልለት የጥናት ፅሁፉን አክሽን ኤይድ ሄጄ አቶ ጌታቸውን አነጋግሬ ማየት እንደምችል ነገረኝ።

ማክሰኞ ግንቦት 2 ቀን 2003 ዓ.ም ወደ አክሽን ኤይድ በመሄድ አቶ ጌታቸውን አግኝቼ የመጣሁበትን ጉዳይ ሳነጋግራቸው ፎቶ ኮፒ አድርጌ እንድመልስ ነግረውኝ ተቀብዬ ወደ አማራ ክልል ብዙሀን መገናኛ ኤጀንሲ ሄድኩ። ከዚያም የስራ መጨናነቅ ስለነበረባቸው አንዱን ፊልም አሳይተውኝ ሌላ ቀን እንድመጣ ነገሩኝ። ኢየሩሳሌም የህፃናትና ማህበረሰብ ልማት ድርጅት ከማህበረሰቡ ጋር የተለያዩ ስራዎች እንደሚሰራ ስለተነገረኝ ወደ ድርጅቱ ጽ/ቤት በመሄድ ስራ አስኪያጁን አቶ እደግልኝ ፈንታን ሳነጋግራቸው በድርጅታቸው አንድ ጥናታዊ ፅሁፍ እንደተዘጋጀና ፅሁፉ የሚገኘው ድርጅቱ ባሰራው ደጃች ገነሜ ቤተመፃህፍት ውስጥ መሆኑን እና አውሰውኝ ፎቶ ኮፒ ማድረግ እንድችል ማስታወሻ ፅፈውልኝ ተመለስኩ። ከዚያም ወደ ሰፈራቸው በመሄድ የመስጊድ አስተዳዳሪ ከሆኑት አቶ ሙሀመድ አንተነህ ጋር ከተዋወቅሁ በኋላ ሌላ ቀን ልንገናኝ በቀጠሮ ተለያየን።

ረቡዕ ግንቦት 3 ቀን 2003 ዓ.ም ጠዋት የማህበረሰቡ አባላት ወደ ሚኖሩበት ሰፈር ስሄድ ባጋጣሚ አንድ ሰው ሞቶ ለቅሶ ላይ ደረስኩ። ከዚያ ድንኳኑ ውስጥ በመግባት ከእማ ሙሉ ጋር ሁኜ የለቅሶ ስርዓቱን ተከታተልኩ። የማህበረሰቡ አባላት የእስልምና እምነት ተከታይ በመሆናቸው ሴቶቹ ሬሳ ሸኝተው ሲመለሱ አብሬ በመመለስ አንዳንድ ሴቶችን ሳነጋግር ቆየሁና ወደ ቀብር ቦታው ያልሄዱና መረጃ ያውቃሉ የተባሉትን ሰው እማ ሙሉ አስተዋውቀውኝ ከአባ ሰይዴ ጋር ከለቅሶው ቤት ወጥተን መስጊድ አካባቢ ተቀምጠን አንዳንድ መረጃዎችን ነገሩኝ። ከዚያም ሼህ ጅብሪል ሰማኸኝ እየሩሳሌም ባሰራላቸው ሻወር ቤት ትኬት ቆራጭ ስለሆኑ ወደ ሻወሩ ቤት ሄጄ ስራቸውን እየሰሩ የተለያዩ መረጃዎችን ሲነግሩኝ እስከምሳ ሰዓት ድረስ አብረን ቆየን። ከሰአት በኋላ ባብዛኛው የማህበረሰቡ አባላት ልጆች ወደ ሚማሩበት ቁልቋል ሜዳ የመጀመሪያ ደረጃ ሙሉ ሳይክል ትምህርት ቤት በመሄድ ርዕሰ መምህሩን በማነጋገር የማህበረሰቡ አባላት ልጆች ተረት ፅፈው እንዲያመጡልኝ በማድረግ እንዲተባበሩኝ ስጠይቃቸው ወደ አማርኛ መምህርቷ መሩኝና የመጣሁበትን ጉዳይ አስረድቻት አርብ ድረስ አስፅፋ እንደምትጠብቀኝ ነግራኝ ተለያየን።

ሀሙስ ግንቦት 4 ቀን 2003 ዓ.ም ወደ ደጃች ገነሜ ቤተመፃህፍት በመሄድ ስራ አስኪያጁ የፃፉልኝን ማስታወሻ በማሳየት የተባለውን ጥናታዊ ፅሁፍና የአቶ ሰሎሞንን ጥናት ፎቶ ኮፒ በማድረግ ለቤተመፃህፍቱና ለአክሽን ኤይድ ከመለስኩ በኋላ ወደ አማራ ክልል ብዙሀን መገናኛ ኤጀንሲ ስሄድ ለቀጣዩ ቀን ጠዋት ቀጠሩኝ። ወደ ክልሉ ኮሙዩኒኬሽን ጽ/ቤት ሄጄ አቶ ምስክርን ስጠይቅ አልገቡም ስለተባልኩ በተደጋጋሚ ሞባይላቸው ላይ ብሞክርም ሊነሳልኝ ስላልቻለ ተመለስኩ።

አርብ ግንቦት 5 ቀን 2003 ዓ.ም ጠዋት ወደ ብዙሀን መገናኛ ኤጀንሲ ሄጄ የጠፋው ፊልም በመገኘቱ ሁሉንም ፊልሞች አይቼ ወደ ቁልቋል ሜዳ ትምህርት ቤት ስሄድ፣ መምህርቷ በየክፍሉ ካስፃፈችው ተረቶች ውስጥ በጣም ጥቂት የማህበረሰቡ ተወላጅ ተማሪዎች ብቻ በመፃፋቸው በየክፍሉ ያሉትን የማህበረሰብ ልጆች ጠርታልኝ የሚያውቁትን ተረት እንዲነግሩኝ በማድረግ መረጃዬን በመቅረፀ ድምፅ ሰበሰብኩ። ልጆቹም ተረት የሚያውቁትን አሮጊቶች ስም ነግረውኝ በቀጣዩ ቀን ሰፈራቸው ብሄድ እንደማገኛቸው ጠቆሙኝ። ከዚያ ወደ መናሪያ ሰፈራቸው ሄጄ አባ ሰይዴን ስላገኘኋቸው ከእሳቸው ጋር አንዳንድ መረጃዎችን ሲነግሩኝ ቆይቼ ተለያየን።

ቅዳሜ ግንቦት 6 ቀን 2003 ዓ.ም ተረት ያውቃሉ ወደ ተባሉት ባልቴት በመሄድ እንዲነግሩኝ ከተስማማን በኋላ የተወሰኑ ተረቶችን ነግረውኝ በቀጣዩ ቀን ስመለስ ሌላውን አስታውሰው ሊጠብቁኝ ተነጋግረን ወደ ሌላዋ መረጃ አቀባዬ ሄድኩ። እሷም የተወሰኑ ተረቶችን ከነገረችኝ በኋላ ወደ አቶ ሙሀመድ ቤት በመሄድ የሚያውቁትን መረጃ ሲነግሩኝ ውለው ሌላ ቀን ልንገናኝ ተቀጣጥረን ተለያየን።

እሁድ ግንቦት 7 ቀን 2003 ዓ.ም እማ ይጋርዱ ጋር በመሄድ የተወሰኑ ተረቶች ነገሩኝ። ከዚያ እማ ሙሉና ዘይንዬን በማነጋገር ሰፈራቸው ውስጥ የተዳረ ሰው ስለነበር የሰርጉን ስርዓት ስከታተል ቆይቼ ወደ ማረፊያዬ ሄድኩ። በዚህ ቀን ግን አቶ ሰሎሞን ጥናቱን በሚያጠና ጊዜ መረጃዎችን የሰበሰበለትን ሰው አግኝቼ ተዋወቅሁትና አልማ እንደሚሰራ ገልፆልኝ በቀጣዩ ቀን ከስራ ሲወጣ ልንገናኝ ተቀጣጠርን።

ሰኞ ግንቦት 8 ቀን 2003 ዓ.ም የግርዛት ስርዓት ስለሚፈፀም ወደ ሰፈራቸው በጠዋት ደርሼ ስርዓቱን ስከታተል ዋልኩ፤ ፎቶ ለማንሳትና ቪዲዮ ለመቅረፅ ቢከለክሉኝም እስከ

አመሻሹ ድረስ ቆይቼ አንዳንድ ፈቃደኛ የሆኑ ሰዎችን በማነጋገር ፕሮግራሙ ወደ መጠናቀቁ ሲል ለሰሎሞን ደውዬለት ተገኛኘንና መረጃዎችን ሲነግረኝ አመሸ፡፡

ከማክሰኞ ግንቦት 9 ቀን 2003 ጀምሮ እስከ ግንቦት 30 ቀን 2003 ዓ.ም ድረስ ከሰሎሞን ጋር እየተገናኘን የተለያዩ መረጃዎችን ይነግረኝ ነበር፡፡ በተጨማሪም በቂ እውቀት ይኖራቸዋል የሚላቸውን ሰዎች እየጠቆመኝና ቤታቸውም ድረስ እየወሰደኝ የተለያዩ ሰዎችን ለማነጋገር ችያለሁ፡፡ በእነዚህ ቀናት ውስጥ የመረጃ አቀባዮቹ በሚመቻቸው ሰዓት እና ቦታ እየተቀጣጠርን በተደጋጋሚ የምፈልገውን መረጃ ለመሰብሰብ ችያለሁ፡፡ ባጋጣሚ ግንቦት 15 ቀን 2003 ዓ.ም ደልጊ የሚኖሩት ሼህ ነጃት ሰላይኑ ለግል ጉዳይ ወደ ባህር ዳር መጥተው ስለነበርና መረጃ አቀባዮቼም ስለማህበረሰቡ የተለያዩ መረጃዎች እንደሚያውቁ በጠቆሙኝ መሰረት ለማነጋገር ችያለሁ፡፡ በተጨማሪም ስለማህበረሰቡ የሚገልፁ የታሪክ መጻሕፍት ያላቸውን አባውንቶች በማውቃቸው ሰዎች እያፈላለኩ የሚጠቅሙኝን መረጃዎች ፎቶ ኮፒ በማድረግ ማስቀረት ችያለሁ፡፡ አቶ ምስክር አፈላልግልሻለሁ ያሉኝ ሰውም እስከምመጣ ድረስ ባለመገኘቱ የጥናት ወረቀቱን ለማግኘት አልቻልኩም፡፡ የማህበረሰቡን የህዝብ ብዛትና ለጥናቴ የሚያስፈልጉ ካርታዎችን ለመሰብሰብ ወደ ሴንትራል ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ፣ ማዘጋጃ ቤትና የአማራ አቀፍ ልማት ማህበር በመሄድም ለመሰብሰብ ችያለሁ፡፡ ባህር ዳር ዩኒቨርስቲ በመሄድም በማህበረሰቡ ዙሪያ የተሰሩ ጥናቶችን ለማየት ሞክሬያለሁ፡፡

በአጠቃላይ ከሚያዝያ 23 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ግንቦት 30 ቀን 2003 ዓ.ም ድረስ በባህር ዳር ከተማ ቆይታ በማድረግ ለጥናቴ የሚሆኑ መረጃዎችን ከሰበሰብኩ በኋላ ሰኔ 1 ቀን 2003 ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ ተመልሻለሁ፡፡

## 1.9. ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ የመፍትሔ እቅጣጫዎች

በመስክ ቆይታዬ ወቅት መረጃ ለመሰብሰብ የተለያዩ ችግሮች ያጋጠሙኝ ቢሆንም፣ በተሳካ ሁኔታ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ እንዲያስችለኝ የተለያዩ የመፍትሄ አቅጣጫዎችን በመጠቀም የነበረውን ክፍተት ለመሙላት ጥረት አድርጌያለሁ፡፡

ካጋጠሙኝ ችግሮች ውስጥ የመጀመሪያው፣ መረጃውን ያውቃሉ ተብለው የሚመረጡት ግለሰቦች የሚጠይቁኝ የብር መጠን በተማሪ አቅም የማይቻል ከመሆኑም በላይ

ባነጋገርኳቸው ቁጥር በየጊዜው እንድከፍላቸው መፈለጋቸው ነበር። ይህን ችግር ለመቅረፍም እንዳንድ አላማዬ የገባቸው መረጃ አቀባዮች ሌሎቹን እንዲያግባቡልኝና እንዲያሳምኑልኝ በማድረግ፣ እንዲሁም በየጊዜው ወደ መኖሪያ አካባቢያቸውና በቆይታዬ ወቅት በነበሩ ማህበራዊ አጋጣሚዎች ላይ ሁሉ በመገኘት፦ አብሬ በመሳተፍ፣ ቡና በመጠጣት እና የቡና ቁርስ በመብላት ለእነሱ ጥሩ አመለካከት እንዳለኝ በማሳየት ነበር።

እንደ ሁለተኛ ችግር ሊነሳ የሚችለው የማህበረሰቡ አባላት በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ በመሆናቸው በእነሱ ላይ የሚሰሩ አጥኚዎች ሁሉ በአጭር ጊዜ ካለባቸው ችግር እንደሚያላቅቋቸው ያምኑ ስለነበር እና አንዳንድ አጥኚዎችም በቀላሉ መረጃውን ለማግኘት ሲሉ ያለባቸውን ችግር እንደሚቀርፉላቸው ስለሚነግሯቸው ከዚህ በፊት በተደጋጋሚ መረጃ ሲሰጡ ቆይተዋል። ሆኖም ያ ያሰቡት ለውጥ ባለመምጣቱ ሁሉም የማህበረሰቡ አባላት ከአሁን በኋላ ለሚመጣ ማንኛውም ሰው መረጃ ለመስጠት የተማማሉ ይመስል ፈቃደኞች አልነበሩም። እንደውም አንዳንዶቹ የእኛን ታሪክ እየወሰዳችሁ መክበሪያ አደረጋችሁን በማለት እያንዳንዱ የማህበረሰቡ አባል ምንም አይነት መረጃ እንዳይሰጥ ያሳድሙብኝ ነበር። ከዚህም ሌላ በሄድኩበት ቦታ ሁሉ በጥርጣሬ አይን የሚከታተሉኝም ነበሩ። እንዲህ አይነት ሁኔታ በተለይ በመጀመሪያዎቹ የመስክ ቆይታዬ ወቅት በተደጋጋሚ ያጋጠሙኝ ሲሆን፣ ይህንን ጉዳይ ለመፍታትም የጥናቱን አላማ የተረዱ የማህበረሰቡ አባላት ሌሎች ሰዎችን የማሳመን ስራ እንዲሰሩልኝ በማድረግ፣ የጥናቱን አላማ እና በማህበረሰቡ ዙሪያ መጠናቱ የሚሰጠውን ጠቀሜታ እውነታውን በመንገር እንዲተባበሩኝ በማድረግና በቆይታዬም ጥሩ ግንኙነት በመፍጠር መረጃውን ለመሰብሰብ ችያለሁ።

እንደ ሦስተኛ ችግር ሊነሳ የሚችለው የማህበረሰቡ አባላት በአብዛኛው የሚተዳደሩት በጉልበት ሥራ በመሆኑ መረጃ ለመሰበሰብ አስቸጋሪ ሁኔታ ገጥሞኝ ነበር። በቀጠሮኝ ጊዜና ቦታ ለማግኘት አስቸጋሪ ነበር። በተለይ ወንድ የመረጃ አቀባዮቹ ድንገል ለመቁረጥ እና ለወፍጮ የሚሆን ድንጋይ ለማምጣት ራቅ ወዳለ ቦታ ስለሚሄዱና የቀን ሥራ ለመስራት ስለሚዘዋወሩ ብዙዎቹ በሚገኙበት ሰዓት ማለትም ሁልጊዜ ማታ ማታ እና እሁድ እሁድ ጠዋት በመሄድ ለመሰብሰብ ችያለሁ። ይህም ብዙ ጊዜ መስክ እንድቆይ አድርጎኛል።

በመጨረሻ ደረጃ ሊነሳ የሚችለው ችግር ማህበረሰቡን በሚመለከት በቂ መረጃ ይኖራቸዋል እየተባልኩ የሄድኩባቸው በባህር ዳር ከተማ የሚገኙ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ምንም አይነት የተፃፈ መረጃ ባለመኖራቸው እና ከአንዱ መስሪያ ቤት ወደ አንዱ በመንከራተት ጊዜዬን እና ጉልበቴን ያባከንኩ ቢሆንም፣ ተስፋ ባለመቁረጥ ባደረኩት ሙከራ ከመንግስት መስሪያ ቤቶችና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጥቂት የጥናት ፅሁፎችን ለማግኘት ችያለሁ።

# ምዕራፍ ሁለት

## የነገደ ወይጦ ማህበረሰብ ማህበረ-ባህላዊ ዳራ

በዚህ ምዕራፍ ስለ ነገደ ወይጦ ማህበረሰብ አጠቃላይ ገለጻ ለማድረግ ይሞከራል። በተለይ ስለማህበረሰቡ ጥንተ አመጣጥ፣ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊና የእርስ በርስ ግንኙነት ላይ ትኩረት ይደረጋል።

### 2.1. የነገደ ወይጦ ጥንተ አመጣጥ

የነገደ ወይጦ ማህበረሰብ በጎንደርና በጎጃም አካባቢ በጣና ሀይቅ ዙሪያና ወደ ጣና የሚፈሱ ወንዞችን ተከትለው ይኖራሉ (Teclehaimanot,1984:1)[2]። የማህበረሰቡን አመጣጥ በተመለከተ ግልፅና ተጨባጭ መረጃ እስከ አሁን ድረስ አልተገኘም (Solomon,2006:23)።

ስለነገደ ወይጦ ለመጀመሪያ ጊዜ የፃፉት የኢየሱሳውያን መልዕክተኛና በአስራ ሰባተኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ወደ ኢትዮጵያ መጥተው የነበሩት Almaida ሲሆኑ፣ በወቅቱ የማህበረሰቡ አባላት በንግድ የሚተዳደሩና ጉማሬዎችን በመግደል ስጋቸውን ለምግብነት፣ ቆዳቸውን ለአለንጋ፣ ለጋሻ እና ለልጓም መስሪያነት እንደሚያውሉት፣ ከደንገል ደግሞ ታንኳ እንደሚሰሩ መግለፃቸውን ሆኖም የማህበረሰቡን ስም በግልፅ አለመጥቀሳቸውን Beckingham and Huntingford (1954:35) በጻፉት መጽሐፍ ማስፈራቸውን Teclehaimanot ይናገራል (1984:4)።

የማህበረሰቡን ስም በግልፅ በመጥቀስ ለመጀመሪያ ጊዜ የፃፉት ከ1770 - 1771 በጎንደር የቆዩት James Bruce ሲሆኑ፣ ነገደ ወይጦ አዳኝ፣ ጉማሬ ገዳይ፣ ከአካባቢው ማህበረሰብ የተለየ የራሳቸው ቋንቋ ያላቸው፣ በክርስትናና በእስልምና እምነት ተከታዮች መካከል እየኖሩ የራሳቸው የሆነ ሃይማኖት የሌላቸው ህዝቦች እንደሆኑ ጠቅሰዋል (Teclehaimanot,1984:4)።

ከBruce በኋላ በአስራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ወደ አካባቢው የመጡት ፈረንሳዊው ተጓዥ Guillaume Lajean (1870) ወይጦዎች የኦሮሞ አንዱ ጎሳ ከሆነው

---

[2] በዚህ ጥናት ውስጥ በውጭ ቋንቋ የተፃፉ ስራዎች በሙሉ እንደ ኤሮፓውያን ዘመን አቆጣጠር ቀርበዋል።

ዋቶ ጋር ዝምድና ያላቸው ሲሆኑ እንደሚችሉ መጥቀሳቸውን Teclehaimanot ይገልፃል (ዝኒ ከማሁ፣ገፅ 5)።

ከ1866 እስከ 1868 በጎንደርና በጣና ሐይቅ አካባቢ የኖሩት Hormuzd Rassam ስለነገደ ወይጦ አመጣጥ ከLajean ጋር ተመሳሳይ የሆነ መላምት የሰነዘሩ ሲሆን፣ ሁለቱም የጉማሬ ስጋ እንደሚበሉ ጠቅሰው በተለይ ወይጦዎች ጉማሬ ለመግደል መርዝ የተቀቡ ጦሮችን እንደሚጠቀሙ ይናገራሉ (Rassam,1869:134)።

በ1840ዎቹ መጀመሪያ ጀምሮ እስከ ሞቱበት 1860ዎቹ በጎንደርና በጣና ሀይቅ አካባቢ የኖሩት Plowden ደግሞ ነገደ ወይጦዎች ጉማሬ አዳኞችና ከደንገል የሚሰሩ ታንኳዎችን እንደሚሰሩ ጠቅሰው ስለቋንቋቸውና ሃይማኖታቸው ግን ምንም ሳይሉ አልፈዋል። (Plowden,1969:194)።

Piaggia ደግሞ ስለነገደ ወይጦ የአኗኗር ዘይቤና በአካባቢው ባሉት ማህበረሰቦች የተለዩ እንደሆኑ ጠቅሰው፣ ወይጦዎች ከኢሲያ የተሰደዱ ከአማራ ጋር በሕብረት ለመኖር ፈቃደኛ ያልሆኑና በሂደት በአማራ ተፅዕኖ ስር የወደቁ በማለት ይገልፃሉ (Teclehaimanot,1984:6)።

ከPiaggia በኋላም በነገደ ወይጦ ኬትመጣ (Origin) ዙሪያ የፃፉ ምሁራን የነበሩ ሲሆን ከእነዚህ መካከል E. Cerulli, F.S. Simoons, E. Gamst, Asme Walda Silassie እና ሌሎችም እንዳሉ ይጠቅሳል። እነዚህ ምሁራን በዋናነት የሚያነሱት ነገደ ወይጦ ከቀደምት የኢትዮጵያ ሕዝቦች መካከል አንዱ እንደሆነ ነው (ዝኒ ከማሁ፣ገፅ 7)።

Asme እንደሚለው ከሆነ ነገደ ወይጦዎች በአንድ ወቅት Jabarti የሚባል ቋንቋ ይናገሩ እንደነበር ገልፆ፤ በተለይ በንጉስ ሱስንዮስ (1607-1632) ካቶሊክ ሃይማኖትን እንዲቀበሉ ይገደዱ እንደነበር ጠቅሷል (ዝኒ ከማሁ፣ገፅ 8)። በተመሳሳይ Darmon የወይጦ ቋንቋ በአሁኑ ጊዜ የጠፋ ቢሆንም ከዘመናት በፊት ግን በጣና ሀይቅ እና በሰሜን ኢትዮጵያ አካባቢ ይነገር እንደነበር ይገልፃሉ (2010:1)።

Teclehaimanot (1984) ግን በማህበረሰቡ ላይ ጥናት በሚያካሂድበት ጊዜ ከአማርኛ በተለየ የወይጦ ቋንቋ የሚባል አንድም ቃል ሲነገር አለመስማቱን፣ ሆኖም አንድ የማህበረሰቡ አባል ነኝ የሚልና በባህር ዳር ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ የሚሰራ ሰው

Lahemegna (የነገዴዎች ቋንቋ) ነው ብሎ ሲናገር እንደሰማ ገልጿል፡፡ ሆኖም ለዚህ ጥናት መስክ ላይ በነበርኩበት ጊዜ በአደን ጊዜ ከጠላቶቻቸው ለመደበቅና ጠላቶቻቸውን ለማጥቃት የሚጠቀሙበት የምስጢር ቋንቋ እንደነበራቸው ከጠቀሱልኝ ውጭ የተለየ ቋንቋ እንደሌላቸው ገልፀውልኛል፡፡

በሌላ መልኩ ነገደ ወይጦ በ2360 ዓመት ወደ ኢትዮጵያ እንደገቡ ገልፀው በ3140 ዓመተ ዓለም በምስርና በሱዳን አገር ብርቱ ርሀብ በመከሰቱ የአባይን ወንዝ ተከትለው ጉማሬውን፣ አዞውን፣ ይብራውን፣ ጋጋኖውንና ሌሎቹን አዕዋፍ እያደኑና ዓሳም እያጠመዱ ኢትዮጵያ ውስጥ ከገቡ በኋላ ግማሾቹ በጣና ባህር ዙሪያ ሲቀመጡ፣ ቀሪዎቹ ደግሞ ወደ ከፋ መሄዳቸውን ይገልፃሉ (ታዬ፣1920:12፤ ዮሐንስ፣1940:108)፡፡

Teclehaimanot በበኩሉ ነገደ ወይጦዎች በመልክና በቁመና በአካባቢው ካሉ ከአማራና ከአገው ማህበረሰቦች የማይለዩ መሆናቸውን ጠቅሶ፣ ወይጦዎች አማርኛ ከመናገራቸው በፊት የአገውኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ሊሆኑ እንደሚችሉ ይገልፃል (1984:9)፡፡

## 2.2. አስተዳደራዊ ሁኔታን በተመለከተ

ባለፉት ዘመናት ዋታ (Watta) በኦሮሞ፣ ማንጆ (Manjo) በከፋ፣ ሚድጋን (Madgan) ዞማልና (Zumaal) ያቢር (Yibir) በሶማሌ፣ ፉጋ (Fuga) በጉራጌ ተገልለው እንደኖሩት ሁሉ ነገደ ወይጦም በአማራ ተፅዕኖ ይደረግባቸው ስለነበር በፖለቲካ ረገድ ይህ ነው የሚባል ቦታ እንዳልነበራቸው ይጠቅሳል (ምስጌ፣1979:2፤Solomon,2006:27)፡፡

ሆኖም ቀደም ብሎ ማህበረሰቡ ራሱን በራሱ የሚያስተዳድርበት ነጋድራስ የሚባል ስርዓት እንደነበረው አንዳንድ በማህበረሰቡ ላይ ጥናት ያደረጉ ምሁራን ይናገራሉ (Teclehaimanot,1984:31;Solomon,2006:41;ምስጌ፣1979:2)፡፡

የነገደ ወይጦ ማህበረሰብ በድሮ ጊዜ በጭቃ ሹም ወይም በአጥቢያ ዳኝነትና በመሳሰሉት የሹመት ቦታዎች ተመድበው እንደማያውቁ ጠቅሶ፣ ሆኖም ማንኛውንም የውስጥ አስተዳደርና የፀጥታ ጉዳይ የሚታየው ነጋድራስ ወይም አሳዳኝ በሚባል ማዕረግ በሚታወቀውና በማህበረሰቡ አማካይነት በተመረጠው ሰው እንደሆነ ይናገራል (ምስጌ፣1979:2)፡፡ ነጋድራሱ ኑሯቸው በእርሻ ላይ ከተመሰረተ የነገዱ አባላት በመስቀል

ጊዜ ግብር ሰብሳቢ የነበረ ከመሆኑም ሌላ የአሞራ ግብር (የማህበረሰቡ አባላት ማንኛውንም አይነት አውሬ ባደኑ ጊዜ የሚከፈል ክፍያ) የመቀበል ስልጣን ነበረው።

በወቅቱ የነበረው አሳዳኝ ወይም ነጋድራስ የሚባለው የማህበረሰቡ መሪ ህዝቡን በማስተዳደሩ የሚከፈለው ምንም አይነት ምንዳ አልነበረውም፤ ሆኖም ደንብ አፍርሶ ሲገኝ በስሩ የነበሩት የህዝቡ ሽማግሌዎች ከስልጣኑ አውርደው ሌላ የጎበዝ አለቃ በምትኩ ይሾማሉ። ይህ ነጋድራሱን አውርዶ በምትኩ ሌላ ሰው የሚሾመው የሽማግሌዎች ሸንጎ የሚመሰረተው ታዋቂና ተሰሚነት ባላቸው የማህበረሰቡ አባላት ነው። የሽማግሌዎች ሸንጎ አባል መሆን የሚቻለው በገደሉት ጉማሬ ብዛት ይሆናል። ነጋድራስ የሚባለውና በሽማግሌዎች ሸንጎ ይመራ የነበረው የማህበረሰቡ አስተዳደራዊ ስርዓት በጊዜ ሂደት እየቀረ ሄዶ አባጋር በሚባል አስተዳደራዊ ስርዓት የተተካ ሲሆን የአባጋር ስልጣን የነጋድራሱን ያህል የጎላ አለመሆኑን፣ ይህም የሆነበት ምክንያት ማህበረሰቡ በሂደት በተከተለው የእስልምና ሃይማኖት ስልጣኑ በመከፋፈሉ እንደሆነ ይነገራል (አየለ፣1998:21)።

ነገደ ወይጦ እስከ አፄ ሱስንዮስ ዘመነ መንግስት በተለይ ከአራቱ ጎሳ አንዱ የሆነው የሽሎ ጎሳ በከንፈሮ አባይ ላይ (አባይ ከጣና ሲወጣ) ይካሄድ የነበረውን ማንኛውንም የማጓጓዝ አገልግሎት ይዞ የነበረ ሲሆን፣ በኋላ ግን የዛብያ ልጆች በሚባል የአማራ ማህበረሰብ አባላት በመነጠቁ ምክንያት ከዚያ በፊት ያገኘው የነበረውን ጥቅም አጥቷል (ምስጌ፣1979:3)።

በኢጣሊያ ወረራ ጊዜ ጣሊያኖች ማህበረሰቡን ሊያቀርቧቸውና ከእነርሱ ጋር እንዲሰለፉ ለማድረግ ሙከራ ቢያደርጉም የተሳካ ውጤት አላመጡም (ዝኒ ከማሁ፣ገጽ 4)።

## 2.3. ኢኮኖሚያዊ ሁኔታን በተመለከተ

በሰው ልጅ ታሪክ አዳኙ ለማደኛ፣ አርብቶ አደሩ ለግጦሽ፣ አርሶ አደሩ ደግሞ ለእርሻ የሚውል መሬት መኖሩ መሰረታዊ ጉዳይ ነው (Solomon,2006:39)። የነገደ ወይጦ ማህበረሰብም አስቀድሞ በሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ በጣና ሐይቅ ዙሪያ የመሬት ባለቤት እንደነበር ይጠቅሳል (Teclehaimanot,1984:24)።

ሆኖም በሂደት የመሬት ባለቤትነታቸውን እያጡ ከሄዱ በኋላ የሚያርሱት መሬት እና በንግድ ለመተዳደር የሚያስችል አቅም ባለመኖራቸው የኑሮ ህልውናቸው ወደ አደንና ልዩ ልዩ ባህላዊ ነገሮችን ወደ መስራቱ አዘነበሉ (ምስጌ፣1979፡5) በማለት ይናገራል፡፡

በሌላ መልኩ ታፈሰ የማህበረሰቡ አባላት ከጥንት ጀምሮ በአያትና በቅድመ አያቶቻቸው እንደሚደረገው በሀይቅና በወንዞች ዳርቻ በመኖር ከውሃ ውስጥና ከአካባቢው የሚያገኟቸውን ነገሮች እንደሚመገቡ ጠቅሶ፣ እንደዋነኛ የገቢ ምንጭ (Source of Income) አድርገው የሚጠቀሙባቸው ስራዎች ዓሳ ማስገር፣ የድንጋይ ወፍጮ መውቀር፣ ታንኳ ከደንገል መስራት፣ ሴቶች ስፌት በመስፋትና ፈትል በመፍተል፣ የማገዶ እንጨት በማቅረብና ለምግብነት የሚያገለግሉ እንደ ጉማሬ የመሳሰሉትን እንስሳት በማደን እንደሆነ ይገልፃል (1978፡4)፡፡

## 2.4. ማህበራዊ ግንኙነትን በተመለከተ

የማህበረሰቡ አባላት ማህበራዊ መዋቅር የአዳኝ፣ የጎሳና የነገድ ደረጃዎች በመባል በሦስት ይከፈላሉ፡፡ አዳኝ የሚባለው ማህበረሰቡን በያታ፣ በዕድሜ ወይም አባላቱ በነገዱ ውስጥ ባላቸው ስልጣን ሳይወሰን የአዳኝ አባላትን ያቅፋል፡፡ ጎሳ በነገዱ ውስጥ ያሉት የፉጋ፣ የደምባቂራ፣ ፉጋግራና ሽሎ ጎሳዎች እያንዳንዳቸው የሚጠሩበት ሲሆን፣ የአዳኝ መዋቅርንም ያቅፋል፡፡ ነገድ ደግሞ በነገዱ ውስጥ ያሉት ጎሳዎች በአንድ ላይ የሚጠሩበት ስያሜ ነው፡፡ በነገዱ ውስጥ በስካርና በሌላ ጥቅም ምክንያት ግጭት ወይም ጠብ ሲፈጠር ከላይ የተጠቀሱትን ደረጃዎች ጠብቀው መፍትሄ ይሰጣሉ፡፡ ግጭቱ ከሌላው ማህበረሰብ ጋር ከሆነም በየደረጃው የተጠቁትን ክፍሎች በማገናኘት ግጭቱ በሰላማዊ መንገድ የሚፈታበትን ሁኔታ ያመቻቻሉ (ምስጌ፣1979፡7-8)፡፡

የነገደ ወይጦ ማህበራዊ ተቋም ሁሉም በእኩልነት እንዲኖር የሚፈቅድ ነው፡፡ በማህበረሰቡ መካከል የጎላ የገቢ ልዩነት የማይታይ ሲሆን፣ እርስ በርስ በመረዳዳት፣ በመተባበርና ሁሉን በእኩል የማየት ባህል እንዳላቸው ይነገራል፡፡

በነገደ ወይጦ ማህበረሰብ ብዙ ጉማሬ የሚገድሉት ተለይተው የጎሳው መሪዎች ይሆኑ እንደነበር፣ ሆኖም በአሁኑ ጊዜ የዚህ አይነት ስርዓት የሌለ ሲሆን፣ የማህበረሰቡን ማህበራዊ ተቋም በኃላፊነት የሚመሩት የማህበረሰቡ ሽማግሌዎች ናቸው፡፡ በማህበራዊ ሕይወታቸው አንዱን አባል ከሌላው ለይተው የማይዩ ቢሆንም እንኳ በአንዳንድ ጉዳዮች

ላይ ሴቶቻቸው እኩል እንዲሳተፉ እድል አይሰጧቸውም፡፡ የማህበረሰቡ ሽማግሌዎች በቡድኑ መካከል፣ የተጣሉትን በማስታረቅ፣ ፍትህ በመስጠት፣ በማጋባት፣ በማፋታት ረገድ ኃላፊነቱን ወስደው ይሰራሉ፡፡ እነዚህ ሽማግሌዎች ጥፋተኛውን አባል ከማህበራዊ ህይወት እንዲገለል እስከ ማድረግ ድረስ የሚደርስ ቅጣት የመወሰን ስልጣን አላቸው፡፡

በአሁኑ ጊዜ ግን ልማዳዊው የማህበረሰቡ የፍትህ ስርዓት ዘመናዊ በሆነው የቀበሌና የወረዳ ፍርድ ቤቶች እየተተካ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ነገደ ወይጦዎች በባህር ዳር ከተማ አንድ እድር ያላቸው ሲሆን፣ ሁሉም የማህበረሰቡ አባላት የእድሩ አባል ናቸው፡፡ ማህበረሰቡ እንደ እድር ሁሉ እቁቦችም አሏቸው (Solomon,2006:78-79)

የነገደ ወይጦ ማህበረሰብ በሌላው የአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ ተገልለው የኖሩ እንደሆኑ ይጠቀሳል፡፡ የመገለላቸው አይነተኛ ምክንያት ከአካባቢው ማህበረሰብ በተለየ ሁኔታ ጉማሬ፣ አምባዛ፣ በተፈጥሮና በሌሎች አጋጣሚ የሞተና ያልታረደ የቤት እንስሳ የመመገብ ልማድ ስላለቸው ነው (የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ባህልና ቱሪዝም ቢሮ፣2001፡36)፡፡ ይህም ሆኖ ግን በሰርግና በሌሎች የግብዣ ስርዓት ላይ ጥሪ የሚደረግላቸው ቢሆንም፣ በግብዣው ላይ ግን በተለየ ዕቃ ይሰጣቸዋል እንጂ ከሌላው ማህበረሰብ ጋር በአንድነት እንዲበሉ አይፈቀድላቸውም፡፡ በአንዳንድ መጠጥና ምግብ ቤቶች ደግሞ የማህበረሰቡ አባላት የበሉበት ወይም የጠጡበት ዕቃ እንዲቃጠል ወይም እንዲጣል ይደረጋል (ምስጌ፣1979፡7)፡፡ የነገደ ወይጦ ማህበረሰብ አባላት የእስልምና እምነት ተከታይ በሚጠቀሙበት መቃብር ቦታና በሚሰግዱበት መስጊድ እኩል የመጠቀም መብት አልነበራቸውም (ዝኒ ከማሁ፣ገጽ 8)፡፡ እንዲያውም የአማራ ማህበረሰብ ነገደ ወይጦ የተገኘው ከዛፍ ወይም ከባህር ነው እያለ ያገላቸው ነበር (Solomon,2006:81)፡፡

በአሁኑ ጊዜ የነገደ ወይጦ ማህበረሰብ ከሌላው የአካባቢው ማህበረሰብ ጋር የጠነከረ ግንኙነት ለመፍጠር ፍላጎቱ ቢኖረውም በሌላው ማህበረሰብ ዘንድ ግን ግንኙነት እንዲኖር ፍላጎት አይታይም (Jerusalem Children and Community Development Organization,2009:33)፡፡ ይህም ሲባል በነገደ ወይጦና በሌላው ማህበረሰብ መካከል ምንም አይነት ግንኙነት የለም ማለት አይደለም፡፡ በተለይ በሞት፣ በሰርግና በሌሎች ድንገተኛ አደጋዎች ጊዜ የገንዘብና የጉልበት መተጋገዝ አለ (Solomon,2006:78)፡፡

## 2.5. ባህላዊ ግንኙነትን በተመለከተ

የነገደ ወይጦ ማህበረሰብ ከሞላ ጎደል በአካባቢው ካለው ማህበረሰብ ተመሳሳይ ባህል ቢኖረውም፣ በአንዳንድ ባህላዊ ስርዓቶቹ ግን የሚለይባቸው ገፅታዎች አሉት።

በማህበረሰቡ ውስጥ የወንድ ልጅ ግርዛት ሁለት አይነት ሲሆን፣ አንደኛው ህፃኑ በተወለደ በሰባተኛ ቀኑ የሚፈፀም ሲሆን፣ ሁለተኛው የግርዛት አይነት ህፃኑ ካደገ በኋላ ትልቅ ድግስ በመደገስ የሚከናወን የግርዛት ስርዓት ነው። ይህ በነገዱ ያለው የግርዛት ስርዓት በአካባቢው ከሚገኘው ማህበረሰብ ይልቅ በከፍተኛ ደረጃ ይከበራል። በስርዓቱ ወቅት እንደቤተሰቡ አቅም የተለያዩ ዝግጅቶች በማድረግ በግና ፍየል ወይም በሬ በማረድ ያከብሩታል። አባሉ ስርዓቱን በተገቢው መንገድ ለመፈፀም የገንዘብ እጥረት ካጋጠመው ከማህበረሰቡ አባላት ተበድሮ ወይም መዋጮ ሰብስቦ ለማክበር ይገደዳል።

ሌላው ማህበረሰቡ የራሱ የሆነ የሰርግ ስርዓት አለው። በተለይ በቀደመው ጊዜ የማህበረሰቡ አባል የሰርግ ስርዓት ለማድረግ ሲፈልግ አስቀድሞ ወንዱ ተጋቢ ጉማሬ መግደል ይጠበቅበታል። ጉማሬ የገደለ ወንድ ከማህበረሰቡ አባላት የፈለጋትን ልጃገረድ ማግባት ይችል ነበር። ከጊዜ በኋላ ግን ጉማሬ እየጠፋ በመሄዱና ድርጊቱም እንደ ጎጅ ባህል በመታየቱ ሊቀር ችሏል።

በአሁኑ ጊዜ ብዙም የተለመደ ባይሆንም ሁለቱ ተጋቢ የማህበረሰቡ አባላት ትዳር ለመመስረት የሚችሉ መሆናቸውን ከተስማሙ በኋላ ሴቷ ከቤተሰቦቿ ጠፍታ ወደ ወንዱ ቤት ትሄዳለች። ከዚህ በኋላ ወንድዬው የታወቁ የማህበረሰቡን ሽማግሌዎች መርጦ የሴቷን ቤተሰቦች እንዲያሳምኑለት ይልካል። የእርሷ ቤተሰቦች ፈቃደኛ ከሆኑ በሁለቱ ቤተሰቦች እርዳታና በተጋቢዎች ጥረት "ክንድሽ በክንዴ ክንድህ በክንዴ ይሁን" በመባባል ትዳራቸውን ይመሰርታሉ።

በጋብቻ ወቅት የማህበረሰቡ አባላት የተለመደው የጥሎሽ ልማድ ወንዱ ለሴቷ ብቻ እንዲሰጥ የሚያስገድድ ነው። የወንድ ሚዜዎች ሙሽራዋን ወደ ወንዱ ቤት ይዘው ሲሄዱ "የወሮ ዘመድ" የሚል ድምፅ ሲያሰሙ በልጅቷ የሰርግ ስርዓት ላይ የተገኘው ዘመድ "እኔ አለሁ ዘመድ" እያለ ሳሙና፣ አምባር፣ ሌሎች ጌጣጌጦችን፣ የተፈጨ ጨው፣ ቅመምና ሌሎች አስፈላጊ ነገሮችን ይሰጣል (ምስጌ፣ 1979:9-10)።

# ምዕራፍ ሦስት

## ክለሳ ድርሳን

በዚህ ምዕራፍ ከቃላዊ ዝርው ተረኮችና ከባህላዊ ሥርዓቶች ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሙያዊ ቃላትና ፅንሰ ሐሳቦች ይብራሩበታል። ከዚህም በተጨማሪ ከጥናት ርዕሱ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ጥናቶች በመዳሰስ ያላቸውን አንድነትና ልዩነት ለማሳየት ይሞከራል።

### 3.1. የንድፈ ሀሳቦች ቅኝት

የፎክሎር ባለሙያዎች ፎክሎርን በጥቅል ከማጥናት ይልቅ በተለያዩ ፈርጆች ከፋፍሎ ማጥናት የተሻለ እንደሆነ ይገልፃሉ። Dorson የፎክሎርና የፎክላይፍ ጥናት በአራት ሰፋፊ ክፍሎች እንደሚመደቡ ጠቁመው፣ እነሱም፣ ስነቃል (Oral Literature) ወይም ቃላዊ ጥበብ (Verbal Art)፣ ቁሳዊ ባህል (Material Culture)፣ ሀገረሰባዊ ልማድ (Social Folk Custom) እና ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት (Performing Folk Arts) እንደሆኑ ይገልፃሉ (Dorson,1972:3)። እነዚህ የፎክሎር ክፍሎች ሰፊ እንደመሆናቸው መጠን በስራቸው ተካተው የሚጠኑ የተለያዩ ዘውጎች አሏቸው (Sims,2005:13)።

ብዙ የዘርፉ ምሁራን ከፎክሎር አይነቶች መካከል አንዱን ብቻ በመምረጥ ማጥናት እንደሚሻል ይናገራሉ፤ ሆኖም እያንዳንዱን የፎክሎር አይነት በጥልቀት ለመረመረው በአንዱ የፎክሎር ዘውግ ውስጥ ሌላ የፎክሎር ዘውግ ውህደት ፈጥሮ ሊገኝ ይችላል። ይህን አስመልክቶ እነ Sims Tolekenን ጠቅሰው የፎክሎር ዘውጎች አንዱ በአንዱ ውስጥ ሊከሰት ይችላል ይላሉ (2005:17)።

በዚህ ጥናትም ቃላዊ ዝርው ተረክንና ባህላዊ ሥርዓትን በአንድ ላይ በማጣመር ለማሳየት ይሞከራል።

#### 3.1.1. ቃላዊ ዝርው ተረክ

ቃላዊ ዝርው ተረክ (Oral Prose Narrative) የስነቃል አንዱ ክፍል ሲሆን፣ ተለጣጣቂነት ወይም ተከታታይነት ያላቸው ድርጊቶችና ሁነቶች የሚፈፀሙበት፣

በድርጊቶቹ ውስጥ የሚሳተፉ ባለታሪኮች ያሉበት፣ ድርጊቱ የሚፈፀምበትን ቦታና ጊዜ የሚያሳይ ታሪክ ነው። ይህን አስመልክቶ Oring ቃላዊ ዝርው ተረክ በሁነቶችና በድርጊቶች የተዋቀረ የአንድን ቡድን ወይም ማህበረሰብ ልማድ ለማስተላለፍ የሚጠቅም መሣሪያ ነው በማለት ይገልፃሉ (1986፡122)። በመሆኑም ተረክ ተከታታይ ድርጊቶች ቃላዊነታቸውን ሳይለቁ በዝርው ቅርፅ የሚቀርብበት ነው ማለት ይቻላል። ይህ ሲባል ግን ተረክ ተራ የሆነ የድርጊቶች ዘገባ ሳይሆን በተረኮች አማካይነት ስርዓት ባለው ሁኔታ ቅደም ተከተላቸውን የጠበቁ ድርጊቶች፣ በትረካው የሚገለፀውን መልዕክት የሚያስተላልፉ ባለታሪኮች ወይም ገፀባህሪያትን የሚያካትት ነው። በአጠቃላይ ቃላዊ ዝርው ተረክ በውስጡ የአንድን ማህበረሰብ ወይም ቡድን አመለካከት፣ እምነት፣ ባህል፣ ወዘተ. የሚያንፀባርቅ ነው ማለት ይቻላል።

ቃላዊ ዝርው ተረክ ከሰው ልጅ ታሪክ ጋር የጠበቀ ግንኙነት ያለውና በማንኛውም ማህበረሰብ ወይም ቡድን ውስጥ ሊገኝ የሚችል እንደሆነ ፊቃደ ቃላዊ ዝርው ተረክ በማንኛውም ማህበረሰብ ውስጥ ያለ በዕለታዊ ሕይወት በተለያየ መልክ የሚከወን ነው ይላል (1991፡52)። በተመሳሳይ Dégh ቃላዊ ዝርው ተረኮች በማንኛውም ማህበረሰብ እንደሚነገሩት ሁሉ በየትኛውም አካባቢና ማህበራዊ ሁኔታ (Social Condition or Climate) ሊቀርቡ እንደሚችሉ ይናገራሉ (1972:54)።

የቃላዊ ዝርው ተረክ ኬትመጣ ከቅድመ ታሪክ ሰው ልማዶችና እምነቶች የተገኘ ሲሆን፣ በተፈጠረበት ማህበረሰብ ወይም ቡድን ውስጥ ለረጅም ዘመን ሳይጠፋ ከትውልድ ትውልድ ሲተላለፍ የቆየ ነው፤ ተስተላልፎውም እንደ ዘመኑ ተጨባጭ ሁኔታና እንደሚነገርበት ማህበረሰብ አቋም ራሱን በማስማማት ወይም በመለዋወጥ ሊሆን ይችላል። ይህን በተመለከተ Dégh ቃላዊ ዝርው ተረክ የማያረጅ ወይም ዘላለማዊ፣ ሲተረክ ስሜት የሚይዝና ከሰው ልጅ የስልጣኔ ታሪክ ጋር አብሮ የሚጓዝ፣ ራሱንም እንደዘመኑ ሁኔታ በመቀያየር የሚኖር እንደሆነ ይናገራሉ (1972:54)።

Vansina በበኩላቸው ቃላዊ ዝርው ተረክ ከሰው ወደ ሰው በቃል የሚተላለፍ እንደሆነና የቆይታ ጊዜውም ከአንድ ትውልድ በላይ ሊዘልቅ እንደሚችል ይገልፃሉ (1985:101)። በአፍሪካ የስነቃል ጥናት በቀዳሚነት ከሚጠቀሱት ምሁራን መካከል አንዷ የሆኑት Finnegan ደግሞ በማንኛውም ማህበረሰብ ውስጥ ያሉ የቃላዊ ዝርው ተረክ አይነቶች

ህልውና ተጠብቆ የሚቆየው፣ በማህበረሰቡ ውስጥ ባላቸው ክዋኔና ከትውልድ ትውልድ በሚደረገው ቃላዊ ተስተላልፎ እንደሆነ ይገልፃሉ (1970:380)።

በሌላ መልኩ ቃላዊ ዝርው ተረኮች የአንድን ማህበረሰብ አይነኬውን ባህል (taboo) እና ልማዱን ጠብቆ ማቆያ ከመሆናቸውም ባሻገር፣ የማህበረሰቡን አባላት ቁጣ ወይም ንዴት በማብረድና ነባራዊውን አለም በመግለፅ በኩል አስተዋፅኦ አላቸው (Bascom,1969:21)።

በአጠቃላይ ቃላዊ ዝርው ተረክ ተከታታይነት ያላቸው ድርጊቶች ወይም ሁነቶች የሚፈፀምበት፣ የድርጊቱ ተሳታፊ ባለታሪኮችን የያዘ፣ ድርጊቱ የሚፈፀምበትን ቦታና ጊዜ የሚያሳይ፣ የአንድን ማህበረሰብ ባህል ለማስተላለፍ የሚጠቅም፣ ከሰው ልጅ ታሪክ ጋር የጠበቀ ትስስር ያለውና በዕለታዊ ሕይወት በተለያየ መልኩ የሚከወን ታሪክ ነው ማለት ይቻላል።

በሌላ መልኩ የአንድን ማህበረሰብ ቃላዊ ዝርው ተረክ ለማጥናት ሲፈለግ ትኩረት መደረግ ያለባቸው ነገሮች አሉ። እነሱም በተረኮቹ አማካይነት የሚተላለፈው መልዕክት ምንድን ነው? ለተረኮቹ መፈጠርና መነገር ምክንያት የሆነው ጉዳይ ምንድን ነው? ተረኮቹን ተራኪዎቻቸውና ታዳሚዎቻቸው እንዴት አድርገው ይመለከቷቸዋል? የሚሉትን ጥያቄዎች ተረድቶ መልስ መስጠት እንደሚገባ (Dégh,1972:54) ይገልፃሉ። ከዚህም በመነሳት ይህ ጥናት እነዚህን እና ሌሎች መሰል ጥያቄዎችን ትኩረት ውስጥ በማስገባት ቃላዊ ዝርው ተረኮቹ ለተጠኝ ማህበረሰቡ የሚሰጡትን ፋይዳ ለመመርመር ይሞክራል።

### 3.1.2. ባህላዊ ሥርዓቶች

ባህላዊ ሥርዓቶች (Rituals) የህገረሰባዊ ልማድ አንዱ ክፍል እንደሆነ የፎክሎር አጥኚዎች ይናገራሉ። ባህላዊ ሥርዓቶች በአንድ ቡድን ወይም ማህበረሰብ ውስጥ ለረጅም ዘመናት ፀንተው የቆዩትን ረቂቅ እሴቶች፣ እምነቶችና አመለካከቶች ገልፆ ለማሳየት የሚጠቅሙ አይነተኛ መሣሪያዎች ናቸው። ይህን በተመለከተ እነ Sims ባህላዊ ሥርዓቶች እያንዳንዱ ቡድን ወይም ማህበረሰብ በተደጋጋሚ የሚያከብራቸው ወይም የሚከውናቸው ሲሆኑ፣ የማህበረሰቡን ጥልቅ ወይም ረቂቅ ልማዶችን ለቡድኑ አባላትና ለውጭው ማህበረሰብ በግልፅ በሚታይ መልኩ ለማቅረብ ይጠቅማሉ በማለት ይገልፃሉ (2005:95)።

ባህላዊ ሥርዓቶች ነባሩ ትውልድ የእኔ ብሉ ይሏቸው ያቆያቸውን ባህላዊ እሴቶች በቀጣዩ ትውልድም ህልውናቸው ተጠብቆ እንዲዘልቁ ለማድረግ ይረዳሉ፤ በመሆኑም ባህላዊ ሥርዓቶች ለቡድኑ አባላት በተለይም ለአዲሱ ትውልድ ስለባህላቸው በቂ መረጃ እንዲያገኙ የሚያስችል፣ ጊዜን ጠብቆ የሚደጋገም፣ ከትውልድ ትውልድ የሚተላለፍ፣ ዕኑ መልዕክቶችን፣ ባህላዊ እሴቶችንና ረቂቅ አስተሳሰቦችን በተግባር በክወና የሚያሳይ ነው (Kottak,2002:307)። ይህን ሀሳብ በማፅናት እነ Sims ባህላዊ ሥርዓቶች ድብቅ ወይም ረቂቅ የሆኑ እሴቶችን፣ እምነቶችንና አመለካከቶችን ለፎክሎር ተመራማሪውና ለማህበረሰቡ አባላት በጉልህ ወይም በግልፅ እንዲታዩና እንዲጨበጡ በማድረግ በኩል ጠቀሜታ አላቸው ይላሉ (2005:97)።

ባህላዊ ሥርዓቶች የቡድኑን ወይም የማህበረሰቡን ባህላዊ እሴቶችን፣ አመለካከቶችንና እምነቶችን ከትውልድ ትውልድ ከማስተላለፋቸው እና ጎልተው እንዲታዩ ከማድረጋቸው ባሻገር ስርዓቱ ሲከበር ወይም ሲከወን በቡድኑ አባላት ዘንድ የጎደለው እንዲሟላላቸው፣ ያጡትን እንደሚያገኙ፤ ያገኙትንም ደግሞ ህልውናው ተጠብቆ እንዲዘልቅ ከሚል እምነት እንደሚመነጭም ይነገራል። ይህን በተመለከተ Ray ባህላዊ ሥርዓቶች ከበሽታ ለመፈወስ፣ ትውልድን ለማባዛት፣ ጠላትን ድል ለማድረግ፣ የቡድኑን ማህበራዊ ደረጃ ከፍ እንዲል ለማስቻል፣ ኃጢአትን ለማስተሰርይ እና መጭውን ጊዜ ለመተንበይ ይከወናሉ በማለት ይገልፃሉ (1976:78)።

ባህላዊ ሥርዓቶች የሚደጋገሙና በዘወትራዊ ድርጊቶች የተቀናጁ፣ ምክንያታዊ በሆነ መንገድ የሚከወኑ፣ በከፍተኛ ደረጃ የተደራጁና ባዕድ ስርዓት እንዳይገባባቸው በጥንቃቄ የሚጠበቁ፣ የማህበረሰቡን አባላት ማንነት በሚያመላክት ወይም በሚያስተዋውቅ መልኩ የሚያቀርቡ ናቸው (Sims,2005:96)።

ሥርዓቶቹ በቡድኑ ወይም በማህበረሰቡ ሙሉ ስምምነት የሚፈፀሙ ሲሆኑ፣ ከሥርዓቱ ውጭ የሚወጡ ክዋኔዎች ቢኖሩ እንኳ በማህበረሰቡ አባላት ዘንድ ተቃውሞ ወይም ውግዘት ይደርስባቸዋል፤ በመሆኑም ባህላዊ ሥርዓቶቹ ሲፈፀሙ የቡድኑን ስምምነት ባልጣሰ መልኩ መሆን ይኖርበታል። ይህን ሐሳብ በተመለከተ Kottak ባህላዊ ስርዓቶች የሚዋቀሩበት ቅርፅ ማህበረሰባዊ ስምምነት ያለው ነው በማለት ይገልፃሉ (2002:95)።

ባህላዊ ስርዓቶች መንፈሳዊ (Sacred) እና አለማዊ (Secular) ተብለው ይከፈላሉ። መንፈሳዊ ስርዓቶች ከእያንዳንዱ የቡድኑ አባላት እምነት ጋር የጠበቀ ግንኙነት ያላቸው

ሲሆን፣ የቡድኑ መንፈሳዊ ወይም ልዕለ ተፈጥሯዊ አለማቱ (Super Natural World) እና ክስተቶች ጋር የጠበቀ ትስስር ያላቸው ናቸው። አከዋወናቸውም በጥቂት የማህበረሰቡ አባላት፣ በቤተሰብ ወይም በግለሰብ ደረጃ ሲሆን፣ አንዳንዴም አባላቱ በምስጢር ሊፈፅሟቸው ይችላሉ (Sims,2005:103)

አለማዊ ባህላዊ ሥርዓቶች ከመንፈሳዊ እምነቶች ጋር በግልፅ የተሳሰሩ አይደሉም። ሆኖም ትኩረታቸው የማህበረሰቡን የሕይወት መመሪያ በማስተማር ወይም በመቅረፅ ረገድ ይጠቅማሉ። በብዙ ባህላዊ ሥርዓቶች ውስጥ መንፈሳዊውም ሆነ አለማዊው በጥምረት ሲቀርቡ ይታያሉ። ከዚህ ላይ የሰርግና የቀብር ስርዓቶችን ለአብነት ማቅረብ ይቻላል (Sims,2005:104)።

ባህላዊ ሥርዓቶች የተለየ አቀራረብን (Stylized)፣ አውዳዊ አገባብንና ጥልቅ የሆኑ ተምሳሌታዊ ክንውኖችን አዋህደው የያዙ ናቸው። ከዚህም በተጨማሪ የስነቃል ዘውግ በሆኑ /በዜማ፣ በመነባንብ፣ በግጥም ወይም በዘፈን/፣ ማህበራዊ ልማድ በሆኑ /በአካላዊ እንቅስቃሴዎች (gestures)፣ በዳንስ ወይም በውዝዋዜ/፣ ቁሳዊ ባህል በሆኑ /በባህላዊ የምግብ አዘገጃጀት፣ በመጻሕፍት፣ በሽልማቶች፣ በባህላዊ አልባሳት/ በጥምረት ሊቀርብ ይችላል (Sims,2005:96)።

በአንዳንድ ባህላዊ ሥርዓቶች የቡድኑ ወይም የማህበረሰቡ መሪዎች ልብስ (attire) ከተራው አባል ወይም ከሥርዓቱ ተሳታፊዎቹ የተለየ ሊሆን ይችላል፤ ሆኖም በሥርዓቱ ውስጥ ተሳትፎ ያለው እያንዳንዱ ሰው ሥርዓቱ የሚፈቅደው አለባበስና አጊያጊያጥ ይኖረዋል። ይህ በአልባሳት ተለያይቶ መቅረቡ በቡድኑ ውስጥ ማን ምን እንደሆነ ለመለየት ያስችላል፤ ይኸውም የቡድኑ መሪ፣ ተከታዮቹን (novice) እና ተመልካቹን ነጣጥሎ ለማወቅ ይረዳል ማለት ነው።

በሌላ መልኩ ባህላዊ ሥርዓቶች በሚከበሩበት ወቅት የቡድኑ አባላት ከሚፈፅሟቸው ተግባራት በመነሳት አባላቱ በብድኑ ውስጥ ያላቸውን ቦታ መለየት ይቻላል።

በባህላዊ ሥርዓቶች የሚቀርቡ ክዋኔዎችና አጊያጊያጦች በሂደት ሌላ መልክ ሊይዙ ወይም ሊቀየሩ የሚችሉበት አጋጣሚ የሚከሰትበት ሁኔታ ይኖራል፤ በሌላ በኩል ደግሞ የቡድኑ አባላት ተጨማሪ ሥርዓቶችን በመፍጠር ወይም ከአጎራባች በመዋስ የነባሩ ስርዓት አካል ሊያደርጉ ይችላሉ (Sims,2005:100)።

በአጠቃላይ ባህላዊ ሥርዓቶች የአንድን ቡድን ባህል ትርጉም ባለው መልኩ ተጠናክሮ እንዲቀጥል በማድረግ በኩል ከፍተኛ እገዛ ያደርጋሉ። በመሆኑም በዚህ ጥናትም የተጠኘ ማህበረሰቡን ባህላዊ ስርዓት በመመርመር የሚኖረውን ማህበራዊ ፋይዳ ማሳየት ይሆናል።

### 3.1.3. ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ (Functional Approach)

በነገደ ወይጦ ማህበረሰብ ቃላዊ ዝርው ተረኮችና ባህላዊ ሥርዓቶች ላይ ትኩረቱን ያደረገው ይህ ጥናት የተመሰረተበት የምርምር ቴዎሪ ተግባራዊ (Functional) ንድፈ ሐሳብ ይሆናል።

ንድፈ ሐሳቡ የአንድን ማህበረሰብ ስነቃልና ባህላዊ ሥርዓት ፋይዳ ወይም አገልግሎት ለመተንተን የሚያስችል ነው፤ በመሆኑም በዚህ ንድፈ ሐሳብ አማካይነት ለጥናቱ የተመረጠው ማህበረሰብ ተረኮቹን ለምን ተግባር ያውላቸዋል? ባህላዊ ሥርዓቶቹንስ ለምን ይከውናቸዋል? ተረኮቹና ባህላዊ ሥርዓቶቹ ለማህበረሰቡ አባላት ምን ፋይዳ አላቸው? ተረኮቻቸውንና ባህላዊ ሥርዓቶቻቸውን ለአዲሱ ትውልድ የሚያስተላለፉበት ምክንያት ምንድነው? ለሚሉ ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት ይሞክራል።

ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ የአንድን ቡድን ወይም ማህበረሰብ ቃላዊና ልማዳዊ ሀብቶቹን በመመርመር ተግባራቸውን የሚያሳይ እንደሆነ ይናገራሉ (Sims,2005:175)። በሌላ መልኩ Oring የዘርፉ ምሁራን ፎክሎር ለፈጠረውና ለሚገለገልበት ማህበረሰብ ምን ትርጉም ይሰጠዋል? ወይም ምን መልዕክት ያስተላልፍለታል? የሚለውን ጥያቄ በማንሳት ዘርፉ በአንድ ማህበረሰብ ወይም ቡድን ውስጥ ያለውን ተግባር ለማወቅ ይመረምራል (1986:68) በማለት ይናገራሉ።

ከእነዚህ የመስኩ ተመራማሪዎች በሰፋ መልኩ የፎክሎርን ተግባር የመረመሩት የፎክሎር ተግባራዊ ጥናት ቀዳሚ አቀንቃኝ የሆኑት William R. Bascom ሲሆኑ፣ Bascom ፎክሎር አራት አበይት ተግባራት እንዳሉት ይገልፃሉ፤ እነዚህም የማዝናናት ወይም የማስደሰት (Amusement)፣ የባህልን ጠቀሜታ መግለፅ (Validating Culture)፣ የማስተማር (Education) እና የመግታት ወይም የመቆጣጠር (Maintaining Conformity to the accepted Patterns of behavior) ናቸው (1954:343-346) በማለት ይገልፃሉ።

እንደ Bascom አገላለፅ ፎክሎር ለየትኛውም ቡድን በተለይ ደግሞ የፅሁፍ ቋንቋ ባልዳበረበት ማህበረሰብ ዘንድ ጉልህ የማስተማር ድርሻ አለው። ፎክሎር ፈጣሪው ማህበረሰብ ልዩ ልዩ የስነቃል ቅርፃቹን በመጠቀም የታዳጊ ህፃናትን አእምሮ በትምህርት ለማጎልበት፣ ወጣቶችን በስነምግባር ለማነፅ በአጠቃላይ ለማህበረሰቡ መብቱን፣ እውነተኛ ታሪኩን፣ ባህሉንና የሕይወት መመሪያዎቹን ለማስረጽ ይጠቀምበታል (1954:344-345)።

በተመሳሳይ ፈቃደ ስነቃሎች የአበላል፣ የአጠጣጥ፣ የአለባበስ፣ የአቀማመጥ፣ የአነጋገር፣ የአካሄድ ስርዓት ያሳውቃሉ። በህይወት ውስጥ የትጋትን፣ የለጋስነትን፣ የህብረትን ጥቅም አጥብቀው ይሰብካሉ በማለት ይገልፃል (1991:20)።

ፎክሎር የፈጣሪው ማህበረሰብ ወይም ቡድን እሴት ማስተማሪያ ሆኖ ከማገልገሉ በተጨማሪ ከማህበረሰቡ እምነትና አመለካከት ወይም ስምምነት (Social Convention) የሚያፈነግጡ ግለሰቦች ላይ ጫና ለማሳዳሪያነትና ለመቆጣጠሪያነት እንደሚያገለግል Bascom ይገልፃሉ፤ ለመቆጣጠርም ባህላዊ የፍትህ ተቋማት፣ እምነቶችና አመለካከቶች ትልቁን ድርሻ ይወስዳሉ ይላሉ (1954:346)። ፈቃደም ይህን ሐሳብ በማፅናት ፎክሎር በተለይ ስነቃል ለፈጠረው ማህበረሰብ ምስጉን እና ድንቅ ከሚላቸው እሴቶቹ የሚያፈነግጡትን ወይም ለማፈንገጥ ዳር ዳር የሚሉትን ወደ ብዙሃኑ አስተሳሰብ በመመለስ በኩል ድርሻ እንዳለው ይናገራል (1991፡20)።

በሌላ መልኩ ፎክሎር የአንድ ማህበረሰብ ወይም ቡድን አባል ባህሉ ወይም ልማዱ ከጫነበት ደንብ፣ እንዲንቀሳቀስበት ከወሰነበት መልክዐምድራዊ ክልል (Geographical Environment) እና ሰብአዊ ተፈጥሮው ከሚፈቅድለት ወሰን (Biological Limitation) የሚያመልጥበት ወይም የሚያፈነግጥበት መንገድ ነው (Bascom,1954:343) በማለት ይገልፃሉ።

የሰው ልጅ የሚኖርበት ማህበረሰብ ባህል ወይም ልማድ አጥር ሆኖ አላንቀሳቅሰው ሲል፣ ድግግሞሽ የበዛበት ሕይወቱ እርካታ አልሰጠው በሚልበት ጊዜ በፎክሎር አማካይነት ወደ ፈለገው አለም መግባትን ይወዳል። ይህን በተመለከተ ፈቃደ ከአሰልችና ከተደጋጋሚ የህይወት ክስተቶች ሸሽቶ በምናቡ አዲስ አለም መግባት እንደሚሻ ይጠቅሳል (1991፡18)።

ፎክሎር ከማስተማር፣ ከማዝናናት፣ ከመቆጣጠርና ከመግታት ተግባሩ በተጨማሪ የተፈጠረበትን ማህበረሰብ ወይም ቡድን ባህላዊ እሴቶች ተገቢነት፣ ትክክለኛነትና ጠቀሜታ ከፍ የማድረግ ወይም የማረጋገጥ ተልዕኮ አለው። ይህን በተመለከተ Bascom ፎክሎር የተራኪውን ወይም የአድማጩን ማህበረሰብ ባህል ጠቃሚነት የመግለፅ፣ የተቋማቱንና የባህላዊ ስርዓቶቹን ተገቢነት የማረጋገጥ ተግባርን ይጫወታል (1954፡344)። ፎክሎር የማህበረሰቡን ባህል ትክክለኛነት የማረጋገጥ ተግባር እንደሚጫወት እነ Sims የቡድኑ ድርጊቶችና ሁነቶች በማህበረሰቡ ሕይወት ውስጥ ቦታ እንዲኖራቸው በማድረግ ባህሉን የማረጋገጥ ተግባር ይፈፅማል (2005፡176) በማለት ይገልፃሉ።

በተመሳሳይ Dorson (1972፡22) የአንድ ቡድን ፎክሎር በተለይ በሐተታ ተፈጥሮ አማካይነት እምነቶችን፣ ባህሉችንና ሥርዓቶችን የማፅናት ተግባር አለው ይላሉ። ፊታደም ይህን ሐሳብ በመደገፍ የቡድኑን አባላት በስነቃል አማካይነት ከልደት እስከ ሞት የሚያከናውናቸውን ድርጊቶች አስፈላጊነትና ተገቢነት እያሳመኑ ከንዋኔዎቹ እንዳይከስሙ፣ ቀጣይነት እንዲኖራቸው ያደርጋሉ (1991፡18) ይላል።

### 3.2. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ክፍል የሚዳሰሱት የጥናት ስራዎች የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ፅሁፎች ብቻ ሲሆኑ፣ ይህም የሆነበት ምክንያት የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ፅሁፎች ቁጥራቸው በርካታ በመሆኑ ነው። በጥናቱ አስራ ሦስት ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረቡ ጽሑፎች ተቃኝተዋል። ጥናቶቹም በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በኢትዮጵያ ስነጽሑፍ እና ፎክሎር፣ በውጭ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ፣ በታሪክ እና በሶሻል አንትሮፖሎጂ የትምህርት ክፍሎች የተሰሩ ናቸው። ከጥናቶቹ መካከል ሦስቱ በነገደ ወይጦ ማህበረሰብ ላይ በመመስረታቸው ከዚህ ጥናት ጋር የሚመሳሰሉ ሲሆን፣ ቀሪዎቹ አስር የጥናት ጽሑፎች ደግሞ ትኩረታቸውን በቃላዊ ዝርው ተረኮች ላይ በማድረጋቸው ከዚህ ጥናት ጋር ተዛምዶ አላቸው። ጥናቶቹም በሦስት ንዑስ ርዕሶች ተከፋፍለው የቀረቡ ሲሆን፣ በእያንዳንዱ ንዑስ ርዕስ የሚቀርቡት ጥናቶች በተጠኑበት ዘመን ቅደም ተከተል መሠረት ይሆናል።

### 3.2.1. በነገደ ወይጦ ማህበረሰብ ላይ በመመስረት የተሰሩ

ተክለሃይማኖት ገብረሥላሴ (1984) "The Wayto of Lake Tana: An Ethino-History" በሚል ርዕስ በታሪክ የትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ ያቀረበ ሲሆን፣ የጥናቱ ዓላማ የወይጦ ማህበረሰብን ኬትመጣ /Origin/ መመርመር እንደሆነ ጠቅሷል፡፡ አጥኚው በጥናቱ ከ17ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ስለወይጦ ማህበረሰብ ኬትመጣ የቀረቡትን የጽሁፍ መረጃዎች ቢያይም፣ የማህበረሰቡን ቋንቋና ሃይማኖት በተመለከተ የቃልም ሆነ የፅሁፍ መረጃ አለማግኘቱን ገልጿል፡፡

ተክለሃይማኖት ከጥናቱ በመነሳት ወይጦ የአገው ነገድ አንዱ ክፍል ሊሆን እንደሚችል ግምቱን ሲገልፅ፣ የወይጦ ማህበረሰብ ከሌሎች የአካባቢው ሕዝቦች ጋር ያላቸውን ባህላዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ግንኙነቶች እና በማህበረሰቡ ላይ ያለው መገለልን ለማሳየት ሞክሯል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ወይጦዎች ጉማሬ እያደኑ በመመገብ ለረጅም ዘመን መኖራቸውን እና አመጋገባቸው ከአካባቢው ማህበረሰብ በመለየቱ ምክንያት ተገልለው መኖራቸውን ጠቅሷል፡፡

አየለ ፍቅሬ (1998) "ባህላዊ የግጭት ዘዴ በባህር ዳር ነገዴ (ወይጦ) ኅብረተሰብ" በሚል ርዕስ በኢትዮጵያ ስነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያቀረበ ሲሆን፣ የጥናቱ ዓላማ በባህር ዳር ከተማ ውስጥ የሚኖሩ ነገዴዎች እርስ በርስ እና ከሌሎች ነዋሪዎች ጋር የሚፈጠረውን ግጭት በባህላዊ መንገድ እንዴት እንደሚፈቱ እና ፎክሎር በነገዴ ኅብረተሰብ ውስጥ ለባህላዊ የግጭት አፈታት ያለውን አስተዋጽኦ ማሳየት ነው፡፡ አጥኚው በስራው የነገዴዎች (ወይጦዎች) ኬትመጣቸውን ለመጥቀስ የሞከረ ሲሆን፣ ማህበረሰቡ እስልምናን ከመቀበላቸው አስቀድሞ በነጋድራስ ሥርዓት ሲተዳደሩ መቆየታቸውን እና በኋላ ግን በአባጋር መተካቱን፣ በነገዴዎች የነፍስ ግድያ ግጭት ሲፈጠር አባጋሩ ሽማግሌዎችን ሰብስቦ ስፊ ድርድር ካደረገ በኋላ የደም ካሳ ተከፍሎ ባለደሞቹ የሚታረቁ መሆኑን ጠቅሷል፡፡ በነገዴ (ወይጦ) ማህበረሰብ ሽማግሌዎችን ማክበር፣ ለቃላቸውም መገዛት፣ እርግማን መፍራት፣ መረዳዳት፣ ጥቃትን በኅብረት መመከት፣ ማንኛውንም አለመግባባት በድርድር መፍታት አበይት የአኗኗር ዘይቤያቸው መሆኑን ገልጿል፡፡

መላክ ምህረት (2010) "A Study of the Socio-Cultural and Economic Marginalization of the Wayto in and around Bahir Dar, Northwestern Ethiopia" በሚል ርዕስ በሶሻል አንትሮፖሎጂ ክፍለ ትምህርት ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያቀረበ ሲሆን፣ የጥናቱ ዓላማ በባህር ዳር ከተማና በዙሪያዋ የሚኖሩት የወይጦ ማህበረሰብ በማህበራዊ፣ በባህላዊና በኢኮኖሚያዊ ሁኔታ በሌላው ማህበረሰብ ዘንድ እየደረሰባቸው ያለውን መገለል (Marginalization) መመርመርና ከአካባቢው ሕዝብ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ምን እንደሚመስል ማሳየት እንደሆነ ጠቅሷል።

መላክ በጥናቱ የወይጦ ማህበረሰብ ኬትመጣ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ባህላዊ ሁኔታዎችን የተመለከተ ሲሆን፣ ለጥናቱ የተመረጠው ማህበረሰብ በአካባቢው ሕዝብ ዘንድ በሁሉም ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያውና ባህላዊ ጉዳዮች የተገለለና በኢኮኖሚም በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ እንደሆነ ማረጋገጡን ገልጿል።

ከላይ የቀረቡት ሦስት ጥናቶች በነገደ ወይጦ ማህበረሰብ ላይ ትኩረት አድርገው የተሰሩ ቢሆንም፣ ተክለ ሃይማኖት በማህበረሰቡ ታሪክ፣ አየለ በግጭት አፈታታቸው ላይ፣ መላክ በአካባቢው ማህበረሰብ እንዴት እንደተገለሉ ያጠኑ በመሆናቸው ከዚህ ጥናት ጋር ይለያያሉ፤ ምክንያቱም የዚህ ጥናት ትኩረት የማህበረሰቡን ቃላዊ ዝርው ተረኮችና ባህላዊ ሥርዓቶች ለማህበረሰቡ ያላቸው ማህበራዊ ፋይዳ ላይ ያተኮረ በመሆኑ ነው።

### 3.2.2. በየማህበረሰቡ ማህበራዊና ባህላዊ ፋይዳ ላይ የተጠኑ

አብዱልቃድር ሐጂ (1982) "Some Cultural Elements as Reflected in Somali Folktales" በሚል ርዕስ ለውጭ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያቀረበ ሲሆን፣ የጥናቱ ዓላማ በተረቶቹ ላይ በመመስረት የሶማሌን ማህበረሰብ ባህላዊና ስነልቦናዊ ገፅታዎችን ማሳየት የሚል ነው። አጥኚው በፅሁፉ ስማንያ ሁለት ተረቶችን ካላቸው ጭብጥ አንፃር በስምንት ክፍል መድቦ ለማሳየት ሞክሯል፤ የተረቶቹ ይዘትም ብልህነትን ወይም ጥበበኝነትን፣ ፍትህን፣ ሃይማኖትንና ሥነምግባርን፣ ጋብቻን፣ ሴቶችንና ቅናትን የሚያመላክቱ እንደሆነ ጠቅሷል። አብዱልቃድር ለጥናቱ በተመረጡት ተረቶች አማካይነት የሶማሌን ማህበረሰብ ባህላዊና ስነልቦናዊ ገፅታዎች ለማሳየት ቢሞክርም፣ ለጥናቱ የሚያስፈልጉትን መረጃዎች የሰበሰበበት ቦታ ጅጅጋ የስደተኞች ካምፕ (1982:23) ውስጥ ብቻ በመሆኑ፣ በአንድ ካምፕ የተሰበሰቡ

መረጃዎች ሁሉንም የሶማሌ አካባቢዎችና ጎሳዎች በሚያሳይ መልኩ ቀርቧል ለማለት የሚያስደፍር አይመስልም።

ተስፋዬ ገብረማርያም (1990) "A Study of Major Themes in Jabalwi Folktales" በሚል ርዕስ ለውጭ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያቀረበ ሲሆን፣ የጥናቱ ዓላማ ለጥናቱ የተመረጡትን ተረቶች ጭብጥ በመተንተን የማህበረሰቡን እምነት፣ ማህበራዊ እሴት እና ለአለም ያላቸውን አመለካከት ማሳየት የሚል ነው። አጥኚው በጥናቱ ሰባ ሁለት ተረቶችን ወስዶ በሃያ አምስት ጭብጦች ለመመደብ ሞክሯል፤ ጭብጦቹም ብቀላን፣ ቅናትን፣ ስስታምነትን፣ ምቀኝነትን፣ ሞኝነትን፣ ደደብነትን፣ ስንፍናን፣ ትዕግስትን፣ ጨካኝነትን፣ አንድነትን፣ ፍትህን እና እውነትን በሚሉት ርዕስ ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ እንደሆኑ ለማሳየት ሞክሯል። ተስፋዬ ለጥናቱ ከመረጃ አቀባዮች ፈቃድ ውጭ መረጃ ለመሰብሰብ መሞከሩ (1990፡12) የሙያውን ስነምግባር የጣሰ ይመስላል።

መላክነህ መንግስቱ (1990) "The Major Themes and Motifs of Southern Agaw Folktales" በሚል ርዕስ ለውጭ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያቀረበ ሲሆን፣ የጥናቱ ዓላማ የደቡባዊ አገውን ሀገረሰባዊ ተረቶች በመሰብሰብ በጭብጥና በሞቲፍ ላይ የተመሰረተ ትንተና በማድረግ የተረቶቹን ስነፅሁፋዊና ማህበራዊ ጠቀሜታ መመርመር፣ ማህበራዊ፣ ባህላዊ ጠቀሜታ እና የህዝቡን ስነልቦናዊና ስነምግባራዊ አመለካከት ማሳየት የሚል እንደሆነ ገልጿል። አጥኚው በፅሁፉ ተረቶች ተደጋጋሚ ጭብጦች እንዳሏቸው የተመለከተ ሲሆን፣ የማህበረሰቡን መልካም እሴቶች ለማስተማር፣ የወጣቶችን ስብዕና በመልካም ስነምግባር ለመቅረፅ እንደሚያገለግሉ ገልጿል።

ከላይ የቀረቡት ሦስት የጥናት ሥራዎች ከዚህ ጥናት ጋር ትኩረታቸው በተረቶች ላይ በመሆኑ የተለዩ ቢሆኑም በአንድ የስነቃል ዘውግ ጭብጣዊ ወይም ይዘታዊ ትንታኔ (thematic analysis) ላይ ተመስርተው የየማህበረሰቡን ማህበራዊና ባህላዊ ፋይዳ ከመመርመር አንፃር ሲታዩ ተመሳሳይነት ይታይባቸዋል።

### 3.2.3. ቃላዊ ዝርው ተረኮችን በአውዳዊ አገባባቸውና በዘውግ በመመደብ ያጠኑ

ሳህሉ ኪዳኔ (1996) "Borana Oromo Prose Narratives: A Contextual Study" በሚል ርዕስ ለውጭ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያቀረበው ጥናት ዋና ዓላማው በተጠኚ ማህበረሰቡ ውስጥ የሰበሰባቸውን ተረቶች የሚገኙበትን ሁኔታ በመግለፅ አይነታቸውን (ethnic genres) ማሳየት እንደሆነ ጠቅሷል። ሳህሉ ለጥናቱ የሰበሰባቸውን ሰባ አራት ተረቶች "ዱሪ ዱሪ" (የልጆች ተረቶች)፣ "ማማክሳ" (የጎልማሶች ተረቶች) እና "አርጋጌቲ" (ሚቶችና አፈታሪኮች) በማለት በሦስት ክፍሎ ለማሳየት ሞክሯል። እነዚህ ተረቶችም የማህበረሰቡን ጥበቦች፣ ህጎች፣ ባህሎች፣ ታሪኮችና ትውፊቶች እንደያዙ ገልጿል። አጥኚው ቃለመጠይቅ አይነተኛ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ መሆኑ እየታወቀ (Dorson,1972:407-425; Goldstein,1964:76) በጥናቱ ውስጥ መጠቀሙን አልገለፀም። የሳህሉ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚመሳሰለው በቃላዊ ዝርው ተረኮች ላይ በማተኮሩ ሲሆን፣ ልዩነቱ የእኔ ጥናት የነገደ ወይጦ ማህበረሰብን ቃላዊ ዝርው ተረኮችና ባህላዊ ስርዓቶች ማህበራዊ ፋይዳ ሲመረምር፣ የሳህሉ ግን በቦረና ኦሮሞ ቃላዊ ዝርው ተረኮች አውዳዊ አገባብና በዘውግ መመደብ ላይ መሆኑ ነው።

ይሄነው ጀምበር (1996) "A Generic Classification of Amharic Oral Prose Narratives of West Gojjam" በሚል ርዕስ ለውጭ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያቀረበ ሲሆን፣ የጥናቱ ዓላማ ለጥናቱ በተመረጠው አካባቢ የሚገኙትን ቃላዊ ዝርው ተረኮች መሰብሰብና መመደብ ነው። የአመዳደብ ስልቱ ለተረኮቹ ያላቸውን አመለካከት፣ የአተራረክ ዘዴያቸውን፣ የገፀባህሪያቱን አሳሳል መሰረት በማድረግ እንደሆነ ገልጿል። አጥኚው የሰበሰባቸውን አንድ መቶ ሰላሳ ስምንት ተረኮች ህገረሰባዊ ተረቶች፣ አፈታሪኮች እና ዘር ቆጠራዎች (genealogy) በማለት በሦስት ምድብ ከፍሏቸዋል። ህገረሰብ ተረቶች በየትኛውም የዕድሜ ክልል በሚገኙ የማህበረሰቡ አባላት የሚነገሩ ሲሆኑ፣ አፈታሪኮችና ዘር ቆጠራዎች ግን በእድሜ ባለፀጎች እንደሚቀርቡም ጠቅሷል። ይኼነው ተረኮቹን የባህል ባለቤቶቹን መንገድ ተከትሎ በዘውግ የመከፋፈል ተገቢነትን ቢገልፅም፣ ለጥናቱ የሰበሰባቸውን ተረኮች ግን አካዳሚያዊውን መንገድ ተከትሎ folktale, legend, genealogies በማለት ለመመደብ መሞከሩን ማየት ተችሏል። የይሄነው ጥናት ከእኔ ጥናት የሚለየው ቃላዊ ዝርው

ተረኮችን በየመደባቸው በመከፋፈል ላይ ብቻ ሲያተኩር ይህ ጥናት ግን ቃላዊ ዝርው ተረኮችንና ባህላዊ ስርዓቶችን ከይዘት አንጻር ማየቱ ላይ ነው።

ባይለየኝ ጣሰው (1999) "Anyuaa Oral Prose Narratives: Ethnic Genres and Social Functions" በሚል ርዕስ ለውጭ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት አቅርቧል። የጥናቱ ዓላማዎች የማህበረሰቡን ቃላዊ ዝርው ተረኮች የባህል ባለቤቶቹን የአመዳደብ ስርዓት እንደ ዋና የመከፋፈያ ስልት በመጠቀም ማሳየት እና ተረኮቹ ያላቸውን የጋራ ማህበራዊ ተግባር መመርመር እንደሆነ ጠቅሷል። ባይለየኝ ለጥናቱ አንድ መቶ አስራ ስምንት ቃላዊ ዝርው ተረኮችን የሰበሰበ ሲሆን "ሌሬ" (the leere)፣ "ዋኤ" (the wae) እና "አንጋዴ" (the angade) በማለት በሦስት ምድብ ከፍሏቸዋል። "ሌሬ" ስለሞቱ ጀግኖችና ስለታሪካዊ ክንውኖች፣ "ዋኤ" ልዩ ልዩ የሰው ባህሪያትን እና "አንጋዴ" ደግሞ ያለፉ ሁነቶችን፣ የእምነት ስርዓቶችን፣ ማህበረሰቡ ስለአለም ያላቸውን አመለካከት እንደሚያሳዩ ጠቅሷል። ይህ ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ትኩረቱን በቃላዊ ዝርው ተረኮችና በማህበራዊ ፋይዳቸው ላይ በማድረጉ ሲሆን፣ የእኔ ጥናት ባህላዊ ስርዓቶችን በማየቱና የቃላዊ ዝርው ተረኮችን አካባቢያዊ አመዳደብ ባለመመልከቱ የተለየ ያደርገዋል።

አብርሃም አለሙ (2000) "Jimma Oromo Oral Prose Narrative: A Preliminary Descriptive Analysis" በሚል ርዕስ ለውጭ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ ያቀረበ ሲሆን፣ የጥናቱ ዓላማዎች ማህበራዊና ባህላዊ እውዶችን መሰረት በማድረግ የተጠኝ ማህበረሰብ ተረቶችን መለየትና መበየን፣ በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው ቃላዊ ዝርው ተረኮች የትኞቹ እንደሆኑ ማሳየት፣ ተጠኝ ማህበረሰቡ ተረቶችን እንዴት እንደሚመድቧቸው መመርመር፣ የተረቶቹን ውስጣዊ ባህርያት፣ አጀማመርና አጨራረሱን ማውጣት፣ ተረቶቹ የሚከወኑባቸውን አጋጣሚዎችና ሁኔታዎች መለየት የሚሉ ሲሆኑ፣ ተረኮቹን "ሴና" (seenaa Taarika)፣ "ኦዱ ዱሪ" (oduu duri)፣ እና "ቆሳ" (qoosaa) በማለት በሦስት መድቧቸዋል። አጥኚው ተረኮቹ ማህበረሰቡ የሚለያቸው በስማቸው፣ በውስጣቸው ባለው ነባራዊ እውነትና ፈጠራ፣ እንዲሁም በትረካው ዓላማ መሆኑን ጠቅሷል። የአብርሃም ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር ተመሳሳይነቱ ቃላዊ ዝርው ተረኮችን ለጥናቱ መነሻ ማድረጉ ሲሆን፣ ልዩነቱ ግን በተለይ የእኔ ጥናት ትኩረቱ ቃላዊ ዝርው ተረኮቹና ባህላዊ

ስርዓቶቹ ባላቸው ማህበራዊ ፋይዳ ላይ በመሆኑ የአብርሃም ጥናት ግን ተረቶችን በማህበራዊና ባህላዊ አውዶች መለየቱ ላይ በዋናነት ማተኮሩ ነው።

ማንያለው አባተ (1999) "የቤንች ቃላዊ ዝርው ተረክ ዘሮችና ማህበራዊ ፋይዳቸው" በሚል ርዕስ በኢትዮጵያ ስነፅሁፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያቀረበ ሲሆን፣ የጥናቱ ዓላማ በቤንች ቃላዊ ዝርው ተረኮች ማህበራዊ ፋይዳ ላይ ገላጭ ትንተና ማድረግና የቤንች ብሔረሰብ አባላት የቃላዊ ዝርው ተረክ ዘሮች ናቸው ብለው የሚጠቅሷቸውን ለይቶ መግለፅ እንደሆነ ጠቅሷል።

አጥኚው በስራው የቤንች ዝርው ተረኮች ክክወና አውዳቸው (ጊዜ)፣ ከፈጠራነታቸው፣ ከታሪኩ እውነተኛነትና ከትረካው ግብ ዓላማ አንፃር ቤንችቶስ እና ኤሸሽ ተብለው እንደሚከፈሉ ገልፆ፤ ቤንችቶስ የሚተረከው በቀን ሆኖ በአካባቢው የተነሱትን ቃላዊ (ታሪካዊ) ሰዎችን የሚመለከቱ አፈታሪኮችና የብሄረሰቡን ባህላዊ እምነት፣ የአምልኮ ስርዓትና አሰራሮችን የሚመለከት ሲሆን፣ ኤሸሽ ደግሞ ተረኩ የፈጠራ ሆኖ ክወናውም በምሽት ጊዜ በአዋቂዎች አማካይነት ለሕፃናት የሚቀርብ እንደሆነ ለማሳየት ሞክሯል። ይህ ጥናት የቃላዊ ዝርው ተረኮችን ማህበራዊ ፋይዳ በመመልከት ከእኔ ጥናት ጋር ተመሳሳይነት አለው፤ ሆኖም የእኔ ጥናት ባህላዊ ስርዓቶችን ማየቱና የማንያለው ደግሞ የተረኮችን አካባቢያዊ አመዳደብ በማየቱ ልዩነት ይታይባቸዋል።

አማረ ሞላ (1999) "የሸካቾ ብሄረሰብ ሀገረሰብ ተረቶች ምደባ የአከዋወን ስልትና የይዘት ትንተና" በሚል ርዕስ በኢትዮጵያ ስነፅሁፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያቀረበ ሲሆን፣ የጥናቱ ዓላማ የሸከቾን ብሄረሰብ ሀገረሰባዊ ተረቶችን በመሰብሰብ መድቦ ከአከዋወን ስልትና ከይዘት አንፃር መተንተንና ተረቶቹን ለንዶ ለመጭው ትውልድ ቅርስ ማቆየት በሚል ጠቅሷል። አጥኚው ተረቶቹን ቀያዊ (አካባቢያዊ) ምደባን ተከትሎ የመደበ ሲሆን፣ ከይዘትም አንፃር ተረቶቹ ብልህነትን፣ መጥፎ ባህሪያትን፣ ፍትሀዊነትን፣ ጓደኝነትን፣ ትዕግስትን እና ጣውንትነትን እንደሚያሳዩ ገልጿል። የዚህ ጥናት ትኩረቱ በተረቶች ላይ መሆኑ፣ አከዋወናቸውን ማየቱና ተረቶችን በአካባቢያዊ ምድባቸው መለየቱ ከእኔ ጥናት የተለየ ሲያደርገው የይዘት ትንተና በማድረጉ ግን ከእኔ ጥናት ጋር ተመሳሳይ ያደርገዋል።

ምንዳ ገብሬ (2000) "የጌዴኦ ልማዳዊ ስርዓቶችና ዝርው ቃል ተረኮቻቸው" በሚል ርዕስ በኢትዮጵያ ስነፅሁፍ እና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያቀረበ ሲሆን፣ የጥናቱ ዓላማዎች በማህበረሰቡ ልማዳዊ ስርዓትና ዝርው ቃላዊ ተረኮቻቸው ውስጥ ምን ምን ግንኙነቶች እንዳሉ መመርመር፣ የዝርው ቃል ተረኮቹን ከማህበራዊ ግልጋሎቶች አንፃር ይዘቶቻቸው በምን ላይ እንደሚያተኩሩ ማሳየት፣ የተረኮቹን ጎሳዊ ምደባና አካባቢያዊ ስያሜዎቻቸውን መለየት የሚሉ እንደሆኑ ገልጿል። በጥናቱ ዝርው ቃል ተረኮቹን ጢንን እና መማን በማለት በሁለት ክፍሎ አንድነትና ልዩነታቸውን የተመለከተ ሲሆን፣ የጌዴኦ ዝርው ተረኮች ይዘታቸው ሲመረመር የህብረተሰቡን ልማዳዊ ስርዓቶች (እሴቶች) ለማጠናከርና ቀጣይነት እንዲኖራቸው በማድረግ ረገድ እንደሚያገለግሉ ጠቅሷል። የምንዳ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚመሳሰለው ልማዳዊ ስርዓቶችንና ቃላዊ ዝርው ተረኮችን የተመለከተ በመሆኑ ሲሆን፣ ምንዳ ቃላዊ ዝርው ተረኮቹን ጎሳዊ የአመዳደብ ስልትን ተከትሎ መክፈሉ ከእኔ ጥናት የተለየ ያደርገዋል።

## ምዕራፍ አራት

## ከነገደ ወይጦ ማህበረሰብ ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ቃላዊ ዝርው ተረኮች ትንተና

በዚህ ክፍል ውስጥ የተለያዩ ቃላዊ ዝርው ተረኮች ትንታኔ ይሰጥባቸዋል፤ እነዚህ ቃላዊ ዝርው ተረኮች ከነገደ ወይጦ ማህበረሰብ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ናቸው፡፡ ትንተናውም ትኩረት የሚያደርገው ቃላዊ ዝርው ተረኮቹ ለማህበረሰቡ ያላቸውን ማህበራዊ ፋይዳ መመርመር ላይ ይሆናል፡፡ በዚህ መሰረት ከማህበረሰቡ አባላት የተሰበሰቡትን ቃላዊ ዝርው ተረኮች ከማህበረሰቡ ስያሜ፣ አመጣጥ፣ አሰፋፈር፣ አምልኮ፣ የስራ ባህልና ከውሃ ጋር ካላቸው ትስስር አንፃር ከፋፍሎ ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ ቃላዊ ዝርው ተረኮቹን በአካባቢያዊ ምደባ ለመክፈል ያልተቻለው ማህበረሰቡ ለቃላዊ ዝርው ተረኮቹ የሚሰጠው ስያሜ ባለመኖሩ ነው፡፡

### 4.1. ከነገደ ወይጦ ማህበረሰብ ስያሜ ጋር የተያያዙ ተረኮች

በአለም ላይ ያለ ማህበረሰብ ሁሉ በጎሳው፣ በቋንቋውና በባህሉ ስም ይሰየማል (ብርሃኑ፣2001፡8)[3]፡፡ የነገደ ወይጦ አባላትም የነገዱን (የጎሳውን) ስያሜ ሲጠየቁ ከቆየው የማበረሰቡ አባላት በሽግግር የመጣ ነው ብለው የሚያምኑበትንና የአካባቢው ማህበረሰብ ይሉናል የሚሏቸውን ተረኮች በመንተራስ የስያሜ መነሻዎችን ያቀርባሉ፡፡

#### 4.1.1. ከአመጋገብ ስርዓት አንፃር የተሰጠ ስያሜ

ከአመጋገብ ስርዓት አንፃር የተሰጠው ስያሜ መነሻ የሆነው አባላቱ የሚከተሉት የአመጋገብ ስርዓት ከአካባቢው ማህበረሰብ የተለየ በመሆኑ እንደሆነ ይነገራል፡፡ ይህን በተመለከተ ዮሀንስ፣

> ነገደ ዮቅጣን ወይም ነገደ አግዓዚያን ወደ ኢትዮጵያ በገቡ ጊዜ ከሌላው ህዝብ ተለይተው በአምልኮ የማይቀላቀሉ፣ ያገኙትንም እንስሳ ርኩስና ቅዱስ ሳይለዩ ሁሉን የሚበሉ እንደሆኑ አይተው 'እኒህ ምን አይነት ህዝብ ናቸው?' ብለው

---

[3] በዚህ ጥናት የተጠቀሱ የሀገር ውስጥ አጥኚዎችና የመረጃ ምንጮች ለአገላለፅ እንዲያመች ሲባል በነጠላ ቁጥር ቀርበዋል፡፡

ጠየቁ። ዋቶ ይባላሉ ያገኙትንም ሁሉ ይበላሉ አሏቸው። ነገደ አግዓዝያንም የእኒህስ ስማቸው ዋቶ አይደለም ያገኙትን ሁሉ የሚበሉ የማይጸየፉ ናቸውና ስማቸው ዉሂጦ ነው አሉ፤ ስለዚህም በዚያ ዘመን ዉሂጦ ተባሉ ዉሂጦ ዋጭ ማለት ነው። ከዘመን ብዛት ግን እያደረ ዉሂጦ ተለውጦ ወይጦ ተባለ ይላሉ (1940፡108)።

በማለት ወይጦ የሚለው የነገድ ስያሜ እንዴት እንደተጀመረ ይናገራል።

በዚህ ተረክ መነሻነት እንደተሰጠ የሚታመንበት ይህ ስያሜ ለማህበረሰቡ መጠሪያ ሆኖ ከማገልገሉ በተጨማሪ የስያሜ መነሻ ምክንያቱ የማህበረሰቡን የአመጋገብ ስርዓት የተለየ ወይም በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ እንደ "ርኩስ" የሚቆጠሩትን የሚበሉ ከመሆኑ የመነጨ ስለሆነ ስያሜው ማህበረሰቡን ዝቅ አድርጎ ለማሳየት ወይም ለማጥላላት የሚጠቀም ነው ማለት ይቻላል። የአማራ ክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ይህንን ሀሳብ በማጽናት "ከአካባቢያቸው ማህበረሰብ በተለየ ሁኔታ ያልተባረከ ወይም በተፈጥሮና በሌሎች አጋጣሚ የሞተና የተለያዩ የባህር እንስሳት የመመገብ ልምዳቸው በሚኖሩበት ሕብረተሰብ ለመገለላቸው አንዱና አብዩ ምክንያት እንደሆነ ይታመናል" (2001:36) በማለት የማህበረሰቡ አባላት የተለየ የአመጋገብ ባህል በመከተላቸው ምክንያት ተገልለው እንደሚኖሩ ይገልፃል። በሌላ መልኩ የዚህ ስያሜ መነሻ እንደሆነ የሚታመንበት ተረክ የተነገረው የማህበረሰቡ አባላት የአካባቢው ማህበረሰብ "ርኩስ" ነው ብሎ አውግዞ ከተወው የአመጋገብ ስርዓት ወጥተው ብዙሀኑን እንዲመስሉ ለማድረግ የተጠቀሙበት ይመስላል።

ከአመጋገብ ስርዓታቸው በመነሳት "ወይጦ" የሚለው ስያሜ መምጣቱን ከላይ ከተገለጸው ተረክ በተለየ መልኩ የሚያቀርቡም አሉ። በቅድሚያ በተረክ አራት ቸርነት ስያሜውን በመጽሀፍ ቅዱስ ከተጠቀሱት ከኢሳውና ያዕቆብ ታሪክ ጋር ለማስተሳሰር ይሞክራል። ሁለቱ ወንድማማቾች በአንድ ወቅት በደረሰ የርሃብ ዘመን ጉማሬ ገድለው ለመመገብ ወሰኑ። የጉማሬውንም ስጋ በካራ (ቢላዋ) ከቆራረጡ በኋላ "በል አንተ ቅመሳት በል አንተ ቅመሳት" በመባባል ላይ እያሉ የነገደ ወይጦ አባት የሆነው ተቻኩሎ የጉማሬውን ስጋ በላ። በዚህን ጊዜ ገና መብላት ያልጀመረው ወንድሙ ያዕቆብ "ኧረ ዋጠው" አለው። ይህም በሂደት ወይጦ በሚለው ተለውጦ ለማህበረሰቡ መጠሪያ ሊሆን እንደቻለ ይናገራል (ካሴት ቁጥር 3(ሀ)፣ ሚያዝያ 30 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)።

ምንም እንኳ ከላይ የተጠቀሰው ተረክ በመጽሀፍ ቅዱስ ከተጠቀሰው የኢሳውና የያዕቆብ ታሪክ ጋር የማይገናኝ ቢሆንም፣ ዔሳው በራበው ወቅት በእንጀራና በምስር ወጥ ለያዕቆብ ብኩርናውን የሸጠ (ዘፍ.27፣32-34) በመሆኑ ክብር የሌለው ሰው እንደሆነ ይቆጠራል። በዚህ ተረክም ኢሳው የወይጦዎች አባት ሆኖ መሰየሙና በብሉይ ዘመን እንደ ርኩስ የሚቆጠረውን ወይም ሸኮና ድፍን የሆነውን የጉማሬ ስጋ ቀድሞ እንዲበላ መደረጉ የማህበረሰቡ ስረ መሰረት ክብር የሌለው እንደሆነ እና ርኩሱንና ቅዱሱን ለይቶ የማይመገብና ለመብላት የሚቸኩል እንደሆነ ለማሳየት የተነገረ ይመስላል።

ሌላው ከዚህ ስያሜ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ተረክ በፈርኦንና በነብዩ ሙሴ ዘመን ተፈፀመ ተብሎ ከሚታመንበት አንድ ክስተት ጋር ይገናኛል ተብሎ የሚታመንበት ነው።

> ፍራኦንና ነብይ ሞሳ ያው በውጊያ ሲለያዩ ነብይ ሞሳ ፍራኦን ወደ ባህሩ ሲሰምጥ በዘንገ ሲመቷት ሰመጠ ይላል እና ፍራኦን በዚያ ሲሰምጥ ነብይ ሞሳ ከነጭፍራቸው ጉዞ ቀጠሉ። አሁን ጉዟቸውን ሲኼዱ ይከተሏቸው የነበሩ የጦር አበጋዞች ጃሉትና ጧሉት የሚባል ነበራቸው እና ጃሉት አንድ የጦር አበጋዝ ነው። ጧሉት ደግሞ አንዱን የጦር አበጋዝ የሚመሩት ሁነው ተከፋፍለው ሲቀጥሉ አሁን የእኒህ ጎሳዎች የሚሏቸው ከጧሉት ጎሳ ጋር ነበሩና እዚያ ላይ እንዳሉ ምን ሰጡት ለጦር ተከታዮቻቸው ምን ሰጧቸው ትዛዝ አንዳንድ እፍኝ ውሃ ጠጡ ተዛ በላይ እንዳትጨምሩ የሚል ትዛዝ ሰጡ ይላል። አሁን ያን ሲሉ እንግዲህ ተሰብስበው ቁጭ እንዳሉ በጣም ጠማቸውና መጨመር አምጠዋል ሦስት አራት እፍኝ መጠጣት አምጠዋል ሲሉ ኧረ ጠጡ ኧረ ብዙ ውሃ ጠጡ እየጨመሩ ጠጡ ብለው በሚሰሙበት ጊዜ ዘወር ብለው ቢያዩ እየጠጡ አንተ ዋጠው ብለው በሚሉ ጊዜ ኧረ ወይጦ አላት ስም ተሰየመ ይላል ዋጠው በሚል ወይጦ በሚለው ተሰየመ (ሙሀመድ፣ ካሴት ቁጥር 6(ለ)፣ ግንቦት 6 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)።

በማለት "ወይጦ" የሚለውን የነገድ መጠሪያ መሰየሙን በተረክ ሰባት ይናገራል። በአጠቃላይ ከላይ የቀረቡት ሦስት ተረኮች ነገደ ወይጦ የተባለው ማህበረሰብ "ወይጦ" ተብሎ ለመሰየሙ መነሻ ምክንያት ተደርገው በአካባቢው ማህበረሰብ የተነገሩና ማህበረሰቡን ለማጥላላትና ለማግለል የሚጠቀሙባቸው ይመስላል፣ ሆኖም እነዚህ ተረኮች በተጠኝ ማህበረሰቡ አባላት ዘንድም ቦታ ተሰጥቷቸው ሲተረኩ ይሰማሉ። ይህ ምናልባት የአካባቢው ማህበረሰብ ከሳደረባቸው ተጽዕኖ የተነሳ እነርሱን ከፍ አድርጎ ከማየትና የሚናገሩትም እውነትነት ያለው እንደሆነ ከማመን የመነጨ ሊሆን ይችላል።

### 4.1.2. ከነገዱ ስም በመነሳት የተሰጠ ስያሜ

የአንድ ማህበረሰብ አባላት ስያሜ በነገዱ ስም ወይም የነገዱን አባት ሊጠራ ይችላል። በመጽሀፍ ቅዱስ በኦሪት ዘፍጥረት "እግዚአብሄር ለያቆብ ከሁለት ወንዞች መካከል ከሶሪያ ከተመለሰ በኋላ እንደገና ተገለጠለት፤ ባረከውም። እግዚአብሄርም፦ ስምህ ያዕቆብ ነው። ከእግዲህም ወዲህ ስምህ ያዕቆብ ተብሎ አይጠራ፤ ስምህ እስራኤል ይባል እንጂ አለ፤ ስሙንም እስራኤል ይባል እንጂ አለ፤ ስሙን እስራኤል ብሎ ጠራው" (35፡9-11) በማለት የእስራኤል ነገድ በነገዱ አባት መጠራቱ ተጠቅሷል።

በተመሳሳይ መልኩ የነገደ ወይጦ ስያሜም የወይጦ አባት ነው ተብሎ ከሚታመንበት ዋቶ ጋር ተያይዞ የሚነገር ተረክ አለ። ዋቶ፣ ቅማንትና አዝማሪ የሚባሉት ነገዶች በችግር ምክንያት ወደ ኢትዮጵያ ፈልሰው ሲገቡ በተለይ ዋቶዎች ለሁለት ተከፍለው ግማሾቹ ወደ ከፋ ግማሾቹ ደግሞ የአባይ ወንዝን ተከትለው በጣና ሀይቅ ዙሪያ መስፈራቸውን፣ ወደ ከፋ የሄዱት እስከ ዛሬ ድረስ ዋቶ ወይም ዋታ ተብለው ሲጠሩ፣ በጣና ሀይቅ ዙሪያ ያሉት ግን በጊዜ ብዛት "ዋቶ ይባል የነበረው ተለውጦ ወይጦ" መባሉን በተረክ አንድና አምስት ይጠቅሳሉ (ሰጡ፣ ካሴት 1(ሀ)፣ ሚያዝያ 30 ቀን 2003፣ ባህር ዳር፤ ጅብሪል፣ ካሴት 3(ለ)፣ ግንቦት 03 ቀን 2003)።

ዮሀንስም ይህን ሀሳብ በማፅናት "ስምሪ ዋቶን ወለደ ዋቶ ደግሞ የወይጦዎች አባት ነው። ... በዘመን ብዛት ዋቶ ተለውጦ ወይጦ ተባለ" (1940፡108) በተመሳሳይ ታዬ "ስማቸው በአባታቸው ስም ዋቶ ነው። ከዋቶ እያደረ ወደ ወይጦ ተመለሰ" (1920፡12) በማለት ይናገራል።

ይህ የስያሜ መነሻ ተረክ ከነገደ ወይጦ ማህበረሰብ የተገኘ ይመስላል። የማህበረሰቡ የስያሜ መነሻ ምክንያት በዚህ መልኩ መቅረቡ ወይጦ የሚለው ስያሜ በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ የሚሰጠው መጥፎ ትርጉም መሰረት አልባና ከአመጋገብ ልማዳቸው በመነሳት የሚሰጠው ስያሜ ተጨባጭነት የሌለው እንደሆነ እዲገነዘቡ በማድረግ በኩል አስተዋጽኦ ይኖረዋል። በሌላ መልኩ ደግሞ ወይጦዎች ተራ ህዝቦች ሳይሆኑ እንደ አካባቢው ማህበረሰብ ስረ መሰረት ካለው ነገድ የመጡ እንደሆኑ እንዲያስቡ ሊያግዝ ይችላል።

### 4.1.3. ከስራ ባህላቸው አንፃር የተሰጠ ስያሜ

አንድ ማህበረሰብ ወይም ቡድን ከሚሰራው የስራ አይነት ወይም ጠባይ አንፃር ሊጠራ ይችላል፡፡ ስያሜውም ለተወከለበት ማህበረሰብ በመጠሪያነት ያገለግላል፡፡ በአገራችን በቀደመው ጊዜ ሸማኔ፣ ቀጥቃጭ/አንጥረኛ፣ ሸክላ ሰሪ/ደበላንላ፣ አዝማሪ፣ ወታደር ወዘተ እየተባሉ በሚሰሩት ስራ ስያሜ ይሰጣቸው ነበር፡፡

በተመሳሳይ መልኩ ወይጦ የሚለው ስያሜ የመጣው የወይጦ ማህበረሰብ በአንድ ቦታ አረግተው የማይኖሩና ባተሌ ወይም ዋቶ አደር በመሆናቸው ዋቶ የሚለው ቃል ወደ ወይጦ መለወጡን ይናገራሉ (ጅብሪል፣1975፡29)፡፡ ይህን ሀሳብ በማዕናት ምስጌ የማህበረሰቡ አባላት አብዛኛውን ጊዜ የዕለት ከዕለት ኑሯቸውን የሚያካሂዱት በጣም በሚያደክም ስራ ስለነበር በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ ዋቶ/ባዝና/ አደር ይባሉ እንደነበርና ይህ ቃል ከጊዜ ብዛት ተለውጦ ወይጦ በሚለው ስያሜ የተተካ መሆኑን ይገልፃል (1979፡2)፡፡

ይህ ተረክ የማህበረሰቡ አባላት በአድካሚ የስራ መስክ ብቻ ተሰማርተው እንደሚኖሩ ያሳያል፡፡ በመሆኑም ስያሜው ለአባላቱ ለፍቶ ማደር የቀደሙ አባቶቻቸውም ተግባር እንደሆነ ያመላክታል፤ በተጨማሪም በጉልበታቸው፣ በላባቸው ጥረው ግረው የሚኖሩ እንጂ በአቋራጭ ለመክበር የሚሞክሩ የማህበረሰብ ክፍል እንዳልሆኑ እንዲያምኑና ሙያቸውን አክብረው እንዲኖሩ በማሰብ የተነገረ ይመስላል፡፡ በሌላ መልኩ ወይጦ የሚለው ስያሜ ከአመጋገብ ስርዓታቸው የመጣ ሳይሆን ለፍቶ አዳሪ ከመሆናቸው የተነሳ የተሰጠ እንደሆነ የአካባቢው ማህበረሰብ እንዲያምን የተነገረ ይሆናል፡፡

### 4.1.4. በአካባቢው ካለ የእህል ፍሬ ጋር በተያያዘ የተሰጠ ስያሜ

በዚህ ክፍል የማህበረሰቡ ስያሜ መነሻ ከአንድ የእህል ፍሬ መጠሪያ ጋር የተሳሰረ እንደሆነ የሚነገረውን ለማየት ይሞከራል፡፡ በተረኩ የማህበረሰቡን ስያሜ የሰጠው የአማራው ማህበረሰብ እንደሆነ ሙሀመድ በተረክ ስድስት ሲገልጽ፣ ማህበረሰቡ ከግብጥ ተነስቶ ወደ ኢትዮጵያ ሲመጣ ፍላጣ፣ መንጠቆ፣ ፊሾ ጤፍና ግብጦ የምትባለዋን የእህል ፍሬ ይዞ እንደመጣና አማራውም ያችን ለእነርሱ እንግዳ የሆነችውን የእህል ፍሬ ምንነት ለማወቅ በመፈለግ ሲጠይቋቸው ፍሬዋን ከግብፅ ማምጣታቸውን ለመናገር

በቋንቋቸው ግብጣዊ ናት ሲሉ እህሉን "ግብጦ" ማህበረሰቡን ደግሞ ወይጦ ብለው መሰየማቸውን ይናገራል (ካሴት ቁጥር 6(ለ)፣ ግንቦት 6 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)፡፡

በተመሳሳይ ነጃት በተረክ አስራ ሁለት "ወይጦ" የሚለው ስያሜ የመጣው በማህበረሰቡ ዘንድ የሚታወቀውን የእህል ፍሬ "የአማራው ማህበረሰብ ምን እንደሆን ሲጠይቋቸው ግብጦ ብለው በቋንቋቸው ቢናገሩ ግብጦ ሲሉ ወይጦ በማለት ለማህበረሰቡ ስያሜ ሰጠዋቸል ሲባል በአባት የቃል መረጃ በታሪኩ አቆይተውናል" (ካሴት ቁጥር 15(ሀ) ግንቦት 15 ቀን 2003፣ ባህር ዳር) በማለት ይገልጻል፡፡

በዚህ ተረክ የነገዱ ስያሜ ከማህበረሰቡ ጋር አብሮ ወደ ኢትዮጵያ ገብቷል ተብሎ በሚታመንበት የእህል ፍሬ ተሰይሟል መባሉ እንድም ማህበረሰቡ አመጣጡን ከ"ግብፕ" እንደሆነ ስለሚያምኑና መጠሪያቸውም "ወይጦ" ስለሆነ ለሁለቱም ስያሜዎች የድምፅ ቅርበት ያለውን የእህል ፍሬ በመምረጥ የስያሜ መነሻ ሆኖ እንዲያገለግል የተነገረ ሊሆን ይችላል፡፡ ወይም ግብጦ በኢትዮጵያ ውስጥ በብቸኝነት የሚገኘው ማህበረሰቡ በሚኖርበት አካባቢ ብቻ የሚገኝ ወይም የግብጦ ፍሬ ሳይታረስ የሚበቅል እና ፍሬው ውሃ ውስጥ ተነክሮ ከሰነበተ በኋላ የሚበላ በመሆኑ ከማህበረሰቡ ጋር ግንኙነት ይኖረው ይሆናል ከሚል እሳቤ ይመስላል፡፡

በሌላ መልኩ ግብጦ የሚመርና በርካሽ የሚገኝ፣ በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ የዝቅተኛ ደሪዎች ምግብ እንደሆነ ይቆጠራል፡፡ ይህንንም ዝቅ ተደርጎ የሚታይ የእህል አይነት በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ በዝቅተኛነት ለሚታዩት የማህበረሰብ ክፍሎች መስጠት ተፈልጎ ይሆናል ወይም ማህበረሰቡም ወደ ኢትዮጵያ ሲመጣ የሚጠቅም ወይም የከበረ ነገር አለማምጣቱን በመንገር ነገዱ ከስረ መሰረቱ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ የነበረና ተራ ምግብ የሚመገብ እንደሆነ ለማሳየት ይሆናል፡፡

## 4.2. ከነገደ ወይጦ ማህበረሰብ አመጣጥ ጋር የተያያዙ ተረኮች

በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ጽሁፍ ከመጀመሩ በፊት የሰው ልጅ ልማድና ታሪክ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፈው በቃል እንደነበር ይታወሳል፡፡ ስለሆነም በአንድ አገር ውስጥ ያሉትን የማህበረሰብ ክፍሎች ልማድና ታሪክ ለማጥናት ቃላዊ የታሪክ መረጃዎች (Oral History) ከፍተኛ አስተዋፅኦ አላቸው (Vansina,1985:12; ምስጌ፣ 1979:1)፡፡ የነገደ ወይጦ ማህበረሰብ አባላትም ስለአመጣጣቸው ሲጠየቁ በቃላዊ ዝርው

ተረኮቻቸው አማካይነት ኬትመጣችን ነው ብለው የሚያምኑበትን እና የዘር ሀረጋቸውን ከታወቁ የሃይማኖት መሪዎችና ነገስታት ጋር ያስተሳስሩታል፡፡ በሌላ መልኩ ደግሞ በርሃብ ምክንያት ከግብፅ ተነስተው መምጣታቸውን ይናገራሉ፡፡ በተጨማሪም እንደስያሜያቸው ሁሉ አመጣጣቸው ላይም ከአመጣጣችን ጋር ተያይዞ በአካባቢው ማህበረሰብ የተነገረ ነው በማለት የሚያቀርቡት ተረክ አለ፤ በዚህ ክፍልም ለንጽጽር እንዲያመች ሲባል በቅድሚያ በአካባቢው ማህበረሰብ ተነገረ የተባለውን በማቅረብ በማስከተል ደግሞ ማህበረሰቡ የእኛ ናቸው የሚላቸውን ለማቅረብ ይሞከራል፡፡

### 4.2.1. ነገደ ወይጦና ጡሊ (ቅምጫና ቅል)

የማህበረሰቡን አመጣጥ በተመለከተ ከሚነገሩት ተረኮች መካከል አንዱ በጡሊ /ቅምጫና ቅል/ ውስጥ ከነበረች ውሃ እንደተገኙ የሚተረከው ነው፡፡ ይህ ተረክ በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ ስለአመጣጣቸው የሚነገር እንጂ በማህበረሰቡ አባላት ዘንድ ተቀባይነት እንደሌለው በተረክ ሃያ አንድ ይናገራል (ሰሎሞን፣ ካሴት ቁጥር 11(ለ)፣ ግንቦት 9 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)፡፡ ተረኩ አንድ ሙስሊም በጡሊ /ቅምጫና ቅል/ ውሃ ይዞ ሊሰግድ ሲሄድ በመንገድ ላይ አንድ መንገደኛ ውሃ ጠምቶት ስለነበር በጡሊ የያዘውን ውሃ ሲያይ ለመጠጣት በመፈለጉ ጡሊዋን የያዘውን ሰው ውሃ ጠምቶኛልና ስጠኝ ይለዋል፡፡ ባለጡሊውም አልሰጥህም ይለዋል፡፡ ያ ውሃ የጠማው ሰውም አዝኖ ይሄዳል፡፡ ሙስሊሙ ባለጡሊም ሊሰግድ ካሰበበት ቦታ ደርሶ ውሃውን ሊያፈስ ቢሞክር አልፈስ ይለዋል፡፡ እንዴት ውሃው አይፈስም ብሎ ጡሊዋን ቢሰብራት ሰው ሆኖ ወጣ በማለት ማህበረሰቡን "ከቅል ውስጥ ተፈቅፍቃችሁ ሰው የሆናችሁ ናችሁ" እንደሚሏቸው ይናገራሉ (ዝኒ ከማሁ፣ ካሴት ቁጥር 11(ለ))፡፡

ምንም እንኳ ይህ ተረክ የማህበረሰቡ አባላት ስለአመጣጣቸው ከሚናገሩት የተለየና ከመንፈሳዊውም ሆነ ከአለማዊው አስተምህሮ የተለየና ተአማኒነት የሌለው ነው ቢባልም የተነገረበት የራሱ የሆነ ምክንያት ይኖረዋል፡፡

ከተረኩ እንደምንገነዘበው ከቅሏ ውስጥ ሰው ሊገኝ የቻለበት ዋናው ምክንያት ለአምልኮ ወይም ለመስገድ የሚሄደው የእስልምና እምነት ተከታይ የሆነ ግለሰብ "ያላችሁን ለሌላቸው አካፍሉ" የሚለውን መንፈሳዊ አስተምህሮ አቃልሎ በመሄዱ ምክንያት ወይም

የተጠማው ሰው ሀዘን ያመጣው ውጤት እንደሆነ እና ተጠኝው ማህበረሰብም የኃጢአት ፍሬ እንደሆነ ለማሳየት ይሆናል፡፡

በሌላ መልኩ ማህበረሰቡን ውሃ ከያዘች ቅምጫና ቅል የተገኘ እንደሆነ መገለፁ አመጣጣቸው ከሰብአዊ ፍጡር ሳይሆን ህያው ነፍስ ከሌለው ቁስ እንደሆነ በማሳየት የማህበረሰቡን ስነልቦና ወይም ሰብዕና መጉዳትና ራሳቸውን ዝቅ አድርገው እንዲመለከቱ፤ ሌላውም ማህበረሰብ እንዲያገላቸው ለማድረግ የተነገረ ሊሆን ይችላል፡፡

የተረኩ ባለቤት (ገፀባህርይ) ሆኖ የተመረጠው እስላም እንዲሆን መደረጉም የማህበረሰቡ አባላት የእስልምና እምነት ተከታዮች በመሆናቸው ሊሆን ይችላል፡፡

ቅምጫናዋ ውስጥ ከነበረው ውሃ እንደተገኙ መነገሩ ደግሞ ምናልባት ተፈጥሯችሁ በቅል ውስጥ ከነበረው ውሃ ውስጥ እንደሆነ ሁሉ ህይወታችሁ የተመሰረተውም በውሃ ላይ ነው ለማለት ይሆናል፡፡

በአጠቃላይ ይህ ተረክ ሰብአዊ ፍጡር እንዳልሆኑ በማሳየት የአካባቢው ማህበረሰብ አባላት በማንኛውም ማህበራዊ ሕይወት እንዲያገላቸው ለማድረግ ታስቦ የተነገረ ይመስላል፡፡

### 4.2.2. ነገደ ወይጦና ነብዩ ሙሴ (ሙሳ)

የነገደ ወይጦ ማህበረሰብ ስለአመጣጣቸው ሲጠየቁ በነብዩ ሙሴ አማካኝነት እስራኤላውያን ከግብፅ ባርነት ነፃ ወጥተው ወደ ከነአን ለመሄድ ጉዞ ከጀመሩበት ዘመን ጋር ግንኙነት እንዳለው ይናገራሉ፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ በተረክ አስራ ስድስት ጅብሪል ሲናገር፣

> ብሄረሰቡ የመጣው በነብዩ ሙሳ ዘመን ተግብጥ ነው ይባላል፡፡ ነብይ ሙሳ ከተከታዮቻቸው ጋር ተግብጥ ተነስተው ሲሄዱ ታንድ ወንዝ ደረሱ፡፡ ተወንዙ ሲደርሱም ህዝቡ ሁላ ውሃ ስለጠማው በከፊል አርጋችሁ ጠጡ በብዛት ስትጠጡ ትደክማላችሁና በከፊል አርጋችሁ ጠጥታችሁ እንሻገር ሲሉ ያው ከፊሉ መሪው ያዘዘውን ጠጣና ሲሄድ፣ ከፊሉ የጠማው ሰው ዝም ብሎ የጠጣ ጊዜ በዚያ ወንዝ ቀረ ይላሉ፡፡ በዚያው እንደተለያዩ ግብጥን አርገው እንግዲህ ያው አባይ ላባይ ሱዳንን አርገው ያገኙትን እየገደሉ አምባዛውን፣ አሳውን እየገደሉና እየበሉ

> ከዚህ የደረሱት ሰበቡ በዚህ ነው። (ካሴት ቁጥር 1(ሀ) ሚያዝያ 30 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)።

በማለት ይገልፃል። ይህ ተረክ የማህበረሰቡን አመጣጥ ለመግለፅ ከማገልገሉም በተጨማሪ ሌላ አገልግሎት ያለው ይመስላል። ይኸውም በተረኩ ማህበረሰቡ ወደ ኢትዮጵያ መጥቷል ተብሎ የሚታመንበት ዘመን ብዙ አመታትን ያስቆጠረ እንደሆነ መጠቀሱ፣ በተለይ በንቀት አይን ለሚመለከታቸው ወይም ከዚህ በላይ ባለው ተረክ ለማሳየት እንደተሞከረው እንደ ሰብአዊ ፍጡርና እንደ ነባር ህዝብ ለማይቆጥራቸው የአካባቢው ማህበረሰብ ጥንታዊነታቸውንና ከሰብአዊ ፍጡር የተገኙ መሆናቸውን በማሳየት በኩል አስተዋጽኦ ሊኖረው ይችላል።

በሌላ መልኩ የዘር ግንዳቸውን ከነብዩ ሙሴና ተከታዮቹ ጋር የተሳሰረ እንደሆነ መጠቀሱ፣ በተለይ በሚከተሉት የአመጋገብ ስርዓትና በሚፈፅሙት የአምልኮ ስርዓት እንደ ርኩስ ለሚቆጥራቸው የአካባቢው ማህበረሰብ ከክርስቶስ ልደት ከብዙ ሺህ አመታት አስቀድሞ አባቶቻቸው ከነብዩ ሙሴ ጋር በመሆን አምልኮተ እግዚአብሄርን ይፈፅሙ እንደነበር ለማሳየትና ለአባላቱም የሚከተሉት የአመጋገብ እና የአምልኮ ስርዓትን ትክክለኛነት በማረጋገጥ ቀጣይነት እንዲኖረው በማድረግ በኩል እገዛ ሊያደርግ ይችላል።

በተለይ ደግሞ የዘር ሀረጋቸውን ከሊቀ ነብያት ሙሴ ነገድ ጋር አስተሳስሮ ማቅረቡ ዘራቸው የጠራና በእግዚአብሄርም ዘንድ የተመረጠ አድርጎ ለማሳየት ይመስላል።

### 4.2.3. ነገደ ወይጦና ግብፅ

የማህበረሰቡ አባላት ስለአመጣጣቸው ሲጠየቁ በአብዛኛው የሚመልሱት ከግብፅ እንደሆነ ነው፤ ሆኖም በተረኮቹ መነሻ ቦታቸው ግብፅ እንደሆነ ቢጠቅሱም ወደ ኢትዮጵያ እንዴት እንደገቡ የሚያቀርቡት ምክንያት ግን የተለያየ ነው። በቅድሚያ ስለማህበረሰቡ አመጣጥ ከግብፅ መሆኑን በመጥቀስ ሰሎሞን በተረክ ሃያ ሲናገር፣

> የነገደ ወይጦ ማህበረሰብ አመጣጡ ግብፅ ውስጥ ነው። በአንድ ዘመን በግብፅ ጦርነት ይነሳል። በወቅቱም አንድ ላቂ ደምበል የሚባል ጎሳ እና ነገደ ወይጦ የሚባል ጎሳ ባንድ ላይ ሁነው ወደ ኢትዮጵያ ድንበር ይመጣሉ። ጦርነቱ እስኪያልፍም ሀገሩን ወደውት ኖሩ። ጦርነቱ እንደተጠናቀቀ ወደ ሀገራቸው

ተመልሰው በሰላም መኖር ሲጀምሩ ደግሞ ሀገራቸው ትራባለች። እነሱም "ወደ ኢትዮጵያ ድንበር ሄደን ጊዜውን እናሳልፍ" በማለት ሁለቱ ጎሳዎች ያባይን ወንዝ ተከትለው ጉዞ ይጀምራሉ። በጉዟቸውም ጉማሬ፣ አምባዛ፣ ቀይ አሳና አሞራ እያደኑ ይበሉ ነበር። ዋናው መግደያቸውም እንጨት ነው፤ በጣም ጀግኖች ነበሩ። አዋሳ አካባቢ ሲደርሱ ላቂ ደምበል የሚባለው ጎሳ በዚያው ይቀራል። ነገደ ወይጦ ግን ማደን ሳይሰለቸው ወንዝ ለወንዝ ጉዞውን ቀጥሎ አባይ ራስ ድረስ ከተጓዘ በኋላ በዚያው ቦታ እያደነ መኖር ጀመረ (ካሴት ቁጥር 11(ለ)፣ ግንቦት 8 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)።

በዚህ ተረክ ማህበረሰቡ ከግብፅ ወደ ኢትዮጵያ እንደመጣ ተጠቅሷል። ከየት እንደመጡ መጠቀሱ በተለይ "ከቅምጫና ቅል ውስጥ ካለች ውሃ ተገኙ" ከሚለው የአካባቢው ማህበረሰብ አመለካከት ጥገኛ ላለመሆን ለአባላቱ የሚያግዝ ይሆናል። ወይም ማህበረሰቡ ለሚደርስበት የስነልቦና ጫና እና ለሚፈጠርበት የማንነት ጥያቄ ምላሽ በመስጠት በኩል አስተዋፅኦ ይኖረዋል። ሌላው ከሁለቱ ጎሳዎች መካከል ላቂ ደምበል የሚባለው በጉዞ ላይ እንዳለ አዋሳ አካባቢ ሲቀር፣ ነገደ ወይጦ ግን እስከ አባይ ራስ ድረስ ታላላቅ የውሃ ውስጥ እንስሳትን እያደነ እንደተጓዘ መነገሩ ከላቂ ደምበል ጎሳ ይልቅ ነገደ ወይጦ የተሻለ የማደን አቅም እንደነበረው ለማሳየት የገባ ይመስላል። ይህም ለጎሳው አባላት የቀደሙ አባቶቻቸውን የውሃ ላይ ገድል በመመልከት በግብር እንዲመስሏቸውና በታሪካቸውም እንዲኮሩ፣ ወይም የዘር ሀረጋቸው መንፈስ ጠንካራና ጀግና እንደሆኑ እንዲያምኑ ሊያደርግ ይችላል።

ነገዱ ወደ ኢትዮጵያ ሲመጣ ጉማሬ፣ አምባዛና ሌሎች የውሃ ውስጥ ፍጥረታትን እያደነ መምጣቱ መነገሩ እንድም የማህበረሰቡ አባላት ጉማሬንና ሌሎቹን በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ እንደ ርኩስ የሚታዩ የውሃ ውስጥ እንስሳት በመመገባቸው ተገልለው ስለሚኖሩና በንቀት ስለሚታዩ እኛ እነዚህን ምግቦች የለመድናቸው በርሃብ ዘመን ባደረግነው አስቸጋሪ የባህር ላይ ጉዞ እንጂ የቆየው የአመጋገብ ስርዓታችን አይደለም ለማለት ይመስላል።

### 4.2.4. ነገደ ወይጦ፣ ንግስተ ሳባና አፄ ፋሲል

የማህበረሰቡ አባላት ስለነገዱ አመጣጥ ሲጠየቁ እንደ መነሻ ምክንያት ከሚያቀርቡት አንዱ የዘር ሀረጋቸው ከንግስተ ሳባና ከአፄ ፋሲል ጋር የተገናኘ እንደሆነ ነው። ይህን በተመለከተ ሙሀመድ በተረክ አስራ ዘጠኝ ንግስተ ሳባ ከባሪያዋ ጋር ወደ ግብፅ እንደሄደች፤ በግብፅም ከሀገሪቱ ንጉስ ጋር አብሮ ከመቆየትና ከመግባባት የተነሳ

እንደተፋቀሩ ይገልፃል። ሳባም ወንድ ልጅ ፀነሰችና ወደ አገሯ ተመለሰች። ልጁም ካደገ በኋላ አባትህን ተዋወቀው ብላ ወደ ግብፅ ላከችው። አባቱም ለልጁ ፋሲል ብሎ ስም አወጣለት። ፋሲልም ብዙ ልጆችን ወለደ። በተለይ ሦስት ልጆቹ በየቦታው ተበታትነው ከኖሩ በኋላ አንዱ ጎሳ በጣቁሳ አድርጎ ወደ ጎርጎራ ገብቷል። ሌላኛው ጎሳ ደግሞ በጎንደር ወደ እንፍራንዝ ገባ። ሦስተኛው ደግሞ በጎጃም በኩል ባህር ዳር መጥቷል። ይህም ነገደ ወይጦ ኢትዮጵያ ውስጥ ካለው ህዝብ ጋር አብሮ እንደተቀላቀለ የሚሳይ ነው በማለት ይናገራል (ካሴት ቁጥር 5(ለ)፣ ግንቦት 6 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)።

ይህ ተረክ ከክርስቶስ ልደት አንድ ሺህ አመት አካባቢ ወደ እየሩሳሌም ሄዳ ከንጉስ ሰሎሞን ቀዳማዊ ምኒልክን ወለደች ተብሎ ከሚታመንበት አፈ ታሪክ ጋር ግንኙነት አለው። ልዩነቱ ንግስተ ሳባ ሄደችበት የተባለበት ቦታና የወለደችው ልጅ በአስራ ሰባተኛው ክፍለ ዘመን በኢትዮጵያ የነገሰው አፄ ፋሲል ጋር ተመሳሳይ ከመሆኑ ላይ ነው።

በተረኩ የነገደ ወይጦን አመጣጥ ከነገስታት የዘር ሀረግ ጋር ማስተሳሰሩ ለማህበረሰቡ አባላት ኬትመጣቸው ከታወቁት ነገስታት እንደሆነ እንዲያምኑ፤ በተለይም በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ ከሚደርስባቸው ተፅዕኖ እፎይታ እንዲያገኙና የበታችነት ስሜት እንዳይፈጠርባቸው ለማድረግ ይሆናል።

### 4.2.5. ነገደ ወይጦና የአካባቢው የቦታ ስያሜዎች

ሌላኛው ተረክ የማህበረሰቡ አባላት ከፀሀይ መውጫ ወይም ከምስራቅ እንደመጡ የሚገለፀው ነው። አዳሩ የተባለ ሰው ሞንታፌላ ከተባለች ሚስቱ ፉጋ፣ ደምባቁራ፣ ጎራዋና ሽሎ የተባሉ አራት ወንድ ልጆችን ይወልዳል። የእነኝህ ልጆች ስም በማህበረሰቡ ውስጥ ላሉት ጎሳዎች እንደመጠሪያ የሚያገለግል ሲሆን፣ ፉጋ ደቡብ ጎንደር ላለው ፎገራ፣ ደምባቁራ ደግሞ ሰሜን ጎንደር ላለው ደንቢያ ወረዳዎች ስያሜ ሆኖ እንደሚያገለግል ገልፀው ጎራዋ ለአለፋ፣ ሽሎ ደግሞ ባህር ዳር ላሉት ጎሳዎች አባት መሆናቸውን ይናገራል (ምስጌ፣1979፡1)።

ይህ ተረክ ከሌላዎቹ ተረኮች ለየት የሚያደርገው በተለይ የማህበረሰቡ አመጣጥ ከግብፅ ሳይሆን ከምስራቅ አቅጣጫ መሆኑ ነው።

በዚህ ተረክ የማህበረሰቡ ጎሳዎች ስምና አሰፋፈር ተጠቅሷል። በተለይ የሁለት ወረዳዎች ስያሜ የጎሳዎቹ አባት ስም እንደሆነ ይነገራል። ይህ ደግሞ ለተጠቀሱት አካባቢዎች መስራች እንደሆኑ ወይም ያካባቢው ማህበረሰብ ከመምጣቱ በፊት ቦታውን በባለቤትነት ይዘውት እንደነበር ለማሳመን የቀረበ ሊሆን ይችላል ወይም እዚያ አካባቢ ለሚኖረው ማህበረሰብ እናንተ የምትኖሩበት ቦታ የእኛ አባቶች በመሰረቱት ላይ ነው ለማለት አሊያም ከእናንተ በፊት የእኛ ግዛት ነበር የሚለውን ለማሳየት ይሆናል።

የጎሳዎቹ አሰፋፈር መጠቀሱ ደግሞ እያንዳንዱ የነገዱ ህዝብ በሚኖርበት አካባቢ ጎሳው እንደነበርና ቦታው ከአባቶቹ ሲወርድ ሲዋረድ ለእነርሱ የደረሰ ዕጣ እርስቱ እንደሆነ እንዲያምንና ምንም እንኳን የአካባቢው ማህበረሰብ ጫና ቢፈጥርበትም የአባቶቹን ወይም የጎሳዬን አካባቢ አለቅም ብሎ በዚያው ፀንቶ እንደቆየ ለማሳየት ይመስላል። አንድም ማህበረሰቡ አሁን ከደረሰበት የህዝብ ቁጥር ማሽቆልቆል በፊት ባለአራት ጎሳ ወይም እንደ አካባቢው ማህበረሰብ ትልቅ ህዝብ እንደነበር ለመንገር ይመስላል።

## 4.3. ነገደ ወይጦና ሼህ ጅብሪል

የማህበረሰቡ አባላት የሃይማኖት ጥንካሬን በተመለከተ ሼህ ጅብሪል ከሚባሉ ሰው ጋር አያይዘው የሚናገሩት ተረክ አለ። ይኸውም ሼህ ጅብሪል ሰጭአላህ በኃይለስላሴ ዘመነ መንግስት ከአዲስ አበባ ዋናው አቡን ይመጡና "እነዚህ ምንድናቸው?" ሲሉ ወይጦ ይባላሉ ይሏቸዋል። አቡኑም ታዲያ እስላሙም ሆነ ክርስቲያኑ እያስጠጋቸውም፤ ከሁለቱም ካልሆኑ ክርስትና መነሳት አለባቸው ይላሉ። ሆኖም ሼህ ጅብሪል ቅዱስ ቁራንን ይዘው በሃይማኖቴ እፀናለሁ እንጂ ክርስትና አልነሳም ይላሉ። አቡኑም በሃይማኖትህ ተከራክረህ ብትሸነፍስ ሲሏቸው ሼህ ጅብሪል "ከተሸነፍኩ ክርስትና እነሳለሁ ሆኖም የማልሸነፍበት ቅዱስ ቁርአን አለኝ" አሉ። በኋላም ከአቡኑ ጋር ተከራክረው ባለመሸነፋቸው አቡኑ አድንቀዋቸው አዲስ አበባ ወስደው ሸልመውና አልብሰው ሰደዋቸዋል በማለት በተረክ ሃያ አምስት ይናገራል (ጅብሪል፣ ካሴት ቁጥር 3(ለ)፣ ግንቦት 03 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)

በተረክ ሃያ ስድስት ደግሞ "አዲስ አበባ ድረስ ሄደው ጳጳሱ ጋር ተከራክረው በሃይማኖታቸው አሸናፊ ሆነው የመጡ ናቸው፣ ከባህር ዳር ሙስሊም እንደኛ ተብለው

የኖሩ እሳቸው ናቸው።" ይላል (ሰይዴ፣ ካሴት ቁጥር 4(ለ)፣ ግንቦት 5 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)

በእነዚህ ተረኮች ሼህ ጅብሪል ከአዲስ አበባ የመጣውን የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ዋና ጳጳስ ተከራክረው አሸንፈዋል ተብሎ መነገሩ የማህበረሰቡ አባላት የሚከተሉት እምነት የአካባቢው ማህበረሰብ የሚከተለው የክርስትና ሃይማኖት መሪ እንኳ የተሸነፈበት በመሆኑ ትክክለኛ እና ለፅድቅ የሚበቃ እንደሆነ እንዲያምኑ፣ እንዲሁም የእነሱ የእምነት መሪ በእምነታቸው ምን ያህል ጠንካራና የማይሸነፉ እንደነበሩና አባላቱ የሼህ ጅብሪልን አርአያ ተከትለው እንዲጓዙ ለማድረግ የተነገረ ይመስላል።

በመጀመሪያው ተረክ ውስጥ ጳጳሱ ተናገሩ ከተባለበት ክፍል አንዱ "ክርስቲያኑም እስላሙም አያስጠጋቸውም" የሚል ነው። ይህ ደግሞ ማህበረሰቡ በእስልምናም ሆነ በክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች ዘንድ የተጠሉና የተናቁ ቢሆኑም እንኳ ይህ ሁሉ ሳይበግራቸው አባቶቻቸው በሃይማኖታቸው ፀንተው የቆዩ እንደሆኑና አዲሱ ትውልድም ተመሳሳይ ችግር ቢገጥመው በቀላሉ እንዳይሸነፍ ለማድረግ የተነገረ ይሆናል። ወይም የሼህ ጅብሪል አርአያነት በቀጣዩ ትውልድ እንዲታወስ ወይም ያደረጉት ተጋድሎ እንዳይረሳ ይመስላል። ይህን በተመለከተ ሰይዴ የማህበረሰቡ አባላት በአመት አንድ ጊዜ መጋቢት 30 ቀን የሞቱበትን ቀን ምክንያት በማድረግ ተሰባስበው የመውሊድ በዓላቸውንና ሙት አመታቸውን ያከብራሉ (ካሴት ቁጥር 4(ለ)፣ ግንቦት 5 ቀን 2003፣ ባህር ዳር) በማለት ይገልጻል።

## 4.4. ነገደ ወይጦና አቢናዝ

የማህበረሰቡ አባላት ከእስልምና ሃይማኖት ጎን ለጎን አቢናዝ የሚሉትን የአምልኮ ስርዓት ይፈፅማሉ። የአፈፃፀሙን ስርዓት በተመለከተ ባህላዊ ስርዓታቸው በሚዳስስበት ምዕራፍ ለማንሳት ይሞከራል፤ ሆኖም ለአቢናዝ በዓል መጀመር መነሻ የሆናቸውን ምክንያት በተመለከተ ከሚያቀርቡት ተረክ በመነሳት ትንታኔ ለመስጠት ይሞከራል።

ኑር አቢናዝ ወይም አቢናዝ የሚለው አምልኮ የተጀመረው አንድ የነገደ ወይጦ ተወላጅ የሆነ ግለሰብ በሌሊት በጣና ሀይቅ ላይ ሲጓዝ በባህሩ ውስጥ ያሉት ጅኒዎች (ሰይጣኖች) አንዱን ልጃቸውን በባህር ላይ ረስተውት ይሄዳሉ። ግለሰቡም አግኝቶት ወደ ቤቱ

ይወስደውና ያስቀምጠዋል። ጅኒዎቹም የልጃቸውን መጥፋት ሲያውቁ ወደ ግለሰቡ ቤት ይሄዳሉ። ልጃቸውንም እንዲመልስላቸው ይጠይቁታል። የማህበረሰቡ አባላትም በግለሰቡ ቤት ተሰባስበው ከጂኒዎቹ ጋር ድርድር ይጀምራሉ። ድርድሩም "የእኛን ማህበረሰብ አባላት በቀንም ሆነ በሌሊት አደን ሲወጡና ለሌላ ጉዳይ በሀይቁ ላይ ሲጓዙ የማትነኳቸው ከሆነ ልጃችሁን እንለቅላችኋለን፤ ካለበለዚያ ግን እንገለዋን" ይላሉ። ጅኒዎቹም "የእናንተ ዘር የሆነ አንገልባችሁም፤ ሆኖም በጉግ የተቀባ የዳጉሳ ቂጣ እና ያልሸና ወይፈን በአመት አንድ ጊዜ በባህሩ ላይ አቋድሱን" በማለት ቃል ይገባሉ። በውላቸው መሰረትም ልጃቸውን ለቀቁላቸው። የማህበረሰቡ አባላትም በየአመቱ ወደ ወንዙ እየሄዱ የገቡትን ቃል ይፈፅማሉ በማለት በተረክ ሰላሳ ይገልፃል (ሰሎሞን፣ ካሴት ቁጥር 10(ለ)፣ ግንቦት 8 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)።

በተረክ ሰላሳ አንድ ስለአቢናዝ የሚነገረው ደግሞ በአብዛኛው ከላይ ከቀረበው ተረክ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ቢመስልም በመጠኑም ቢሆን ልዩነት ይታይበታል። ይኸውም አቢናዝ ጊዮን የሚባል ጅኒ ሲሆን፣ የጅኖች ሁሉ የበላይ ነው። ቀንዱ ከባህር ዳር እስከ ጎርጎራ የሚደርስ እንደሆነ ይናገራሉ። በአንድ ወቅት አንድ የማህበረሰቡ አባል የነበሩ ናቸው የተባሉ አንድ ትልቅ ሰው ጅኒዎችን እያወጡ ሲያናግሩ ጊዮን የሚባለውንም አናግረውታል ይባላል። በሂደት እየተቀራረቡ ከመምጣታቸው የተነሳ ጅኑ ወይም ጊዮንና ግለሰቡ "ያንተ ሰው የሆነውን ላልነካብህ፤ ለእኔ ደግሞ የምጠይቅህን ሁሉ ልታደርግልኝ" በማለት ቃል መገባባታቸውን ይገልፃል (ሙሀመድ፣ ካሴት ቁጥር 14(ለ)፣ ግንቦት 12 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)።

ለመጀመሪያው ተረክ መነሻ የሆነው የማህበረሰቡ አባል የሆነ ግለሰብ በሌሊት በሀይቁ ላይ ሲጓዝ ጅኒዎቹ ረስተውት የሄዱትን ልጅ ይዞ ወደ ቤቱ መሄዱ ነው። ይህን ተረክ የሚሰማ የማህበረሰቡ አባል ደግሞ የቆዩ አባቶቹ ጅኒውን መውሰድና መደራደር የሚያስችል አቅም የነበራቸው ደፋሮች (ሰሎሞን፣ ካሴት ቁጥር 10(ሀ)፣ ግንቦት 8 ቀን 2003፣ ባህር ዳር) እንደሆኑ አምነው እነርሱም በባህር ላይ ሲጓዙ ደፋር መሆን እንደሚገባቸው ለማሳየት ይሆናል።

በሁለተኛው ተረክ ደግሞ በማህበረሰቡና በጊዮን (ጅኑ) መካከል ያለው ግንኙነት የወዳጅ ያህል እንደሆነ ነው። ይህ ደግሞ ማህበረሰቡ በጣና ሀይቅ እና በአባይ ወንዝ ላይ

በሚያደርጉት የዕለት ከዕለት እቅስቃሴ ወዳጃቸው ጊዮን ችግር እንደማይፈጥርባቸው እንዲያምኑ ለማድረግ ይሆናል፡፡

ሌላው በሁለቱም ተረኮች የምንገነዘበው በነገደ ወይጦና በጅኒዎቹ መካከል የተገባው ቃል ኪዳን ነው፡፡ ቃል ኪዳኑ ጅኒዎቹ የነገደ ወይጦን ማህበረሰብ ላይነኩ፣ የማህበረሰቡ አባላት ደግሞ ለጅኒዎቹ በየአመቱ የአምልኮ ስርዓት ሊፈፅሙ መዋዋላቸው ነው፡፡ ይህ ደግሞ ማህበረሰቡ ወደ ሀይቁ ሲገባ ያለ ስጋትና ፍርሃት እንዲንቀሳቀስና ለዕለት ጉርሱ የሚያስፈልጉትን ነገሮች ለመሰብሰብ እንዲችል እንዳበረታታ ሊያግዘው ይችላል፡፡ ለዚህም ይመስላል ጣና ሀይቅም ሆነ አባይ ወንዝ ውስጥ ሌላው የአካባቢው ማህበረሰብ ሲሰምጥ ሬሳ እንዲያወጡና ከውሀው ጋር በተያያዘ የተለያዩ ተግባራትን እንዲፈፅሙ ቅድሚያ ተሰጥቷቸው ወደ ውሃው እንዲገቡ የሚደረገው፡፡

የማህበረሰቡ አባላትም በድፍረት በሀይቁ ላይ ባላቸው የዕለት ከዕለት ህይወት አንድም ቀን ሰምጠው የሞቱበት ጊዜ እንደሌለ ይናገራሉ (ሙሀመድ፣ ካሴት ቁጥር 14(ለ)፣ ግንቦት 12 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)፡፡ ሆኖም በ1985 ዓ.ም የማህበረሰቡ አባላት ለጅኒዎቹ የገቡትን ቃል አፍርሰው በዓሉን ባለማክበራቸው ያጋጠማቸውን ችግር ወለላው በተረክ ሰላሳ ሦስት እንዲህ ይገልፀዋል፡፡

> አቢናዝን በመክዳት አንድ ጊዜ የተፈፀመ ድርጊት አለ፡፡ በ1985 ዓ.ም በውሃ ወይም በአቢናዝ ማመን የለባችሁም ተብለን በአሉን ማክበር አቆምን፤ ሆኖም በሽታ ገባና በቀን ሦስት አራት መሞት ጀመረ፡፡ በኋላ ለትልልቅ ሰዎች በህልም ስላሳየ የማህበረሰቡ አባላት በግ አርደው በሽታውን እንዲያበርድላቸው በመለማመናችን በሽታው ቆሟል፡፡ ከዚያ በኋላ በዓሉን እንደገና ማክበር መጀመራቸውን ይናገራል (ካሴት ቁጥር 17(ሀ)፣ ግንቦት 22 ቀን 2003 ባህር ዳር)፡፡

ይህ እንግዲህ በማህበረሰቡ ዘንድ ለአቢናዝ የሚደረገው የአምልኮ ስርዓት መቋረጥ እንደሌለበት የሚያሳይ ሲሆን፣ ምናልባት በተለያየ ምክንያት ከተተወ ግን የማህበረሰቡን ህልውና የሚፈታተን ችግር ያጋጥማል ከሚል የቀረበ ይመስላል፡፡

በነገደ ወይጦና በአቢናዝ መካከል ስላለው ግንኙነት በተመለከተ በተረክ ሰላሳ አምስት ሙሉ ስትናገር "የኛ ሰው አስረው ቢጥሉትም ውሃው አይበላውም፡፡ አንድ ጊዜ የኛ ነገድ የሆነ ልጅ አባይ ይወስደዋል፡፡ በወቅቱ በቅርበት ስትመለከት የነበረችው የማህበረሰቡ

አባል "እኛው በኛ አቢናዝ እኛው በእኛ አቢናዝ" ብትለው ውሃው ልጇን ከነነፍሱ መልሶ ተፋው" (ካሴት ቁጥር 18(ሀ)፣ ግንቦት 23 ቀን 2003፤ ባህር ዳር) በማለት ትገልፃለች።

በዚህ ተረክ በነገደ ወይጦና በአቢናዝ ወይም በጊዮን መካከል ያለው ግንኙነት ጥብቅ መሆኑን መረዳት ይቻላል።

## 4.5. ነገደ ወይጦና ባህር ዳር

የማህበረሰቡ አባላት ከሚኖርባቸው አካባቢዎች የባህር ዳር ከተማ አንዱ ነው። ሦስት ሺህ ሁለት መቶ ሰላሳ ሁለት ከሚደርሰው የማህበረሰቡ ጠቅላላ የህዝብ ብዛት መካከል አንድ ሺህ አምስት መቶ ሰላሳ ስምንት ያህሉ የሚኖረው በዚሁ ከተማ እንደሆነ ይጠቅሳል (Solomon,2006፡33)። ማህበረሰቡ የአማራው ህዝብ ወደ አካባቢው ከመምጣቱ በፊት በከንፈሮ አባይ ላይ /አባይ ከጣና ሲወጣ/ የነበረውን የማጓጓዝ ተግባር ሲያካሂዱ እንደነበር ይነገራል (ምስጌ፣1979፡5)። በዚህ ምክንያት ይመስላል የማህበረሰቡ አባላት "ባህር ዳር ከተማን የመሰረተው የእኛ ነገድ ነው" የሚሉት (ጅብሪል፤ ካሴት ቁጥር 1(ሀ)፣ ሚያዝያ 30 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)።

ይህን በተመለከተ ሲራክ ሲናገር በ1934 ዓ.ም አካባቢ በከተማው የጣሊያን ባንዳ ሆነው የነበሩ ሴቶችና ወንዶች ጠላት በሰራው ቆርቆሮ ቤት ይኖሩ ነበር፤ ከዚህም ሌላ የአካባቢው ተወላጆችና ነገደ ወይጦዎች ነበሩበት (1975፡27-28) በማለት በወቅቱ ሰፍረው ከነበሩት የከተማው ነዋሪዎች መካከል አንዱ የወይጦ ማህበረሰብ እንደነበር ይጠቅሳል።

በተመሳሳይ መልኩ ሙሀመድ የወይጦ ማህበረሰብ አባላት ባህር ዳርን እንዴት እንደመሰረቷት በተረክ ሰላሳ ስምንት ሲገልፅ፣

> የማህበረሰቡ አባላት መጀመሪያ የሰፈሩት ሹማቦ ፊት ለፊት ነው። በወቅቱ የአሁኑ የፖሊ. ቴክኒክ ኮሌጅ የመምህራን መኖሪያ ቤት የተሰራበት የማህበረሰቡ የቀብር ቦታ ነበር። በዚያ ቦታ ለረጅም ጊዜ ከቆዩ በኋላ ለፖሊ. ቴክኒክ ኮሌጅና ለውሃ ስራዎች ተብሎ እንዲነሱ ተደርጓል። ከዚያም ሲያስለቅቋቸው ጊዮርጊስ አካባቢ ሰፈሩ። በኋላም ለጊዮርጊስ ተብሎ ልቀቁ ተባሉ። በመቀጠልም ስታዲዮሙ ላይ መጥተው ቢሰፍሩም ስታዲየሙ ሲገነባ አስነሷቸው። በመቀጠልም ፋሲሎና ራስ አገዝ አካባቢ ቢሰፍሩም በሂደት ቦታው ይፈለጋል

ተብለው እንዲነሱ መደረጉንና አሁን ባሉበት ቦታ እንዲስፍሩ በደረጉም የባህር ዳር መስራችና ባለቤት ነገደ ወይጦ ነው (ካሴት ቁጥር 14(ሀ)፣ ግንቦት 12 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)።

በማለት ይናገራል።

ይህ ተረክ ባህር ዳር ከተማን በዋናነት የመሰረቱት የነገደ ወይጦ ማህበረሰብ አባላት እንደሆኑና በሂደት ግን በአካባቢው ማህበረሰብ ተገፍተው ወደ ዳር እንዲወጡ መደረጉን የሚገልፅ ነው። ይህ ደግሞ በአንድ በኩል በኢትዮጵያ ውብ ከሚባሉ የክልል ከተሞች አንዷ የሆነችውን ከተማ የመሰረትናት ወይም ባለቤቶቹ እኛ ነን፤ ሌላው ሁሉ መጤ ነው የሚል ሲሆን፣ በሌላ መልኩ ደግሞ እኛ ብንመሰርታትም ባለጊዜ መጥቶ በአገራችን ተገልለን እንድንኖር ሆነናል ለማለት የቀረበ ይመስላል። አንድም ማህበረሰቡ የአሁኑ አኗኗሩ በሌሎች ተፅዕኖ ምክንያት በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ የሚኖርና በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድም በንቀት የሚታይ ቢሆንም አስቀድሞ ግን ማንም ያልሞከረውን ከተማ የመመስረት አቅም ነበረው ለማለት የተነገረ ሊሆን ይችላል።

## 4.6. ነገደ ወይጦ እና የታንኳና የወፍጮ ስራ

ነገደ ወይጦ ታንኳ በመስራት፣ የድንጋይ ወፍጮ በመውቀርና የተለያዩ የዓሳ ማጥመጃ (ማስገሪያ) መሳሪያዎችን በማዘጋጀት ይታወቃሉ (ታፈሰ፣1978፡4)። ከዚያም በፊት በ17ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ወደ ኢትዮጵያ መጥተው የነበሩት Almaida የሚባሉት የኢየሱሳውያን መልዕክተኛን ጠቅሶ ሰሎሞን ሲገልፅ፣ ነገደ ወይጦ ከደንገል ታንኳ ይሰሩ እንደነበር ይገልፃል (2006፡24)። በተመሳሳይ የሻነው በተረክ አርባ አንድ "ነገደ ወይጦ ታንኳን ከደንገል ወፍጮን ደግሞ ከድንጋይ ለመጀመሪያ ጊዜ ሰርተዋል" (ካሴት ቁጥር 17(ሀ)፣ ግንቦት 22 ቀን 2003፣ ባህር ዳር) ይላል።

ታንኳ የተጀመረበትን ምክንያት በተመለከተ በተረክ አርባ ሁለት "አባቶቻችን ታንኳ ስራ የጀመሩት በየቦታው ያሉትን የማህበረሰብ አባላት ለማገናኘት በማሰብ ነው። ሌላው ደሞ የብረት መደሻ እንዳሁኑ ሳይመጣላቸው ድንጋዩን በድንጋይ ጠርበው የእህል ወፍጮ ፈልስመዋል።" (ወለላው፣ ካሴት ቁጥር 17(ሀ)፣ ግንቦት 22 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)። በማለት ይናገራል። ሰሎሞን በበኩሉ ታንኳን ለመጀመራቸው መነሻ ነው ተብሎ የሚተረከውን በተረክ አርባ እንደሚከተለው ይገልፃል፣

የቆዩ አባቶች ከአንዱ አካባቢ ወደ ሌላው አካባቢ ለመሄድ መጓጓዣ ነገር ለምን አንሰራም? እያሉ ሲያስቡ እያለ ደንገል ተነቅሎ በባህር ላይ ሲንሳፈፍ ያዩታል፣ አንዳንዴም እነሱ ሊያድኑ ሲሄዱ ወይም ደንጊያው ላይ ሆነው ሲቆሙ ያንሳፍፋቸዋል። ከዚያም ይህን ነገር በብዛት ብናስረው ሰው ሊይዝ ይችላል የሚል ሀሳብ ይመጣባቸዋል። በሂደትም በደንገል ታንኳ የመጀመሪያ ትራንስፖርታቸውን ጀመሩ፣ ሰው ሲሞትም በታንኳ መላላክ ጀመሩ፣ አደኑንም በእግር እየዞሩና ዱር ይዘው እየቆሙ ከማደን ይልቅ በታንኳ ማደኑ የተሻለ አማራጭ ሆነላቸው። ከሌላ ቦታ ያደኑትንም አውሬ ለማጓጓዝ ተጠቀሙበት። ሰውም ሲያጓጉዙና ሰውንም ሲድሩ በእግር መሄዳቸው ቀርቶ በታንኳ አደረጉት። በታንኳ ሲጓዙ ያያቸው የአካባቢው ማህበረሰብም "እንዴ እነዚህ ሰዎች እንዴት በውሃ ላይ ይሄዳሉ?" እነዚህ ሰዎችማ በቃ መላኮች እንጂ ሰዎች አይደሉም ይሉ ነበር (ካሴት ቁጥር 10(ሀ)፣ ግንቦት 8 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)።

ይህ ተረክ በአካባቢው የታንኳ ስራ እንዴት እንደተጀመረ፣ ማን እንደሰራው፣ ለምን አገልግሎት መዋል እንደቻለና የአካባቢው ማህበረሰብ አዲሱን የፈጠራ ስራ በመመልከታቸው እንዴት እንደተገረሙ በሚያሳይ መልኩ የቀረበ ነው።

በመሆኑም ይህ ተረክ የነገደ ወይጦ ማህበረሰብ አባላት ከተማን በመመስረትና አዲስ የቴክኖሎጂ ውጤት በመፍጠር ከሌላው ማህበረሰብ የተሻለ አቅም እንደነበራቸው ለማሳየት በሚል የቀረበ ይመስላል። በዚህም የማህበረሰቡ አባላት አሁን በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ቢኖሩም፣ የቆዩ አባቶቻቸው ከሌላው የአካባቢው ማህበረሰብ ይልቅ የተሻለ አቅም እንደነበራቸው ለመግለፅ ታስቦ ይሆናል።

በሌላ መልኩ አሁንም ታንኳን እና የድንጋይ ወፍጮን በቀዳሚነት በመስራትና ባለቤቶቹ እነርሱ እንደሆኑ፣ ከእነርሱ ውጭ ሌላ አቅም ያለው ሰው እንደሌለ እንዲያምኑ የሚያደርግ ሊሆን ይችላል።

## 4.7. ነገደ ወይጦና እርግማን

ነገደ ወይጦ በዝቅተኛ ኑሮ ላይ የሚገኙ የማህበረሰብ ክፍል ናቸው። በተለይ ኑሯቸው የተመሰረተው በአሳ ማስገር፣ የድንጋይ ወፍጮ በመውቀር፣ ከደንገል ታንኳ፣ ስፌት፣ ለአጥር የሚሆን በመስራት፣ የማገዶ እንጨት ለከተማው ህዝብ በማቅረብ ላይ ነው። በዚህ ዝቅተኛ ገቢ በሚያስገኝ ስራ ላይ ተሰማርተው መኖራቸውና ህይወታቸው እንደ አካባቢው ማህበረሰቦች የተሻለ ደረጃ ላይ አለመድረሱ የማህበረሰቡ አባላት የቆየ "እርግማን" ስላለበት ነው ብለው ያምናሉ።

በተለይ ስለአመጣጣቸው በሚያቀርቡት ተረክ ላይ "ሙሴ እስራኤላውያንን ከፈርኦን ጭቆና ነፃ ለማውጣት ከምድረ ግብፅ ወጥቶ ባህረ ኤርትራን ሲሻገር በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ከሙሴ ጋር አንሄድም በማለት ጥቂት ሰዎች አፈንግጠው ሲቀሩ 'ብኩን ሁኑ' ተብለው ተረግመዋል በማለት ይናገራሉ (ጅብሪል፣1975፡29)፡፡

በተመሳሳይ ደግሞ በተረክ አርባ ሦስት በነብይ ሙሳ ዘመን ከግብፅ ተነስተው ለጦርነት ሲሄዱ ከትልቅ ወንዝ ላይ ደረሱ፤ ሙሳም የኔ ተከታይ የሆናችሁ ከፊል ከፊል ውሃ ጠጥታችሁ ተከተሉኝ ብለው ሲያዙ፣ ከፊሉ ሰራዊት የተፈቀደለትን ያህል ውሃ ሲጠጣ፣ ከፊሉ ግን ከተፈቀደው በላይ ብዙ ጠጣ፡፡ ትዕዛዝ ያከበሩት ከመሪያቸው ጋር መሄድ ሲችሉ፣ ትዕዛዝን ሳይቀበሉ ብዙ የጠጡት ግን ሆዳቸው ከበዳቸውና በዚያው በነበሩበት ቦታ ቀሩ፡፡ ሙሳም ጦሩ ተገዞ ከማደሪያው ሲደርስ ቆጠራ እንዲደረግ ሲያዙ ብዙ ውሃ የጠጡት እንደቀሩ አወቁ፡፡ ሙሳም ወደኋላ ተቋርጠው የቀሩትን 'አትብዙ አትነሱ፤ አታግኙ አትጡ' ብለው ረገሟቸው (ጅብሪል፣ ካሴት ቁጥር 18(ለ) ግንቦት 28 ቀን 2003፣ ባህር ዳር) በማለት በወቅቱ በሙሴ(ሙሳ) የተረገሙት የሰራዊቱ ክፍል የወይጦ ማህበረሰብ አባቶች እንደሆኑ ይናገራል፡፡

በተመሳሳይ ወለላውና ስንታየሁ በተረክ አርባ አራትና አርባ አምስት "የማህበረሰቡ የቀድሞ አባቶች መረገማቸውን ገልፀው እርግማኑ 'አትጡ አትንጡ፣ የምትይዙት ሁሉ ብትንትን ይበል፣ ዕለታዊ ጥቅማችሁን ብሉ ጠጡ ግን እርስ ብርሳችሁ ተዋደዱ፤ ተፋቀሩ' መባሉን" ይጠቅሳሉ (ካሴት ቁጥር 17(ሀ)፣ ግንት 22 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)፡፡

እነዚህ ተረኮች ማህበረሰቡ ለምን እስካሁን ድረስ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ እንደሚኖር መነሻ ምክንያቱን ለማሳየት የቀረቡ ይመስላል፡፡ ማህበረሰቡም የሚይዙት ነገር እንደማይባረክ፣ ከማህበረሰቡ አባላት ውስጥም ትልቅ ቦታ የሚደርስ ሰው እንደሌለ እንደማሳመኛ አድርገው እንዲቀበሉት፤ እንዲሁም እስካሁን ድረስ ብዙም ያልተቀየረው የማህበረሰቡ የአኗኗር ስርዓት እንደ መርህ የሚከተሉት ህይወታቸው የዕለት ተዕለት የሆነው፤ የዕለት ሰርተው የዕለት መብላት እና የጋርዮሽ ህይወት እንዲኖሩ ያደረጋቸው ይመስላል፡፡ ህይወታቸው የዕለት ጉርስ ላይ የተመሰረተ መሆኑ ከእርግማኑ የመጣ ነው ብለው እንዲያምኑ ሊያደርግ ይችላል፡፡ በሌላ መልኩ ግን የእርስ በእርስ መተጋገዝና መዋደድ እንዲኖር በማድረግ በኩል ተረኩ የራሱ ድርሻ ይኖረዋል፡፡

## 4.8. ነገደ ወይጦና ውሃ

የነገደ ወይጦ ማህበረሰብ አባላት በጣና ሀይቅ ዙሪያና ወደ ሀይቁ በሚፈሱ ወንዞች ዳርቻ እንደሚኖሩ በምዕራፍ ሁለት ለመጥቀስ ተሞክሯል፡፡ አባላቱ ከጥንት ጀምሮ በአያት በቅድመ አያቶቻቸው እንደሚደረገው በሀይቅና በወንዞች ዳርቻ በመኖር ከውሃና ከአካባቢው የሚያገኟቸውን ነገሮች እየተመገቡ ይኖራሉ (ታፈሰ፣ 1978፡3)፡፡

በተለይ ኑሯቸው የተመሰረተው አሳ በማስገር፣ ከሀይቁ ውስጥ የሚገኙ ድንጋዮችን በመጥረብ የእጅ ወፍጮ በመስራት፣ ታንኳና የቤት ቁሳቁስ ከደንገል በመስራት፣ ለምግብነት የሚያገለግሉ እንደ ጉማሬ፣ አምባዛ የመሳሰሉትን የውሃ ውስጥ እንስሳትን በማደን፣ ወዘተ. ላይ በመሆኑ ውሃ በማህበረሰቡ ዘንድ የተለየ ቦታ ይሰጠዋል፡፡ በመሆኑም ቃላዊ ዝርው ተረኮቻቸውና ባህላዊ ስርዓታቸው የተመሰረቱት ከውሃ ጋር በተያያዘ ነው፡፡ በዚህ ክፍልም ቃላዊ ዝርው ተረኮቻቸውንና ባህላዊ ስርዓታቸውን ከውሃ ጋር እንዴት አያይዘው እንደሚያቀርቧቸው ለማሳየት ይሞከራል፡፡

ማህበረሰቡ 'ወይጦ' ስለመባላቸው ሲናገሩ ስያሜውን በተደጋጋሚ ከውሃ ጋር ያገናኙታል፡፡ ይህን በተመለከተ በተረክ ስድስት ሙሀመድ ነገደ ወይጦ 'ወይጦ' ተብሎ የተሰየመው ነብይ ሙሳ በግብፅ ምድር የነበሩትን እስራኤላውያን ይዞ ወደ ከነአን ምድር ለመመለስ ጉዞ በሚያደርጉበት ጊዜ ለተከታዮቹ እፍኝ ውሃ እንዲጠጡ፣ ከዚያ በላይ ግን እንዳይጨምሩ ሲያዝ፣ የተወሰኑት ግን ከታዘዙት በላይ በመጠጣታቸው "እረ ብዙ ጠጡ፣ እየጨመሩ ጠጡ" ብለው ሲሉ በሚሰሙበት ጊዜ ዘወር ብለው ቢያዩ እየጠጡ፣ "አንተ ዋጠው" ብለው በሚሉ ጊዜ "እረ ወይጦ" የሚለው ስም መውጣቱን ይናገራል (ካሴት ቁጥር 6(ለ)፣ ግንቦት 6 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)፡፡ ይህ ደግሞ ወይጦ የሚለው ስያሜ መነሻ ከውሃ ጋር የተያያዘ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

ሌላው ደግሞ የነገደ ወይጦ መነሻው ከግብፅ እንደሆነ ገልፆ "ግብጥን አድርገው አባይ ለአባይ እንደመጡ" በተረክ አስራ ስድስት ይናገራል (ጅብሪል፣ ካሴት ቁጥር 1(ሀ)፣ ሚያዝያ 30 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)፡፡ ይህ ደግሞ ማህበረሰቡ ከአመጣጣቸው ጀምሮ ከውሃ ጋር የተሳሰረ እንደነበር የሚያሳይ ነው፡፡

የነገደ ወይጦ ማህበረሰብ የነብዩ ሙሴን ትዕዛዝ አክብረው የተፈቀደላቸውን እፍኝ ውሃ ብቻ ባለመጠጣታቸው የተነሳም "ኑሯችሁ ውሃ ለውሃ ይሁን" ብለው እንደረገሟቸው (ሰይዴ፣ ካሴት ቁጥር 18(ለ)፣ ግንቦት 28 ቀን 2003፣ ባህር ዳር) በተረክ አርባ ስምንት ይጠቅሳል፡፡

ይህ ደግሞ የማህበረሰቡ አባላት ህይወታቸው ከውሀ ጋር የተሳሰረው በዚህ ምክንያት ነው ብለው እንዲያምኑ ሲያደርግ ይችላል፡፡ በተለይ አቢናዝ የሚባለውን ባህላዊ የአምልኮ ስርዓት ከንፈሮ አባይ ላይ የሚያካሂዱ ሲሆን፣ የዚህ ምክንያቱ "ይህ ቆሌ ወይጦዎች እንደ ጠባቂ አምላካቸው አድርገው የሚቆጥሩት መሆኑንና ለእነሱ የእለት ተእለት ተግባር መሳካት ወሳኝ ሚና ያለው መሆኑን ስለሚያምኑ ነው" (ምስጌ፣1979:10) በማለት የነገደ ወይጦ ማህበረሰብ ከውሃ ጋር ያላቸውን ትስስር ለማሳየት ሞክሯል፡፡ ከዚህ በመነሳት የነገደ ወይጦ ማህበረሰብ በተረኮቻቸውና በባህላዊ ስርዓታቸው ለውሃ ትኩረት የሚሰጡ መሆኑን ማየት ይቻላል፡፡

በአጠቃላይ የነገደ ወይጦ ማህበረሰብ ስያሜያቸውን፣ አመጣጣቸውን፣ አምልኳቸውን፣ የስራ ባህላቸውንና ከውሃ ጋር ያላቸውን ትስስር በተመለከተ በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ ዝቅ አድርገው ሲያዩአቸው ሲሞክሩ ስያሜያቸው ከነገዳቸው እንደመጣ፣ አመጣጣቸውም በታሪክ ከሚታወቁት ነቢያትና ነገስታት እንደሚወጣ፣ በስራ ባህልም ከአካባቢው ማህበረሰብ ይልቅ አዳዲስ ቴክኖሎጅዎችን በመፍጠርና ከተማን በመመስረት ቀዳሚና በአምልኳቸውም ለፈጣሪያቸው የታመኑ እንደሆኑ በመጥቀስ በዝቅተኛ ስራ ላይ የተሰማሩትና ጥሪት የማይዙት በነብዩ ሙሴ በመረገማቸው እንደሆነ በማሳየት ተረኮቻቸውን በአካባቢው ማህበረሰብ ከሚደርስባቸው ጫና ለመከላከልና ራሳቸውንም አፅንቶ ለማቆያት የሚጠቀሙባቸው ይመስላል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## የነገደ ወይጦ ማህበረሰብ የሚያከብሯቸው ባህላዊ ስርዓቶች ገለፃ

በዚህ ምዕራፍ የነገደ ወይጦ ማህበረሰብ አባላት የሚያከብሯቸው የአቢናዝ፣ የግርዛትና የሰርግ ባህላዊ ስርዓቶች እንደ ቅደም ተከተላቸው ይተነተናሉ።

### 5.1. አቢናዝ

አምልኮታዊ ስርዓቶች (Sacred Rituals) መንፈስን ወይም ልዕለ ተፈጥሯዊ አለሙን ከሚያምኑት ቡድኖች ወይም ማህበረሰቦች ጋር የተገናኘ እንደሆነ ይነገራል (Sims,2005:102)። ሰዎች እነዚህን ስርአቶች የሚያካሂዱት ከበሽታ ለመፈወስ፣ ዘርን ለማብዛት፣ ጠላትን ድል ለማድረግ፣ የሰዎችን ማህበራዊ ደረጃ ለመለወጥ፣ ከኃጢአት ለመንጻትና መጭውን ጊዜ ለመተንበይ ስለሚጠቀሙ ነው (Ray,1976:78)። ለዚህ ጥናት የተመረጠው የነገደ ወይጦ ማህበረሰብም በየአመቱ ወደ ከንፈሮ አባይ በመሄድ አቢናዝ የሚባል አምልኮታዊ ስርዓት ይፈጽማል።

አቢናዝ ወይም ኑር አቢናዝ የሚሉት አንዳንዶቹ አባይን እንደሆነ ሲገልፁ፣ የተወሰኑት ደግሞ አባይኛ ከሚባል ጎሳ ኑር አቢናዝ የሚባሉ ሼህ አባይ ዳር ሄደው መስጊድ ሰርተው ይኖሩ እንደነበርና ስያሜው የተወሰደው ከአሳቸው ስም መሆኑን፣ አሁንም በአሉ የሚከበረው እሳቸውን ለማዘከር እንደሆነ ይጠቅሳሉ። በተመሳሳይ ደግሞ አቢናዝ የሚለው ቃል የተወሰደው አቢናጆ ከሚባለው የማህበረሰቡ መሪ እንደሆነና አሟሟቱ በውሃ ላይ ስለነበር ባህላዊ ስርዓቱም መሪያቸውን ለማክበር እንደሆነ ይነገራል (Solomon,2006:71)።

በሌላ መልኩ አቢናዝ ጊዮን የሚባል ጅኒ ሲሆን የጅኖች ሁሉ የበላይ መሆኑን፣ የነገደ ወይጦ ማህበረሰብ አባላትና ጊዮን/ጅኒዎቹ/ "የናንተ ሰው የሆነውን ላልነካ፤ ለእኛ ደግሞ የምጠይቃችሁን ሁሉ ልታደርጉ" በማለት ስምምነት ላይ በደረሱት መሰረት በአሉን ማክበር እንደጀመሩ ይጠቅሳሉ (ሙሀመድ፣ ካሴት ቁጥር 14(ለ)፣ ግንቦት 12፤ ሰሎሞን፣ ካሴት ቁጥር 10(ለ)፣ ግንቦት 8 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)።

ስርአቱ የሚፈጸመው በአመት አንድ ጊዜ የክርስቲያኖች አብይ ፆም ሲገባ የቅበላ ቀን ወደ አባይ ወንዝ በመውረድ ከንፈሮ አባይ (አባይ ከጣና ከሚወጣበት) ላይ ነው። የበአሉ አከባበርን በተመለከተ ለምን በክርስቲያኖች ፆም መያዣ ቀን እንደሚከበር ሲጠየቁ የሚያቀርቡት ምክንያት ማህበረሰቡና አቢናዝ (ጅኑ) በተደራደሩበት ጊዜ የወሰኑት እንደሆነ እና በሁለት ወር ፆም አባይ ላይ ደም እንዳይፈስ ልክ ፆሙ ሲፈስክ ደም ማፍሰስ እንደሚችሉ ከጅኒው ጋር በተስማሙት መሰረት እንደሆነ ይገልጻሉ። ሆኖም በአብይ ፆም ወቅት በአባይ ላይ ደም የማያፈሱት ወይም መስዋዕት የማያቀርቡት ምናልባት በአካባቢው የሚኖረው ማህበረሰብ በአብዛኛው የክርስትና እምነት ተከታይ ስለነበሩና በፆም ወቅት ሥጋ ስለማይበሉ ወይም ስለማያርዱ ከብዙሃኑ ላለመለየት ፈልገው ይሆናል። በሌላ መልኩ ተጠኝ ማህበረሰቡ ጉማሬና ሌሎች እንደ ርኩስ የሚቆጠሩ የውሃ ውስጥ እንስሳትን በመብላታቸው መገለል እንደደረሰባቸው ሁሉ በአብይ ፆምም አርደው ቢበሉ የበለጠ ይጠሉናል ብለው ክርስቲያኑ ለቅበላ በሚያርድበት ቀን የእነርሱም ቅድመ አያቶች አምልኮታዊ ስርአታቸውን ሊፈፅሙ ተስማምተው ሲያከብሩት ቆይተው ሊሆን ይችላል። ከንፈሮ አባይ ላይ ማክበራቸው ደግሞ ቦታው ከ17ኛው ክፍለ ዘመን አስቀድሞ ዋና የንግድ መተላለፊያ እያለ በማህበረሰቡ ይዞታ ስር የነበረና በሐይቁ ላይ የሚያልፈውን ነጋዴም ከጭነቱ ጋር በማሻገር፣ ግብርም በማስከፈል ገቢ ያገኙና የጎሳ መሪያቸው የነበረው ነጋድራሱም በቦታው ላይ ያስተዳድር ስለነበር (ምስጌ፣1979:3) በዘመኑ የአቢናዝን አምልኮታዊ ስርዓት ለማካሄድ ከዚህ ቦታ የተሻለ ባለመኖሩ ይሆናል።

የአቢናዝን በአል ለማክበር ሁሉም የማህበረሰቡ አባላት እንደአቅማቸውና እንደፍላጎታቸው ብር ያዋጣሉ። አቅሙ የሌለው ሰውም እንዲያዋጣ አይገደድም፤ አቅሙ ያለው ደግሞ ከተወሰነው የገንዘብ መጠን በላይ እንደፈለገው ማዋጣት ይችላል። በተዋጣው ብር በድርድሩ መሰረት አንድ ያልሸና ወይፈን ይገዛል። በአሉን ለማክበር ከማህበረሰቡ አባላት ውስጥ ትላልቅ ሰዎች (አባጋሮች) ወይም ኃላፊዎች ይመረጣሉ። እነዚህ የተመረጡ ሰዎች ከማህበረሰቡ ገንዘብ በመሰብሰብ፣ ወይፈን በመግዛት እና ሌሎች ጉዳዮችን ያስተባብራሉ። ከዚያም የበአሉ ቀን ሲደርስ ወንድ የማህበረሰቡ አባላት ከያሉበት ቦታ በዓሉ ወደ ሚከበርበት ቦታ ይሄዳሉ። ባህር ዳር ከተማ የሚኖሩት የማህበረሰቡ አባላት ከጠዋት 12 ሰዓት ጀምሮ በእግራቸው ወደ ቦታው የሚሄዱ ሲሆን፣ ከሌላ አካባቢ የሚመጡት ደግሞ በታንኳ ይመጣሉ። በዚህ በአል ላይ ሴቶች የማይገኙ ሲሆን፣ እንዲሟላላቸው የሚፈልጉት ነገር ካለ ግን ስለታቸው እንዲሰማላቸው፤

እንዲስምርላቸው በበዓሉ ላይ ፀሎት እንዲደረግላቸው መልዕክት ይልካሉ፤ እቅም ያላት ሴት ደግሞ ጀባታ (ስጦታ) ብላ ዶሮ ትልካለች። ሴቶች በአቢናዝ አምልኮታዊ ስርዓት አለመገኘታቸው ማህበረሰቡ የእስልምና እምነት ተከታይ በመሆኑ ሴቶቻቸው በቀብር ስርዓት እንደሚከለከሉት ሁሉ በዚህ ቦታም ላይ ተከልክለው ይሆናል ወይም "አቢናዝ ለሴቶች አይፈቅድም" ከሚል እምነት የመነጨ ይሆናል። በሌላ መልኩ ሴቶች በወር አበባ ምክንያት ሊጎድፉ ወይም ንጹህ ላይሆኑ ስለሚችሉ፣ አቢናዝን ላለማስቀየምና በንጽህና ሆኖ ለመለማመን ከሚል እምነት ይሆናል።

በዓሉን ለማክበር ሲመጡ ከቅርብ አካባቢ የሚመጡ ሰዎች እያንዳንዳቸው ሁለት ሁለት እንጀራ፣ ጨው (በአካባቢው አጠራር አዋዜ/ድቁስ)፣ አሻቦ (ጨው ለማለት ነው)፣ ዘይት እና ጫት ይዘው ይመጣሉ። ሁለት ሁለት እንጀራ የሚሆነው ከሩቅ ለሚመጡ የበዓሉ አክባሪዎች የሚበሉት እንዲሆን በማሰብ እንደሆነ ይናገራሉ። ከዚህ በተጨማሪ የዳጉሳ ቂጣ በኑግ ተቀብቶ ይመጣል። ያልሸናውንም ወይፈን የሚባርከው አባጋሩ ነው። ይህ የሚደረገው ያልሸና ወይፈን እና በኑግ የተቀባ የዳጉሳ ቂጣ እንዲያቋድሱት በጠየቃቸው መሰረት ነው። ሆኖም ያልሸና ወይፈን የሚያርዱበት ምክንያት በመጽሐፍ ቅዱስ ያልሸና ወይም ከላም ያልደረሰ ተባት (ወይፈን) እንዳልረከሰ ወይም ነውር እንደሌለበት ስለሚቆጠር ለፈጣሪያቸው መስዋዕት ያቀርቡ እንደነበረው ሁሉ (ዘሌ.1፤3) ንጹህ የሆነውን መርጠው ለአቢናዝ ማቅረባቸው ከማህበረሰቡ ጋር የገባውን ስምምነት እንዳያፈርስና የሚለምኑትንም ቶሎ እንዲሰማቸው በማሰብ ይመስላል። አንድም ንፁህ ስለሆንህ ንፁህ ነገር አቅርበንልሃል ለማለት ይሆናል።

ከተለያየ አካባቢ በአሉ ወደ ሚከበርበት ቦታ የሚመጡት የበዓሉ ታዳሚዎች ከተሰባሰቡ በኋላ ከጠዋቱ ሁለት ሰዓት ሲደርስ የተሰባሰቡት እድምተኞች (በተለይ ከባህር ዳር ከተማ የሚመጡት የማህበረሰቡ አባላት) የስራ ድርሻ ክፍፍል ያደርጋሉ። በስራ ክፍፍሉ ሽማግሌዎች እና ከሩቅ ቦታ (ከሌላ አገር) የሚመጡት አይመደቡም። የሽማግሌዎቹ ድርሻ ፀሎት ማድረግ ነው። ሽማግሌዎቹ/አባጋሮች ፀሎት ካደረጉ በኋላ በሬው ይታረዳል። የበሬውን ደም ውሃው ላይ ነው የሚያፈሱት። ከዚያ እንደየምድባቸው በሬውን የሚገፉና ብልቱን የሚያዘጋጁት ስራቸውን እንዲሰሩ ይደረጋል፤ ሌሎቹ ለማብሰያ የሚሆን እንጨት ይለቅማሉ፤ ወጣቶቹ ለምግብ ማቅረቢያ የሚሆን ለምለም ቅጠል ይቆርጣሉ። ወጥ የመስራት ልምድ ያላቸው ደግሞ ወጥ ይሰራሉ። ወጥ

የሚሰራው በበርሚል ነው። ሽማግሌዎቹ ተሰብስበው በመቀመጥ ጫት እየቃሙ ዱአ (ጸሎት) ያደርጋሉ።

የወይፈኑን ደም ውሃው ላይ ማፍሰሳቸው አቢናዝ በውሃው ውስጥ አለ ብለው ስለሚያምኑ እርሱ ይጠጣዋል ብለው ይሆናል። በሌላ መልኩ በመጽሐፍ ቅዱስ በዘመነ ኦሪት ለፈጣሪያቸው መስዋዕት ያቀረቡትን ወይፈን ወይም የበግ ጠቦት ሥጋ በማቃጠልና ደሙን በማፍሰስ መስዋዕት ያቀርቡ እንደነበረው (ዘሌ.4፥7) ሁሉ የማህበረሰቡ አባላትም ወደ ውሃው ማፍሰሳቸው ለአቢናዝ መስዋዕት እያቀረቡ ይሆናል።

ከሩቅ አገር የሚመጡት ጠዋት ስለማይደርሱ በመጡበት ሰዓት ዱለት ወይም ስጋ ተጠብሶ ይሰጣቸዋል። እስከ አስር ሰዓት ወይም ወጡ ተሰርቶ እስከሚያበቃ ድረስ ፀሎት እየተደረገ፣ ዱለትና ስጋ እየተጠበሰ ይበላል። የዳጉሳ ቂጣውን የተወሰነውን ለውሃው ካቋደሱ በኋላ እነሱ ይበላሉ። የሚበሉትን ነገር ቅድሚያ ለውሃው ያቋድሳሉ። አስቀድመው ማቋደሳቸው በውሃው ውስጥ ያለው አቢናዝ (ጅን) ከመቋደሱ ወይም ከመብላቱ በፊት እነርሱ ቢበሉ ይቀስፈናል፤ ይቀጣናል ወይም ከአባቶቻቸው ጋር የገባውን ስምምነት ያፈርስብናል ከሚል እምነት ይመስላል።

አስር ሰዓት ሲሆን ግን ቅጠሉ በየፊታቸው ይነጠፍና ሲዘጋጅ የዋለው ምግብ ይበላል። ምግብ ከተበላ በኋላ ፀሎት ተደርጎ ወደ ቤታቸው መሄድ የሚፈልጉ ካሉ ይሄዳሉ። የሚያድሩት ሰዎች ግን በዚያው ይቆያሉ። የሚያድሩት ሰዎች ሌሊቱን ሙሉ ሳይተኙ ጫት ሲቅሙና ፀሎት ሲያደርጉ ያድራሉ። ከንፈሮ አባይ ላይ ሌሊቱን በሙሉ ሳይተኙ ጫት ሲቅሙና ጸሎት ሲያደርሱ ማደራቸው ምናልባት ቀን ሀሳብ ስለማይሰበሰብ በሌሊት በተመስጦ ለመለመን ከመፈለግ ይሆናል። አንድም ሌሊት በተሰበሰበ ህሊና መጸለዩ አቢናዝ ልመናችንን የበለጠ ይሰማናል ከሚል ሊሆን ይችላል።

በሌላ መልኩ ቀን በተለያየ ሥራ ምክንያት በአካባቢው ሕዝብ ስለሚበዛ እና በሌሊት ግን ሐይቁ ላይ ሰው ስለማይዘዋወር ከጅኑ ወይም አቢናዝ ጋር በቀላሉ ለመገናኘት ይቻላል ከሚል ይሆናል።

በቀጣዩ ቀን ጠዋት የተረፈውን ከበሉ በኋላ ቡና ይፈላል፤ ከዚያም ፀሎት አድርገው ተመራርቀው፣ ለሚቀጥለው አመት በሰላም እንዲያደርሳቸው ተመኝተው እንዲሁም

የሚፈፀምላቸው ጉዳይ ካለ እንዲሳካላቸው ተስለው የበዓሉ ፍፃሜ ሲሆን፣ ለበዓሉ ተብሎ ከተዘጋጀው ምግብ የተረፈውን በሙሉ ውሃው ውስጥ ይጨምራሉ፡፡ የበሬውን ቆዳም ውሃው ውስጥ ይጥላሉ፡፡ ምንም ነገር ቢተርፍ ወደ ቤት አይወስድም፡፡ ይህንንም የሚያደርጉት ይዘውት ቢሄዱ፣ የውሀው ቆሌ እንዳይጣላቸውና ቆሌው አብሮ እንዳይሄድ ወይም በጎሳው ላይ መዓት ያመጣል ወይም ከአባቶቻቸው ጋር የገባውን ስምምነት ያፈርሳል ከሚል እምነት እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ አባይ ከጀነት ወይም ከገነት ተነስቶ የሚመጣ ውሃ ነው ተብሎ ስለሚታሰብ በዓሉን አክብረው ወደ ቤታቸው ሲመለሱ በእርጅና እና በተለያየ ምክንያት ወደ ቦታው ላልመጡ ወንዶችና ሴቶች ተህሊሊ /ፀበል/ ቀድተው ይሄዳሉ፡፡ ከቤት ያሉ ሰዎች ውሀውን ይጠጡታል፣ ይታጠቡበታልም፡፡

በአሉን ለማክበር ተብሎ የተዋጣው ብር ቢተርፍ ለሌላ ነገር በፍፁም አይውልም፡፡ ለሚቀጥለው አመት በአል ማክበሪያ ይሆናል፡፡ በዓሉን ለማክበር የሚታረደው በሬ ከአንድ በላይ መሆን የለበትም፡፡ የተዋጣው ገንዘብ ብዙ ቢሆንም፣ ወይም በዓሉን ለማክበር የሚመጡት ሰዎች ቁጥር ቢጨምርም ከአንድ በላይ አይታረድም፡፡ ይህም የሚሆነው ከአንድ በላይ እንዳይታረድ በመስማማታቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡

በዓሉን ለማክበር የሚሄድ ሰው ከፈለገ በግሉ ዶሮ ወይም በግ ይዞ በዛው ቀን ሊያቋድስ ይችላል፡፡ ፍላጎቱ ያላቸው ሴቶችም ከቤታቸው ሆነው ዶሮ በማረድ ያቋድሳሉ፡፡

የሁዳዴ ፆም ቅበላ በዓሉን ካከበሩ በኋላ በፆም ጊዜ ደም እንዳያፈሱ በተስማሙት መሰረት ማንኛውም የማህበረሰቡ አባል ፆሙ እስኪፈታ ድረስ ወደ አባይ በመውረድ ማቋደስ አይፈቀድም፡፡ ፆም ተፈትቶ የፋሲካ በዓል ከተከበረ በኋላ ስለቱ የሰመረላቸው ሰዎች በግላቸው የተሳሉትን ነገር በመያዝ ወደ አባይ ሄደው ያቋድሳሉ፡፡ አንድ ችግር ሲደርስባቸው አቢናዝ ወይ አባይ ብለው ሲጠሩት ለችግራቸው በፍጥነት መፍትሄ እንደሚሰጣቸው ሁሉ ስለታቸው ሰምሮ የተሳሉትን ካላስገቡ ወይም እያወቁ የሚያጓድሉ ከሆነ ይጣላናል፣ በውሻና በአንዳንድ ነገሮች ተመስሎ እየመጣ ይረብሸናል፣ በተለያየ ደዌም ይቀጣናል ብለው ያምናሉ፡፡

በአጠቃላይ በቅበላ እንዲካሄድ በአቢናዝ ትዕዛዝ መሰረት እንደሆነ መታመኑ፣ ሥርዓቱ በቀጣዩ ትውልድ እንዳይቋረጥና የሚካሄድበት እለትም ቅበላን ጠብቆ እንዲሆን በማድረግ በኩል አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡

በሌላ መልኩ ሥርኣተ አምልኮው የሚፈፀምበት ቦታ ከንፈሮ አባይ ላይ እንዲሆን፣ ያልሸና ወይፈን እንዲታረድ፣ ሴቶች በሥርዓቱ ላይ እንዳይሳተፉ፣ የወይፈኑ ደም ውሃው ላይ እንዲፈስ መደረጉ፣ ኑግ የተቀባ የዳጉሳ ቂጣ መቅረቡ፣ ከበዓሉ የተረፈው ምግብና የወይፈኑ ቆዳ ወንዙ ላይ መጣሉ፣ ሥርዓተ ጸሎት ሲደረግ መዋሉና መታደሩ ማህበረሰቡ ከአቢናዝ ጋር በገባው ስምምነት መሠረት እየተፈፀመ መሆኑ መታመኑ ሥርዓቱ መሰረቱን እንደጣለ እንዲቆይና በማህበረሰቡም ዘንድ የሚያቀርቡት መስዋዕት ሁሉ ዋጋ ያለው እንደሆነ እንዲያምኑ ሊያደርግ ይችላል።

## 5.2. የግርዛት ስርዓት

በነገደ ወይጦ ማህበረሰብ ባህል የወንድ ልጅ ግርዛት የሚፈፀመው በሁለት አይነት መንገድ ነው። አንደኛው ህፃኑ በተወለደ በሰባተኛው ቀን ሲሆን፣ በዚህ ቀን የሚፈፀመው የግርዛት ስርዓት ብዙም የተለየ ድግስ አያስፈልገውም፣ አቅም ከሌለ የቡና ቁርስና ከፈቀደ ደግሞ ዶሮ ወይም በግ ታርዶ ይፈፀማል። ሁለተኛውና በዚህ ጥናት ለትንታኔ የሚቀርበው ስርዓት ወላጆች ህፃኑን ሰባት ቀን ካለፈው በኋላ የሚያስገርዙበት ስርዓት ነው።

በማህበረሰቡ ዘንድ ለወንድ ልጅ የተለየ ቦታ ይሰጣሉ። በተለይ ደግሞ የበኩር ልጅ ወንድ ከሆነ የበለጠ ክብር አለው። ይኸውም ማህበረሰቡ ለአደን የተለየ ቦታ ስላለው፣ ወንድ ልጅ የአባቱን ፈለግ ተከትሎ አዳኝ ይሆናል ስለሚሉና ከባድ ስራ የሚሰራ ነው ብለው ስለሚያስቡ ነው። እንዲሁም ወንድ ከተወለደ ለአባቱ ገዳ (መከታ) ይሆናል። በተለይ ደግሞ ብዙ ወንድ ልጆችን የወለደ "ገዳዎቹን አየሃቸው ከእንግዲህ ማን ይነካዋል" ስለሚባል ነው። ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች ወንድ ልጅ ሲገረዝ ትልቅ ድግስ ይዘጋጃል። በተጨማሪም በድግስ ከተገረዘ ገዳይ፣ አዳኝ፣ ጀግና ይሆናል ብለው ያምናሉ።

በሰባት ቀኑ ሳይገረዝ የቀረ ህፃን ልጅ የሚገረዝበት አመት የተወሰነ አይደለም። ወላጆቹ አቅም አግኝተው መደገስ እስኪችሉ ወይም እስከ አስራዎቹ የእድሜ ክልል ድረስ ሳይገረዝ ሊቆይ ይችላል። ወላጆቹ አቅም አግኝተው ለማስገረዝ ሲያስቡ የግርዛቱን ቀን ይወስናሉ። አበልጅ ለሚሆኑት ሰዎችም ቅድመ ዝግጅት እንዲያደርጉ ልጁ የሚገረዝበት ቀን ይነገራቸዋል። ከዚያም ለድግሱ የሚሆኑ የተለያዩ ዝግጅቶችን ይጀምራሉ። በየሀገሩ ያሉ የማህበረሰቡ አባላት በግርዛቱ ቀን እንዲመጡ መልዕክተኛ ይላካል። ለግርዛት

አስር ሰዓት አካባቢ የተጠሩት እንግዶች ይደርሳሉ፤ ሴቶቹ ወደ ተጋበዙበት ቤት ሲመጡ ለመጠጫ የሚሆናቸውን ኩባያ ይዘው ይመጣሉ። ለድግሱ ተብሎ ዳስ ይጣላል። ከዳሱ መውጫ አጠገብ ሦስት ወይም አራት ወንዶች መሰብ ወርቅ፣ የስም ዝርዝር መፃፊያ ወረቀትና እስክርቢቶ ይዘው ይቀመጣሉ። ተጋባዦቹ በልተውና ጠጥተው ሲወጡ እንደየአቅማቸውና ለደጋሾቹ እንዳላቸው ቅርበት ስማቸውን እየተናገሩ ብር ይከፍላሉ። በእያንዳንዱ ማዕድ ስድስት ስድስት ሰው ይቀመጣል። አበልጆቹም ቀን የተሰራውን የዶሮ ወጥ ስድስት ሆነው የራሳቸውን ቤተሰብ ይዘው ይበላሉ፤ ይጠጣሉ፤ ይጨዋወታሉ። የተጠራው እንግዳ መቆየት እስከፈለገበት ሰዓት እየጠጣ ያመሸና ወደየቤቱ ይሄዳል። የማህበረሰቡ አባላት ስርዓቱ ለምን አስር ሰዓት አካባቢ እንደሚጀመር ሲጠየቁ ሁልጊዜ የግርዛት ስርዓት የሚፈፀመው ሰኞ ቀን ስለሆነ ሰኞ ደግሞ የስራ ቀን በመሆኑ የተጠሩት ሰዎች ስራቸውን እንዳይፈቱ በማሰብ መሆኑን ይገልፃሉ። አበልጆቹ ሲጫወቱ አምሽተው ውድቅት (እኩለ ሌሊት) ሲሆን፣ ወደ ቤታቸው ይሄዳሉ።

ማክሰኞ ጠዋት አበልጆቹ "ኑ ተጫወቱ" ተብለው ይላክባቸዋል። እነሱም አስር እንጀራ ይዘው ይመጣሉ። ሲበሉ፣ ሲጠጡና ሲጫወቱ ይውላሉ። አመሻሽ ላይ ወደ ቤታቸው ይሄዳሉ።

ረቡዕ ለአበልጆቹ ዶሮ ይታረድና "ኑ ምኑንም ምኑንም ስንጫወት አምሽተን እንለያያለን፤ አሽከሮችንም ቁስሉ አሟቸው ነው የዋለ" ተብሎ ይጠራሉ። ይህ የሚባለው ታመው ሳይሆን የተለመደ በመሆኑ ነው። መጥተው ሲጫወቱ ውለው መስነባበቻውን በልተው ጠጥተው ይሄዳሉ። ከዚህ ቀን በኋላ በዓል ሲሆን እየተጠራሩ፤ በሀዘኑም በደስታውም ይገናኛሉ። ሁለት ልጆች ተገርዘው ከሆነ የሁለቱም አበልጆች ሳይለያዩ እኩል ይጠራሉ። አበልጁም ለተገረዘው ልጅ እንደአቅሙ በአል በሆነ ቁጥር ያለብሳል። ልጁ አድጎ ሲዳር የሚዜዎቹን ድግስና የሙሽራውን ልብስ ይሸፍናል።

በድሮው ጊዜ አበልጅ የሚሆኑት ምንም ዝምድና የሌላቸው ሰዎች ተፈላልገው የነበረ ቢሆንም፣ በአሁኑ ጊዜ ግን ለባዕድ አናበላም በሚል ሰበብ የቅርብ ዝምድና ያላቸው ሰዎች ሁሉ አበልጅ መሆን ይችላሉ። ባሏ እንዲያቅፈው በማድረግ ሴቷ ወንድ ማንሳት ትችላለች። አበልጆቹ ከዚያ በኋላ ሌላ ልጅ ሲያስገርዙም ሆነ ሌላ ልጅ ሲድሩ ይጠራራሉ። የመጠራራት ስርዓቱ ግጥግጥ ይባላል። የልጁ ወላጆች ልጅ በዳሩ፣ ባስገረዙ ቁጥር የመጀመሪያ አበልጆቹን ለብቻ ደግሰው ይጠሯቸዋል፤ ስማቸውም ግቢዎች

ይባላሉ። ሁለት ሦስት አበልጅ ካለው ሁለት ሦስት ዳስ ይሰራና ለብቻቸው ደግሶ ይጠራቸዋል። የቆይታ ጊዜያቸውም ከሰባት ቀን እስከ አስር ቀን ይደርሳል። በቆይታቸውም ስለጋብቻቸው፣ ስለወደፊቱ ሲጫወቱ ይቆዩና ይሰነባበታሉ። አበልጁ በተራው ጠርቶ ይጋብዛል።

ወንድ ልጅ ሲወልዱ ስለሚያስገርዙ፣ እኔ ወንድ ልጅ ወልጄ የማስገረዝ ወግ ሊደርሰኝ ነው በማለት ይደሰታሉ። ሴት ልጅ ያላቸው ግን አስገርዘው መጥራት ስለማይችሉ "አንተ ሁልጊዜ እየዞርክ የሰው ድግስ መብላት ነው" ሲሏቸው ሚስታቸው ወንድ ልጅ ባለመውለዷ ይፀፀታሉ፤ ቤተሰባቸውም ቢሆን ሌላ ሴት ጋር ሄዶ እንዲወልድ ግፊት ያደርጋሉ። ወንድ አዳኝ ይሆናል፤ ደም ይመልሳል፣ መከታ ይሆናል ብለው ስለሚያምኑ እና በግርዛቱ እንደሌላው ደግሰው መጥራት ስለሚችሉ "ከሰው እኩል ያደርገናል" በሚል ሲወለድ ይደሰታሉ።

ማህበረሰቡ የግርዛት ስርዓቱን የሚያከብሩበት መነሻ ምክንያት የተለያየ ሊሆን ይችላል። የተገራዥ ቤተሰቦች በማህበረሰቡ ዘንድ ክብር የሆነውን ወንድ ልጅ መውለድ በመቻላቸው የግርዛቱን ቀን ጠብቀው ደስታቸውን ለማህበረሰቡ እየገለፁ ይሆናል ወይም በተለይ አባትዬው ከእንግዲህ በኋላ ገዳ ወይም መከታ የሚሆን ልጅ ወልጃለሁ፤ ማህበረሰቡ ወንድ ልጅ ለወለደ የሚሰጠውን ክብር ስጡኝ፣ በክፉ ያያችሁኝም ካላችሁ አጋዥና ደም መላሽ ልጅ ስለወለድኩ አይናችሁን ከእኔ አንሱ ለማለት ሊሆን ይችላል።

በሌላ መልኩ የግርዛት ስርዓት በመድመቁ ተገራዡ ልጅ የበለጠ ጀግና፣ ገዳይ ወይም የባህር ውስጥ አዳኝ ይሆንልኛል ከሚል እምነት ይሆናል።

ማህበረሰቡ የግርዛቱን ቀን ሰኞ ማድረጋቸውና ከነብዩ ሙሀመድ ልደት ጋር ማያያዛቸው ምናልባት የነብዩ ፀጋ ወይም በረከት ይደርሰዋል፤ በመንፈስ ይጎበኘዋል ከሚል እምነት ይሆናል። ወይም እንደ ነብዩ ለሃይማኖቱ ተቆርቋሪ፣ ጦረኛ ወይም ጀግና ልጅ ይሆንልናል ከሚል አስተሳሰብ የመነጨ ሊሆን ይችላል።

አበልጁ የተገራዡን ልጅ ደም በጣቱ ነክቶ በግንባሩ ላይ መቀባቱ ደግሞ የውህደት መፍጠሪያ ምልክት አድርገው በመውሰድ ከተገራዡ ልጅ ጋር የልጅና የአባት ያህል መዋሃዳቸውን ለማሳየት ይሆናል፤ ለዚህ አንዱ ማረጋገጫ "አበልጅ" የሚለው ቃል

ነው፤ "አበነፍስ" የሚለው ቃል "የነፍስ አባት" የሚል የአማርኛ አቻ ትርጉም እንደሚሰጠው ሁሉ አበልጅም "የልጅ አባት" የሚል ትርጉም ይኖረዋል፡፡ ይህም አበልጁ ለተገራገሩ የአባት ያህል ቦታ የሚሰጠው መሆኑን ያሳያል፡፡ ሁለተኛው አበልጅ የተገራገሩን ደም እየተቀባ "ከበኩር ልጅ አብልጬ ላየው" ብሎ የሚገባው ቃል ደም በግንባሩ መቀባቱ አባትነቱን ለማረጋገጫነት ማህተም ሊሆን ይችላል የሚለውን ሀሳብ ያጎላዋል፡፡

በተመሳሳይ የአበልጁ ሚስት ተገራገሩን በጀርባዋ ማዘሏ ለአካለ መጠን እስክትደርስ ድረስ የመንከባከብ ድርሻ የወላጆቹ ብቻ ሳይሆን የእኔም ጭምር ነው ለማለት ይሆናል፡፡ ቁስሉን ማጠቧም በችግር ጊዜ አግዝሃለሁ፤ በጉዳትህ ከጎንህ እቆማለሁ ለማለት ይመስላል፤ በቅቤ መቀባቷ ደግሞ ቅቤ ቁስልን ያለዝባል ወይም ህመምን ያስታግሳልና እኔም አካላዊም ሆነ ልቦናዊ ቁስል ቢደርስብህ አክምሃለሁ፤ በአጠቃላይ ለበኩር ልጅ የማደርገውን እንክብካቤ ሁሉ አደርግልሃለሁ ለማለት ይሆናል፡፡

ለልጁ በግርዛቱ ወቅት አበልጅ ማስፈለጉ ደግሞ አንድም ከወላጆቹ ባሻገር ሌላ አጋዥ በመፈለግ ወይም አበልጆቹና የልጁ ወላጆች ለመዛመድ ከመፈለግ ሊሆን ይችላል፡፡

በአጠቃላይ ለወንድ ልጅ በግርዛቱ ወቅት መደገሱ ልጁ ሲያድግ ጀግና ይሆንልናል ከሚለው በተጨማሪ ለወላጆቹ ወንድ ልጅ በመውለዳቸው በማህበረሰቡ ዘንድ ክብር እናገኛለን፣ የነብዩ ሙሀመድ በረከት ይደርሰዋል ብለው እንዲያምኑ ስለሚያደርጋቸውና ለልጁም በአበልጆቹ አማካይነት ከወላጆቹ በተጨማሪ አጋዥ ስለሚያስተላልፉለት ወላጆቹ ጥለነው ብንሞት ወይም አቅም ቢያቅተን ሌላ ረዳት አለው ብለው ህሊናዊ ዕረፍት እንዲያገኙ ያደርጋቸዋል ለማለት ይቻላል፡፡

## 5.3. የጋብቻ ስርዓት

በማህበረሰቡ ዘንድ ሁለት አይነት የጋብቻ ስርዓት ይፈጸማል፡፡ የመጀመሪያው በቤተሰብ ተፈላልጎ ልጅህን ለልጄ ተባብለው የሚያጋቡት ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ጥፊ ይባላል፡፡

ጥፊ የሚባለው የጋብቻ ስርዓት ልጁ ሊያገባት የከጀላትን ልጃገረድ በሚቀርቧት ሰዎች ፈቃደኛ እንድትሆን ያስለምናትና ፈቃደኝነቷን ሲያረጋግጥ ለመጋባት ይወስናሉ፡፡ ሁለቱ

ተጣማሪዎች ለመጋባት ከወሰኑ በኋላ ለቤተሰብ ሊያሳውቁ ይችላሉ። ከዚያ ለልጅቷ ልብስ ይሰፋላትና በጓደኞቿ አማካኝነት ይበረከትላታል። ልክ አመሻሽ ላይ ልጁ ወስዷት ያድራል። ቤተሰቦቿ ቀደም ብሎ ተነግሯቸውም ቢሆን እንደማያውቁ በመምሰል ልጅቷ ጠፍታናለች ብለው ሌሊት ላይ ይፈልጋሉ። የማያውቁ ከሆኑም በተመሳሳይ ፍለጋ ይጀመራል። ከዚያ ጎረቤት ጓደኞቿ ተሰብስበው እስኪ ቆዩ ምናልባት ከጓደኞቿ ጋር ሄዳ ይሆናል ወይ ደግሞ ባል ወስዷት ሊሆን ይችላል ይሉና ቤተሰቦቿን ለማረጋጋት ይሞክራሉ። ቤተሰቦቿም እንዴት እኛ ሳንጠየቅና ሳንደግስ እንደዚህ ይደረጋል ይላሉ። ከዚያ ካረጋጓቸው በኋላ ልጅቷ በጠፋች በቀጣዩ ቀን ጠዋት ሽማግሌዎቹ ወደ ወላጆቿ ቤት በመሄድ "ያው በቃ አንዴ ሆኗል፣ ሳያውቁ አጥፍተዋል እና ይቅር በሏቸው" በማለት ያግባባሉ። ወላጆቿም ማንን እንዳገባች ይጠይቃሉ። "ለምን እኛ ቀድመን አልተጠየቅንም" በማለት ያጉረመርማሉ። ከዚያም በኋላ "ተው እንደዚህ ነው፣ የነበረ ነው" ተብለው እንዲስማሙ ይደረጋል። በማግስቱ በሀይማኖት ስርዓት ስማኒያ ይታሰርና ጋብቻነቱ ይፀድቃል።

ይህ የጋብቻ አይነት በሴቷ ፍላጎት የተፈፀመ ስለሆነ ከጠለፋ ጋር የተያያዘ አይደለም፣ ስምምነት ያለው ጋብቻ እንዳይባል ደግሞ ብዙ ጊዜ በቤተሰብ ስምምነት ወይም ፈቃድ የሚፈፀም ሳይሆን ይችላል።

በወላጆች ምርጫ በሚፈጸመው የጋብቻ አይነት የመተጫጨቱ ሂደት የሚጀምረው በጋብቻ ለመተሳሰር የሚፈልጉ ወላጆች ገና ተረግዛ እያለች ሴት ከወለድሽ ለልጄ ይባባሉና ቃል ይገባባሉ። እናትዬዋ ሴት ከወለደች፣ ህፃኗ አንድ ወይም ሁለት አመት እንደፍላጎታቸው ሲሞላት ቃል አካፋች ይላካል። ቃል አካፋች ማለት ልጅቱ ስትወለድ ከወላጆቿ ጋር ያደረጉትን ቃል ኪዳን አንድ አመት ሲሞላት እንዲድሩልኝ "ሂዱና ጠይቁልኝ" ተብሎ የወንዱ እናት ወይ ጓደኛዋን ወይም ደግሞ ቤተሰብ የሆነ ሰው ትልካለች። የተላከችው ሴት ወደ ልጅቱ ቤተሰቦች ትሄድና የህፃኗን እናት "ልጅሽን ለልጄ በቃልሽ ፀንተሻል ወይ?" በማለት ትጠይቃለች። የህፃኗ እናትም "ከባሌ ጋር ልማከርና መልሱን አሳውቃለሁ" ትላለች። ባልዬውም ቢሆን ብዙ ጊዜ አይቃወምም፣ "ቃል ከገባሽ ምንም ችግር የለውም" ይባባሉና ቃል ይካፈታሉ ማለት ነው። ከዚህ መረዳት እንደምንችለው የሴቷ መብት ከፍ ያለ መሆኑንና ባልዬው ሳይሰማ ቃል ገብታ የልጇን ባል እስከመምረጥ የሚደርስ መብት እንዳላት ነው። ከዚያም በኋላ ሽማግሌዎች ይላካሉ፣ "እንደዚህ እንደዚህ ተባብላችኋል እና ሽማግሌ ሁኑ ተብለን ተልከን ነው

የመጣነው" ይላሉ። ቃል አካፋች በቡና በሴት ጓደኛ የሚጀመር ሲሆን፣ ሽማግሌዎች የሚላኩት ከዚያ በኋላ ነው። ቤተሰቦቿም "እኛ ቃል ገብተን ነበር፤ ምንም ችግር የለም እንመቻችና እንጠራችኋለን ቀን እንቋረጣለን" በማለት ቡና ከተፈላላቸውና ምሳ ከተጋበዙ በኋላ ይሄዳሉ። ከዚያ የህፃኗ ቤተሰቦች ይመካከሩና ሽማግሌዎቹ ጋር ለመነጋገር መልዕክት ይልካሉ። የሴቷ ወላጆች ድግስ ያዘጋጃሉ። ለሽማግሌዎች ዶሮ ይታረዳል። ሽማግሌዎቹ በዕለቱ የሚበሉት ዶሮ ብቻ ነው፤ በግም ወይም ፍየል ቢታረድ ለእንግዶች እንጂ ለሽማግሌዎች አይቀርብም። ከዚያም የጋብቻው ቀን ይቆረጣል። አብዛኛውን ጊዜ ለሰርግ የሚመረጠው ወቅት የክርስቲያኖች አብይ ፆም ግማሽ ከሆነ በኋላ ነው። ይህን ጊዜ የሚመርጡት በርካታ ክርስቲያኖች ስጋ ስለማያርዱ፤ ከብት እንደፈለጉ ስለሚያገኙና ይረክሳል ብለው ስለሚያስቡ ሲሆን፣ በተጨማሪም በዚህ ጊዜ ዝናብ በደንብ ስለማይጥል ቀንም ሆነ ማታ ለመጨፈር እንዲያመቻቸው ታስቦ ነው።

የሰርጉ ቀን ሲቃረብ ከዋዜማው ቀን ጀምሮ የሙሽራው ሚዜዎች ይሰበሰባሉ። ሚዜዎቹ ተሰባስበው ማታ ሲጨፍሩ ያድራሉ፤ ጠዋት በየቤቱ እየዞሩ "ሙሽራ መርቁ" እያሉ ያስመርቃሉ፤ በየቤቱ በሚዞሩበት ጊዜ እህልና ብር ይቀበላሉ። በሴቷም በኩል በተመሳሳይ ሙሽራ መርቁ እያሉ ይዞራሉ፤ ብር እና የተለያዩ ነገሮች ከየቤቱ ይቀበላሉ። ሙሽራው ከቤቱ ሲወጣ የተለየ ዘፈን ይዘፈናል። ዘፈኑ እየተዘፈነና ሚዜዎቹም እየጨፈሩ ሙሽራው ፀጉሩን ይላጫል። ከተላጨ በኋላ ነጭ ሻሽ ይጠመጥማል። ሲወጣ ሲል ዶሮ ያመጡና ከፊቱ ያቆማሉ፤ ከዚያ ሙቀጫ ቀርቦ ሁለት ሴቶች መውቀጫ ይይዙና ባዶውን እየወቀጡ የራሳቸው የሆነ ዜማ እየዘፈኑ ይዞራሉ። ሙሽራው ዶሮውንም አርዶ ተራምዶት እንደሄደ ሙቀጫው ጋር እንዲደርስ ስርዓቱ ያዛል። አንድ ሴት በዋርማ (ከቅል የተሰራ የጠላ መጠጫ) ድፍድፍ እንድትይዝ ይደረጋል፤ ሙቀጫው ጋር ሴቶች እየዞሩ ይዘፍናሉ። ከዚያም ዋርማውን ይቀበልና ሙቀጫው ውስጥ ይከተዋል። ሴቶቹም እየወቀጡ ይሰባብሩታል፤ እስከድፍድፉ እየወቀጡ እየዞሩ ይዘፍናሉ፤ ሚዜውም አብሮ ሎጋው ሽቦ እያለ እየዞረ ይዘፍንና ይሄዳሉ።

ልክ ከሰአት በኋላ ሙሽራው ወደ ሴቷ ቤት ይሄዳል። ቦታው ሩቅ ወይም ሀይቁን ተሻግሮ ከሆነ ስንቅ አይጫንም። ሙሽራው እና ሚዜዎቹ በሚያርፉበት ቦታ ሁሉ "የእገሌ ልጅ በዚህ ጊዜ ያገባል" ተብሎ ስለሚታወቅ ተደግሶ ይጠብቃቸዋል። በሚያርፉበት ሁሉ በየወደቡ ያሉ ሰዎች ወደቡ ላይ ይጠብቋቸውና አንዱ ቤት ገብተው ተደግሶ ይበላል፤ ይጠጣል። ሌላው ወደብ ሲደርሱም በተመሳሳይ ተቀብለው

ያስተናግዷቸዋል፡፡ ሙሽራዋን ይዞ ሲመለስም በተመሳሳይ ሁኔታ እንደ መጀመሪያው ተደግሶላቸው ይበላሉ፡፡

ሙሽራው ሙሽራዋ ቤት ሲደርስ ይዘፈናል፡፡ ሙሽራው የተቀመጡትን ሽማግሌዎች "እንዴት ዋላችሁ" ሲል፣ "ምንድን ነው? ምን ፈለጋችሁ?" ሲሏቸው፣ "አውራ ይዘን ባዝራ ፍለጋ መጣን" ይላሉ፡፡ "በሉ ትንሽ ቆዩ እድምተኛ በልቶ ያብቃ" ይባላሉ፤ በልተው ሲያበቁ ይገቡና ያመጡትን ጥሎሽ ስር ሚዜው ይዞ ያሳያል፡፡ ከዚያ አጠረ፣ ረዘመ ሽማግሌዎች ይተቻሉ "ዝቅ ይላል፤ ዝቅ ያልከው አጭር ስለሆነ ነው፤ ይዘኸው ቁም" ይባላል፤ "ዋስ ጥሩ" ይባላል፡፡ "ለሚቀጥለው እናስተካክላለን" ካሉ በኋላ ከዚያው አካባቢ የሚኖር ሰው "የጎደለውን ሁሉ እኔ አስተካክላለሁ፤ እኔ እዋሳለሁ" በማለት ዋስ ይሆናል፡፡

የሙሽራዋ የሴት ጓደኞች ለማሳሳት ኩታ ተከናንበው ይቀመጣሉ፡፡ ከጓደኞቿ መሀል ሙሽራዋን ለይቶ ልብሷን ማልበስ አለበት፡፡ መለየት አቅቶት ለሌላ ሰው ካለበሰ ለሙሽራዋ ስጦታ መስጠት ይጠበቅበታል፡፡ ኒካ ወይም ቀለበት ከመታሰሩ በፊት አይበላም፡፡ ኒካ ከታሰረ በኋላ ምግብ መመገብ ይጀምራሉ፤ ይዘፈናል፡፡ አበልጇ አገልግሉን ይዛ ትዘፍናለች፤ ዘመዶቿ ይዘፍናሉ፡፡ ሙሽራው ይዞ ሊወጣ ሲል "አናስወጣም" ብለው ያስቸግራሉ፤ ስር ሚዜዋ ሙሽራዋን ያለብሳትና የሴቷ ዘመድ የሆነ ሰው አዝሏት ይወጣል፤ ከዚያም ይቀመጣል፡፡ በላይዋ ላይም ነጠላ ይዘረጋል፡፡ አራት ሚዜዎች ኩታውን (ነጠላውን) ይይዛሉ፡፡ የስር ሚዜው ኩታው ውስጥ ይገባና "የወሮ ዘመድ፣ የልጅቷ ዘመድ የሆናችሁ፣ የምትወዷት ጓደኞቿ" ይላል፤ ሌሎቹም አብረው እርሱ የሚለውን ይላሉ፡፡ ከዚያም የተለያየ ስጦታ ነጠላው ላይ ይጣላል፡፡ ስጦታው በሙሉ ይሰበሰባል፡፡ በመቀጠልም የስር ሚዜው ስጦታውን በሙሉ ይቆጥርና ይህ "ጓደኞቿና ዘመዶቿ የሰጧት ነው" በማለት ቆጥሮ ያስረክባል፡፡ ኩታውም ይሰበሰባል፡፡ ከዚያም አዝሏት የመጣው የሴቷ ወገን ከጫጉላ ወጥቶ ይሄዳል፡፡ የወንድዬው ሚዜ ያዝላትና ጉዞ ይቀጥላሉ፤ ሙሽራዋን ይዞ ሲመለስ ያ የታረደ ዶሮ ለሙሽሮቹና ለስር ሚዜዎቹ ይቀርብላቸዋል፡፡ ለሁሉም ሚዜዎች ትንሽ ትንሽ የዶሮ መረቅ ይደረግላቸዋል፡፡ የሚዜዎቹ ቁጥር እስከ 40 ሰው ሊደርስ ይችላል፡፡ ቁጥሩ ካነሰ በደንብ አይጨፍሩም ተብሎ ይታሰባል፤ በተጨማሪም ልጅን ብቻዋን ይዟት ሄደ ተብሎ ይተቻል፡፡ በባህላቸው የሴት ሚዜ አይታወቅም፡፡ ሚዜዎቹ ከሙሽሮቹ ዶሮ ወጥ መብላት ስለሚፈልጉ ሰርቀው እስከመብላት ድረስ ይደርሳሉ፣ ሰርቀው ከበሉ እንደ

ሙሽሮቹ ዶሮ በላን እያሉ ያወራሉ። ሙሽራዋንም የሚያዝላት የስር ሚዜው ነው። በዚህ ሁኔታ በወንዱ ቤት እየተዘፈነ እየተጨፈረ ይታደራል።

ከዚያ በሁለተኛው ቀን ሰዎቹ ድብራ ወይም ስጦታ የሚጥሉበት ቀን ነው። ሰዎቹ ተጠርተው ለቀኑ የተዘጋጀው ምግብ ይበላል፤ ይጠጣል። ከቀኑ ሰባትና ስምንት ሰአት አካባቢ ሲሆን "በሉ እንግዲህ ለብር ማስጣያ የሚሆነው ጠላ ይውረድ" ይባላል፤ ለብር ማስጣያ የሚሆን ጠላ ይሾማል። ከዚያም በኋላ ሰዎች ብር ይጥላሉ።

በሦስተኛው ቀን ማክሰኞ የቤተ ዘመድ ይባላል። የቤተዘመድ የሚባሉት እራስ/ ጭንቅላት፣ ምላስ፣ ሰምበርና ጨንራ ሲበላና ሲጨፍር ይውላል፤ ይታደራል።

በአራተኛው ቀን የልጁ ሴት ዘመዶችና ሴት ጓደኞች ለሙሽራው ያላቸውን ፍቅርና ከበሬታ ለመግለፅ ከየቤታቸው ፍትፍት ይዘው ይመጣሉ። ሙሽራው ደግሞ ይህን ዝግጅት እንዲያሳምሩለት ለበርካታ ሰዎች ሹመት ይሰጣል። የሹመት አሰጣጡም ከንጉስ ይጀምራል። የጅ ካለ ወይም ሙሽራው ከአሁን በፊት በሰዎች ሰርግ ላይ ሚዜ ሁኖ ሹመት ተሰጥቶት ከሆነ በእነርሱ ሰርግ ላይ ተሰጥቶት የነበረውን ስልጣን ለእነርሱ መልሶ ይሾማቸዋል። ከዚህ ውጭ ያሉትን ግን እርሱ ወደፊት ሊያገኘው የሚመኘውን ስልጣን ይሰጣቸዋል። ከዚያም መጀመሪያ ስር ሚዜው ስልጣኑን ይለቃል ሙሽራዎቹን እስከ እቃቸው ቆጥሮ ለሿሚ ይሰጣል። የመጀመሪያው ተሿሚ ጫጉላ ጠባቂ የሚባለው ነው። የዚህ ሰው ኃላፊነት ሙሽሮቹን እስከ ንብረታቸው ይጠብቃል። ጫጉላ የሚባለው ዳስ አካባቢ ጋቢ ይጋረድና የሰርጉ ስርዓት እስከሚያበቃ ድረስ ሙሽሮቹ የሚቀመጡበት ነው። እነሱን ማየት የሚመጣውን ሰው ስጦታ እየተቀበለ ጋቢውን በመግለጥ ያሳያል። እንዲሁም ሙሽሮቹንና ንብረታቸውን ይጠብቃል።

ሌላው ሹመት ፍትፍት ቀማሽ የሚባለው ነው። ፍትፍት ቀማሽ የሚባለው እያንዳንዷ ሴት የምታመጣውን ፍትፍት ይቀበላል። ሌላው ተሿሚ ፍትፍት ቆጣሪ የሚባለው ነው። ይህ ሰው የሚመጣውን እያንዳንዱን ፍትፍት ይቆጥራል። ፍትፍት ቆጣሪ አምስት ሲሞላ አራቱን ለእነሱ ይሰጥና አንዱን ለራሱ ያደርጋል። አሁንም አምስት ሲሞላ አራቱን ለእነሱ እየሰጠ ይሰበስባል። በጣም ትንሽ ከተባለ እስከ ሃምሳ ፍትፍት ይመጣል። ፍትፍት የሚያመጡት ሴቶች ቅቤ፣ ዘይት፣ የተለያዩ ቅመማ ቅመሞችንና

ጥቃቅን ነገሮችን ከራሳቸው ቤት የሚያመጡ ሲሆን እንጀራና ስጋ የሚሰጠው ግን ከሰርጉ ቤት ነው።

ሌላዎቹ ተሿሚ ቆራጥ፣ ቀኝ ወንበር፣ ግራ ወንበር፣ ንጉስ፣ ተራ ወታደር ተብለው ይሾማሉ። ተራ ወታደር ሆነው የተሾሙት ከእነሱ ራቅ ብለው ይቀመጣሉ። ሹመት ያልተሰጣቸው ሌሎች ታዳሚዎች ደግሞ ቦታ ቦታቸውን ይዘው ይቀመጣሉ፤ እነዚህ ሰዎች የጨዋታው አድማቂ ናቸው፤ ከዚያም ባሻገር የመጣውን ፍትፍት፣ የሙሽራውን ክፍያና ጫማ ይሰርቃሉ። የተቀመጡትም ሌሎች ሚዜዎች ይከሳሉ፤ ጠባቂውን በአግባቡ ስላልጠበቀ እንዲፈረድበት ይጠይቃሉ። ከዚያም ቆራጥ የሚባለው ወታደሮችን ጠባቂውን አቅርቡት ይላል። ታስሮ ይቀርባል፤ "አቤት" ይላል ንጉስ የሚባለው "አሳስኝ" ብሎ ያነጥሳል። ንጉስ የሆነው ሰውዬ ሲያስነጥስ ጠባቂው "ይነቅዎት" ይላል። ንጉሱም "እንዴ እንዴ እሄማ እኔን የናቀ ሙሽራ መጠበቅ ስለማይችል ይታሰር" ይላል። በደንብ አድርገው ካሰሩት በኋላ ቆራጥ የሚባለው እያዳፋ በሰፈሩ ያዞረዋል። በየቤቱ እየዞረ "አቤት! አቤት! አቤት!" እያለ ይጮሀል። ከዚያም ካንዱ ቤት ዘሎ ይገባል "ምንድነው?" ሲሉት "እቃ ጠፍቶብኝ ታስሬ እስረኛ ነኝና አስፈቱኝ" ይላቸዋል። ሰዎችም "በቃ ምን እናድርግ?" ይሉና እቤታቸው ውስጥ ያለውን ነገር ይሰጡታል። እጁ እንደታሰረ ምንም ነገር ሳያንድል የተሰጠውን ነገር ያስረክባል። "አቤት አቤት" ብለው ይቀበሉታል። አንዳንዴ "ያመጣኸው ስጦታ ከሰራኸው ወንጀል ጋር ስለማይመጣጠን ይደገም" ከተባለ በተመሳሳይ ሁኔታ ሂዶ ሌላ ስጦታ ማምጣት አለበት። ተደጋጋሚ ጥፋት የሚያጠፋ ከሆነ ደግሞ ሌላም ቅጣት ሊጠብቀው ይችላል። ንጉሱም "ትን" ሲላቸው እኔ ልታነቅልዎት ማለት መቻል አለበት። ይህን ካላለ ቅጣት ይጣልበታል። ግን አውቆ ሰውን ለማስደሰትና ለማዝናናት ሲል ይነቅዎት ይልና ይቀጣል። ቆራጥ የሚሆነው ሰው ጠንካራ መሆን አለበት፤ ነጥቆት ከሮጠ ራሱ ቆራጥ የሆነው ሰውዬ ይታሰራል። በዚህ ዝግጅት ላይ ጠባቂ ተብለውና ወታደር ሆነው የተመረጡት ሁሉ ሊሰርቁ ይችላሉ። ሲሰርቁ ከተነቃባቸው ግን "ስልጣን ተሰጥቶህ በመስረቅህ" ተብለው ይፈረድባቸዋል። አንዳንዶቹ ዝግጅቱ በጣም ደስ ስለሚላቸው ተደጋጋሚ ጥፋት ይፈፅማሉ። በዚህ ጊዜ እኛ ብንለው ብንለው ይህ ሊለወጥ ስላልቻለ ለተወሰነ ሰአት ጋን ይቀዳበት ይባልና እንደታሰረ መሬት ላይ አስተኝተውት ሚዜዎቹ የሚጠጡት ጠላ ጋን በሰውዬው ትክሻ ላይ ይደረግበታል። እርሱም ከስር ሁኖ "አቤት! አቤት!" እያለ ይጮሀል፤ እየተቀዳ ሰው ይጠጣል፤ ጨዋታቸውም ይቀጥላል። በመጨረሻም ቀኝ ወንበርና ግራ ወንበር የተባሉት እንደ ፍርድ ቤት ዳኞች ሆነው አስተያየት ይሰጣሉ። በእንዲህ አይነት ሁኔታ ሙሉ ቀን

ይዋላል። ከአምስት ሰሀን ውስጥ አንደኛው ፍትፍት ቆጣሪ ሲወስድ አራቱ ወደ ጫጉላ ቤት ይገባል። ከአራቱ ደግሞ አንዱ ለሽማግሌዎች የሚሰጥ ሲሆን፣ ሦስቱ ወደ ሙሽሮች ይሄዳል። ከዚያም ሚዜው እና ሌሎቹ ይከፋፈሉና ይበላሉ። ማታም ሲጨፍሩ ያድራሉ የአራተኛው ቀን ዝግጅት በዚህ ይጠናቀቃል።

ሀሙስ ጠዋት ሁሉም ሚዜዎች ይሰበሰባሉ። የተራረፈ ድግስ ሲበሉ ሲጠጡ ይውላሉ። ልክ ማታ በአንድ ሰአት አካባቢ ጭፈራ ይጀመራል። ሀሙስ ስም የማውጫ ቀን ነው። ከዚያም ተጨፍሮ ሙሽራዋና ሙሽራው ተዘጋጅተው እንደተቀመጡ አበልጂ (ክርስትና እናቷ) ከምትሰፋላት አገልግል ውስጥ የተለያዩ ሙዳዮች አሉ። ከእነዚህ ውስጥ ስም ማውጫ የምትባል ስፌት አለች። ያች ስፌት በሻሽ ትታሰርና "በሉ አሁን ለሙሽራዋ ስም አውጡላት" ይባላል። ከዚያ እናቷ፣ አባቷ፣ ዘመዶቿ፣ ጎረቤቶቿ፣ እክስት የወንድም ሚስት፣ እህት በሙሉ ለሙሽራዋ ስም ያወጣሉ። ይህ ስርዓት ቢያንስ ከአንድ ሰአት እስከ ሁለት ሰአት ያህል ሊቆይ ይችላል። ከዚያ ሲበላ፣ ሲጠጣ፣ ሲጨፈር ይታደራል።

አርብ ጠዋት ሁለቱ ስር ሚዜዎች ብቻ ቀርተው፣ ሌሎቹ ሚዜዎች በሙሉ ወደየቤታቸው ይሄዳሉ። ሁለቱ ስር ሚዜዎች አርብንና ቅዳሜን ይውላሉ፣ ያድራሉ። ልክ በሳምንቱ እሁድ የሙሽራዎቹን እና የራሳቸውን ልብስ ሲያጥቡ ውለው ሰኞ ጠዋት ወደየቤታቸው ይሄዳሉ። የሰርጉ ስርዓትም በዚህ ይጠናቀቃል።

በሰርጉ ስርዓትም የማህበረሰቡ አባላት የሚያደርጉትን የእርስ በርስ የመተጋገዝና የመረዳዳት ባህል ለመረዳት ይቻላል።

# ምዕራፍ ስድስት

## ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ጽሁፍ በነገደ ወይጦ ማህበረሰብ የሚነገሩ ዝርው ቃል ተረኮችና ባህላዊ ስርዓቶች ለማህበረሰቡ ያላቸውን ፋይዳ ተንትኖ ማሳየት ነው፡፡ በመሆኑም ይህንን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ባላቸው የፅሁፍ ሰነዶች፣ በቃለመጠይቅና በምልከታ መረጃ ተሰብስቧል፡፡ መረጃው በጽሁፍ ማስታወሻ፣ በቪዲዮ ካሜራ፣ በፎቶግራፍና በመቅረፀ ድምፅ አማካይነት ተቀርጿል፡፡ የተሰበሰቡት መረጃዎችም የተለያዩ ማጣቀሻ መፅሀፎችን መሰረት በማድረግ ትንታኔ ተሰጥቶባቸዋል፡፡

ከመረጃዎቹ ተነስቶ በተሰጠው ትንታኔ መሰረት በማህበረሰቡ ከሚነገሩት ቃላዊ ዝርው ተረኮች መካከል የተወሰኑት የማህበረሰቡ ስያሜ ከአመጋገብ ስርዓታቸው፣ ከነገዱ አባት ስም፣ ከስራ ባህላቸውና በአካባቢው ካለ የእህል ፍሬ መጠሪያ ጋር የተያያዘ እንደሆነ ማወቅ ተችሏል፡፡ በተለይ ከአመጋገብ ስርዓታቸው ጋር ተያይዞ የተሰጠው ስያሜ አመጣጡ ከሌላው የአካባቢው ማህበረሰብ ሊሆን እንደሚችልና ተጠኝ ማህበረሰቡን ዝቅ አድርጎ ለማሳየት የተጠቀመበት እንደሆነ ጥናቱ አመላክቷል፡፡ ሌላዎቹ የስያሜ አመጣጥ በማህበረሰቡ አባላት የሚታመንባቸው ሲሆን፣ በሌላው ማህበረሰብ የተሰጠውን ስያሜ ለመከላከልና ማህበረሰቡ ከሌላው ማህበረሰብ የሚደርስበትን ጫና ለመቋቋም እንደሚገለገሉባቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡

የተወሰኑት ቃላዊ ዝርው ተረኮች ደግሞ የማህበረሰቡ አመጣጥ በቅል ውስጥ ከነበረ ውሃ እንደተገኙ፣ በነብዩ ሙሴ ዘመን ከግብፅ ወደ እስራኤል ከሚጓዙት ነገዶች መካከል እንዱ እንደሆኑ፣ የግብፅ ነባር ጎሳ እንደነበሩ፣ የንግስተ ሳባና የአፄ ፋሲል ዝርያ እንዳላቸው የሚያሳዩ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ በቅል ውስጥ ከነበረ ውሃ እንደተገኙ የሚያሳዩ ከአካባቢው ማህበረሰብ ማህበረሰቡን ዝቅ አድርጎ ለማሳየት የሚተርኳቸው እንደሆን በተጠኝ ማህበረሰቡም ዘንድ ተቀባይነት እንደሌላቸው ለመረዳት ተችሏል፡፡

አንዳንዶቹ አመጣጥን የተመለከቱ ቃላዊ ዝርው ተረኮቻቸው በማህበረሰቡ ተቀባይነት ያላቸው ሲሆን፣ የማህበረሰቡን ስረ መሰረት ከነገስታት እና ከሃይማኖት መሪ ጋር

የተገናኘ እንደሆነ በማሳየት ማህበረሰቡ ከሌላው ማህበረሰብ ለሚደርስበት የስነልቡና ጫና ለማረጋጋት እንደሚያግዙ ታውቋል፡፡

ሌሎቹ ተረኮች ማህበረሰቡ በሃይማኖት የመፅናት፣ አዳዲስ የፈጠራ ውጤቶችን ማለትም ታንኳ፣ ወፍጮና የከተማ መስራችነት ለሌላው ማህበረሰብ እንዳስተዋወቁ የሚያሳዩ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ በዚህም ማህበረሰቡ በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ ዝቅ ተደርጎ ለሚታይበት አመለካከት እንደመከላከያነት እንደሚጠቀሙባቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡

ቀሪዎቹ ደግሞ ማህበረሰቡ በነብዩ ሙሴ መረገሙንና ህይወቱ ከውሃ ጋር የተሳሰረ እንደሆነ የሚያሳዩ ናቸው፡፡ እነዚህ ተረኮች ማህበረሰቡ በዝቅተኛ ኑሮ ለመኖሩ ምክንያቱ እርግማን እንደሆነ ለማሳየት ይጠቀሙባቸዋል፡፡

ማህበረሰቡ ከሌላው የአካባቢው ማህበረሰብ በተለየ ሁኔታ የአምልኮ፣ የግርዛትና የሰርግ ስርዓት አለው፡፡ አምልኮታዊ ስርዓቱ የማህበረሰቡ አባላት ከጣና ሀይቅ እና ከአባይ ወንዝ ጋር ባላቸው የዕለት ከዕለት እንቅስቃሴ ከወንዙ አስተዳዳሪ ወይም ከአቢናዝ ችግር እንደማይገጥማቸው እና አቢናዝ እገዛ እንደሚያደርግላቸው እንዲያምኑ የማድረግ ተግባር እንዳለው ለመረዳት ተችሏል፡፡

በግርዛት ስርዓቱ ወንድ ልጅ ተደግሶ ሰኞ ቀን በመገረዙ ምክንያት ጀግና፣ አዳኝ፣ ደም መላሽ ወይም መከታ፣ ለወላጆቹም ኩራት ይሆናል ተብሎ ይታመናል፡፡ የሰርጉ ስርዓት ደግሞ በማህበረሰቡ መካከል መረዳዳትና መተጋገዝ ባህላቸው እንደሆነ የሚያሳይ ነው፡፡

በአጠቃላይ በማህበረሰቡ የሚነገሩ ቃላዊ ዝርው ተረኮች የማህበረሰቡን ስያሜ፣ አመጣጥ፣ የስራ ባህል፣ የእምነት ፅናት እና በዝቅተኛ ኑሮ ያሉት በእርግማን ምክንያት እንጂ ባለመስራታቸው አለመሆኑን የሚያመላክቱ ሆነው ተገኝተዋል፡፡

ባህላዊ ስርዓቶቹ ደግሞ የማህበረሰቡ አባላት ከጣናና ከአባይ ገዥ ወይም ከጅኑ ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንዳላቸውና እንደሚጠብቃቸው፤ በግርዛቱ ስርዓት ወንድ ልጅ ጀግና ይሆናል ተብሎ እንደሚታመንና በሰርጉ ስርዓት ደግሞ ማህበረሰቡ እርስ በእርስ የጠበቀ ትስስር እንዳለው ያሳያል፡፡ በመሆኑም ቃላዊ ዝርው ተረኮቹና ባህላዊ ስርዓቶቹ የማህበረሰቡ ማህበራዊ መሰረት ስለሆኑ ማህበረሰቡ በጥንቃቄ እንደሚጠብቃቸው ለመረዳት ተችሏል፡፡

## ዋቢ ጽሁፎች


ማንያለው አባተ። "የቤንች ቃላዊ ዝርው ተረክ ዘሮችና ማህበራዊ ፋይዳቸው"። በኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1999።

ምስጌ ቢራራ። "የወይጦ ነገድ አጭር ታሪክና ባህል"። ባህር ዳር፤ ያልታተመ፣ 1979።

ምንዳ ገብሬ። "የጌዲኦ ልማዳዊ ሥርዓትና ዝርው ቃል ተረኮቻቸው"። በኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሁፍ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 2000።

ባህር ዳር አጠቃላይ ምክር ቤት። <u>ውቢቱ ባህር ዳር</u>። አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ቤት፣ 1975።

ብርሃኑ ብስራት። <u>የመጠሪያ ስሞች መዝገብ</u>። አዲስ አበባ፤ ኤች ዋይ ማተሚያ ቤት፣ 2001።

ታዬ ገብረማርያም። <u>የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ</u>። ወንጌላዊት ማተሚያ ቤት፤ አስመራ፣ 1920።

ታፈሰ ካሳ። "የወይጦ ብሔረሰብ አባላት በሚመለከት የተዘጋጀ አጭር ጥናታዊ ሪፖርት"። ባህር ዳር፤ ያልታተመ፣ 1978።

አማረ ሞላ። "የሽክቾ ብሔረሰብ ሀገረሰብ ተረቶች ምደባ፣ የአከዋወን ስልትና የይዘት ትንተና"። በኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1999።

አየለ ፍቅሬ። "ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴ በባህር ዳር ነገዴ (ወይጦ) ኅብረተሰብ"። በኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1998።

የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ባህልና ቱሪዝም ቢሮ። <u>የአማራ ህዝብ ባህልና ቋንቋ</u>። አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 2001።

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር። <u>መጽሐፍ ቅዱስ</u>። አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1980።

ዮሐንስ ወልደ ማርያም። (ተርጓሚ) <u>የዓለም ታሪክ</u>። አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1940።

ፈቃደ አዘዘ። <u>የስነቃል መምሪያ</u>። አዲስ አበባ፤ ኢትዮ ጥቁር ዓባይ አታሚዎች፣ 1991።

Abdulkadir Haji Jima. "Some Cultural Elements as Reflected in Somali Folktales." M.A. Thesis, Department of Foreign Language and Literature, Addis Ababa University, 1982.

Abraham Alemu. "Jimma Oromo Oral Prose Narratives: A Preliminary Descriptive Analysis." M.A. Thesis, Department of Foreign Language and Literature, Addis Ababa University, 2000.

Bascom, William R. "Four Functions of Folklore". The Journal of American Folklore, Vol.67, No.266 (Oct.-Dec., 1954), 333-349, American Folklore Society, http://www.jstor.org/stable/URL.

___. "The Forms of Folklore: Prose Narratives". In Segal, Robert A. (Ed.) Anthropology, Folklore, and Myth. New York and London: University of Lancaster, Garland Publishing,1996, 1-16.

___. "The Forms of Folklore: Prose Narrative". The Journal of American Folklore, Vol.78, No.307 (Jan.-Mar., 1965), 3-20, American Folklore Society, http://www.jstor.org/stable/538099.

Bayileyegn Tasew. "Anyuaa Oral Prose Narratives: Ethinc Genres and Social Functions." M.A. Thesis, Department of Foreign Language and Literature, Addis Ababa University, 1999.

Berkowitz, Rabbi Miriam C. "Creative Life Cycle Rituals." Contact, The Journal of the Steinhardt Foundation for Jewish Life, Vol. 12, No. 2, (Winter, 2010), 14; Steinhardt Foundation for Jewish Life.

Darmon, Chloé. "The Weyto Language of Ethiopia: State of the Art". Workshop Language Isolates in Africa, 2010, 1-4.

Dégh, Linda. "Oral Folklore: Oral Narratives." In Dorson, Richard M. (Ed.) Folklore and Folklife: An Introduction. Chicago and London: The University of Chicago Press, 1972.

Dorson, Richard M. (Ed.) Folklore and Folk Life: An Introduction. Chicago: The Univeristy of Chicago Press, 1972.

Finnegan, Ruth. Oral Literature in Africa. Oxford: Clarendon Press, 1970.

Goldstein, Kenneth S. A Guide for Field Workers in Folklore. Detroite: Gale Research Company, 1974.

Jerusalem Children and Community Development Organization. "The Prospect and Challenges of Empowerment among Caste Groups: the Case of Negede Woyto Community in Bahir Dar Town, Ethiopia." Addis Ababa, Unpublished, 2009.

Kottak, Conrod P. Cultural Anthropology. New York: Unknown Publisher, 2002.

Melake Mihret. "A Study of the Socio-Cultural and Economic Marginalization of the Wayto in and around Bahir Dar, Northwestern Ethiopia." M.A. Thesis, Department of Social Anthropology, Addis Ababa University, 2010.

Melakneh Mengistu. "The Major Themes and Motifs of Southern Agaw Folktales." M.A. Thesis, Department of Foreign Language and Literature, Addis Ababa University, 1990.

Ochs, Vanessa L, "The Courage to Reinvent Jewish Ritual". Contact. The Journal of the Steinhardt Foundation for Jewish Life, Vol. 12, No. 2, (Winter, 2010), 5-6; Steinhardt Foundation for Jewish Life.

Oring, Elliot. Folk Groups and Folklore Genres: An Introduction: Logan, Utah: Utah University Press, 1986.

Plowden, Wallter Chichile. Travels in Abyssinia and the Galla Country. London: Longmans Green, and Co., 1969.

Rassam, Harmuzed. Narrative of British Mission to Tewodros, King of Abyssinia. Vol. I. London: John Murray, 1869.

Ray, Benjamin C. African Religion: Symbol, Ritual, and Community. New Jersy: Prentice Hall, Inc., 1976.

Sahilu Kidane. "Borana Oromo Prose Narratives: A Contextual Study." M.A. Thesis, Department of Foreign Language and Literature, Addis Ababa University, 1996.

Sims, Martha C. and Martine Stephens. Living Folklore: An Introduction to the Study of People and their Traditions. Logan, Utah: Utah State University Press, 2005.

Solomon Atnafu. "Negede Wayto: Marginalized Minorities Living on the Banks of the Lake." Bahir Dar, Unpublished, 2006.

Teclehaimanot Gebre Sellasie. "The Wayto of Lake Tana: An Ethino-History." M.A. Thesis, Department of History, Addis Ababa University, 1984.

Tesfaye Gebre Mariyam. "A Study of Major Themes in Jablawi Folktales." M.A. Thesis, Department of Foreign Language and Literature, Addis Ababa University, 1990.

Vansina, Jan. Oral Tradition as History. Madison, Wisconsin: University of Wisconsin Press, 1985.

Yihenew Jembere. "A Generic Classification of Amharic Oral Prose Narratives of West Gojjam." M.A. Thesis, Department of Foreign Language and Literature, Addis Ababa University, 1996.

# አባሪዎች

## አባሪ አንድ የተረኮች ስብስብ

### ወይጦ የሚለውን ስያሜ በተመለከተ

### ተረክ አንድ

በግብጥ ሲመጡ በችግር ምክንያት ነው አሉ። ተሰደው ሲመጡ ሦስት ሆነው ነው አሉ የወጡ። አዝማሪ፣ ቅማንት፣ ዋቶ ተብለው ወደ ባህር የቀሩት ያው በትምህርት ስንሰማ ሦስት ሆነው በችግር የወጡት ሁለቶች አዝማሪና ቅማንት ያው ደጋ ለደጋ ወጡ ይባላል። የኛ ደሞ ዋቶ ተብሎ ባህር ለባህር የቀሩት ያው ባህር ለባህር ኼደው ሱዳንን አድርገው ባህር ለባህር መጠው እነሱ ያው አሳ፣ ይኸው አምባዛ፣ ያው ደሞ ዱሮ ጉማሬ ምትባል ነበረች ያችን ያችን ባህር ለባህር ይዘው ስለቀሩ እነዚያ ዋቶ እየተባሉ የመጡት ያው አገራቸውን ትተው ስለተሰደዱ ዋቶ እየተባሉ የመጡት እንደገና ተፈነጣጥረው ሲለያዩ፤ የኛውን ወይጦ በሚለው ያው በምግቡ በምንም ወይጦ በሚለው መንገድ አመጡት እንጂ ተግብጥ ሲወጡ ነው ያው ስማቸው የተከፋፈለ እንደዚያ ነው ሚባለው። አሁን የኛ አባቶቻችን ሲያወሩ ምንሰማው ዋቶ ተብሎ የነበረው ያው እየተራቀቀ ሲመጣ ወይጦ ሆነ። ያው ወይጦ የሚለው ስም ባህር ለባህርን ይዞ ቀረ። ባህር ለባህርን እንደያዙ ቀሩ። ሀገራችን ባህር ለባህር ሆኖ ቀረ እንጂ ዋቶ የተባሉ ከግብጥ በችግር ምክንያት ሲወጡ ነው ሚባለው (ሰጡ የኔሁን፣ ካሴት ቁጥር 1(ሀ)፣ ሚያዝያ 30 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)

### ተረክ ሁለት

በደርግ ነገዴ ተባለ። ወይጦ ምንባለውን ቀየረና እሱ ተመጣ ምንድን አለነ በደርግ ነው ነገዴ አለነ። ዛሬ ሲጠሩነ ነገዴ እንባላለን። ቀድሞ ጉማሪቱንም አሳይቱንም በላችሁ ስለምንባል ጉድፍድፍ ስንበላ ጊዜ ነው እንጂ ዛሬ እስላም ሊያረጉነ እንደኛ ኀሳ እያሉነ ዛሬ እየተጣራነ ነው እንጂ የዛን ጊዜ ወይጦ ይሉነ የነበር ምኒቱንም ጉማሪቱን በላችሁ ይሉናል። ከብቲቱን መቼም ጠገግ ያለችውን ስለምንበላ ጠገግ ያለችውን ከብት አንመርጥም። እንደነሱ ከፍ ያለውን ስለማንመርጥ እነዚህማ ወይጦች ናችሁ እችን ሚበሏት ወይጦ ነው ይሉናል (ሙሉ ልብሞኝ፣ ካሴት ቁጥር 1(ሀ)፣ ሚያዝያ 30 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)

## ተረክ ሦስት

ሁለት ወንደማማቾች ናቸው አሉ። አባታቸው ልመርቃችሁ ይሏቸውና ጭራሮ ይቀው እንዲያመጡ አዘዋቸዋል። ከዛ ያማራው ቀድሞ መጦ ጭራሮዋን ጣል ሲያረግ፣ ማነህ አንተ ይላሉ - አባትዬው። እኔ እገሌ ነኝ ሲል ይመርቁትና ይሄዳል። ወዲያው የኛው ይመጣና ጣል ሲያረግ ማነህ ይሉታል። እሱም እኔ ነኝ ሲላቸው አይ ያ ርጉም ምርቃትህን እዞብህ ኸደ በል አሁን እሩጥ እና ያነን የመረኩትን ያዝልኝ ሲሉት፣ ተሻግሮ ይመጣና ትንሽ ዳቦ ጣል ያረጋል ተባህሩ ላይ። ዋቶች እንግዲ ወይጦ ተብለን የቀረን ያችነን ያችን ጣል ሲያረጋት ያችን ያነሱና የኛዎች ዋጥ ያደርጓታል። ያችን ተጣና የወደቀችውን ብድግ ያረጉና ኸረ ዋጣት ዋጠ ዋጣት ብሎ ወይጦ የተባልነ በዚህ ነው። (ሼህ ይመር ሙጬዬ፣ ካሴት ቁጥር 3(ሀ)፣ ሚያዝያ 30 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)

## ተረክ አራት

ምክንያቱ በጉማሬ ነው፣ በራብ ጊዜ ነው። ባንድ ላይ ሆነው ይሳና ያቆብ በራብ ጊዜ ገለውት፣ ያነን ባንድ ላይ ገሬው ጉማሬውን ይቆራርጣሉ፣ በካራ ቆራርጠው እንግዲህ እራብ ክፉ አደል በል እስቲ አንተ ሞክር ቅመሳት ቅመሳት ቅመሳት ተባብለዋል ነው አዎ እንግዲህ የኛው ተቻኩሎ ያችን ውጧል። በዛን ጊዜ ዋጣት አለው፣ ተዚያ ወዲህ ወይጦ የተባለ። (ሼህ ቸርነት ዘሪሁን፣ ካሴት ቁጥር 3(ሀ)፣ ሚያዝያ 30 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)

## ተረክ አምስት

ተዘመቻ ላይ ሲኸዱ በነብይ ሙሳ ጊዜ አዲያ ሲኸዱ ታንድ ትልቅ ወንዝ ደረሱ ይላል። አዲያ አሁን እንደምልሽ ደርሰው ሳለ ጉማሬ ሚባለውን ገለው እንግዲህ ሰማችሁ እሂን እንብላው አንብላው የሚለውን ተመካከረዋል። ሲሉ ኸረ እንዲህ አርገው ቆርጠው ቆርጠው በጃቸው እዘው እንብላው አንብላው እንብላው አንብላው እየተባባሉ ሲመካከሩ ይላል። አዲያ አንደኛው ግድም ኸረ ምንድነው ይልና ያን የተጎመደ ስጋ ይውጣል። ኸረ ዋጠው የተባለበት ስያሜው የመጣ እዚህ ላይ ነው። ዋጠው ሲል ዋቶ ሆነ እየቆየ ወይጦ ተባለ በርሀብ ጊዜ ያችን አውሬ በሉ። (ሼህ ጅብሪል ሰማኸኝ፣ ካሴት ቁጥር 3(ለ) ግንቦት 03 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)

## ተረክ ስድስት

ስያሜው ላይ እንዴት መሰለሽ የአማራው ክፍል የጠራበት ስያሜ ተዚያ ተግብጥ ሲመጡ ወደ አራት ነገሮች እዘው መጡ እልሻለሁ። ወደዚህ ሲመጡ አንደኛ ፍላጣ መንጠቆ፣ ፌሾ ጤፍ፣ ግብጦ እዘው መጡ። አሁን እዘው ሲመጡ፣ ወደዚህ እች ግብጦ ምትለዋን ፍሬ አማራው ሲጠይቃቸው፣ እችን ፍሬ አነሱና እች ምንድናት እሉት ለዚያ ለመጡት። አሁን እነሱ በቋንቋቸው ነው ሲናገሩ የፈለጉት ተግብጥ ብለው ቋንቋቸውን ነው ግብጣዊ ናት ሲሉ ነበር በቋንቋቸው ማለት ነው በሚሉ ጊዜ ኧረ ወይጦ አላት አሉና ስሟን ጠሯት ይባላል አማራው ስያሜ ሰጡት ማለት ነው። (አቶ ሙሀመድ አንተነህ፣ ካሴት ቁጥር 6(ለ) ግንቦት 6 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)

## ተረክ ሰባት

ፍራኦንና ነብይ ሞሳ ያው በውጊያ ሲለያዩ ነብይ ሞሳ ፍራኦን ወደ ባህሩ ሲሰምጥ በዘንጓ ሲመቷት ሰመጠ ይላል እና ፍራኦን በዚያ ሲሰምጥ ነብይ ሞሳ ከነጭፍራቸው ጉዞ ቀጠሉ። አሁን ጉዟቸውን ሲኸዱ ይከተሏቸው የነበሩ የጦር አበጋዞች ጃሉትና ጧሉት የሚባል ነበራቸው እና ጃሉት አንድ የጦር አበጋዝ ነው። ጧሉት ደግሞ እንዱን የጦር አበጋዝ የሚመሩት ሁነው ተከፋፍለው ሲቀጥሉ አሁን የእነሂ ጎሳዎች የሚኳቸው ከጧሉት ጎሳ ጋር ነበሩና እዚያ ላይ እንዳሉ ምን ሰጡት ለጦር ተከታዮቻቸው ምን ሰጧቸው ትዛዝ አንዳንድ እፍኝ ውሃ ጠጡ ተዛ በላይ እንዳትጨምሩ የሚል ትዛዝ ሰጡ ይላል። አሁን ያን ሲሉ እንግዲህ ተሰብስበው ቁጭ እንዳሉ በጣም ጠማቸውና መጨመር አምጠዋል ሦስት አራት እፍኝ መጠጣት አምጠዋል ሲሉ ኧረ ጠጡ ኧረ ብዙ ውሃ ጠጡ እየጨመሩ ጠጡ ብለው በሚሰሙበት ጊዜ ዘመር ብለው ቢያዩ እየጠጡ አንተ ዋጠው ብለው በሚሉ ጊዜ ኧረ ወይጦ አላት ስም ተሰየመ ይላል ዋጠው በሚል ወይጦ በሚለው ተሰየመ (አቶ ሙሀመድ፣ ካሴት ቁጥር 6(ለ)፣ ግንቦት 6 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)

## ተረክ ስምንት

አመጣጣችን ያው ተግብጥ ነው። የግብፅ ተወላጅ ፈሪኦን ነው። የግብፅ ተወላጅ ተብሎ ባህር ለባህር ዙሪያ ነው ምንኖረው። ድሮ ወይጦ የተባልነው ኋላ የናንተውና እኛ ሲሻገር ያኛው ሲሻገር እሂኛው ወደዚህ ሲል ያችን ጉማሬ ሊርባቸው ሲሆን ጊዜ ያችንን ጉማሬዋን ገለው ጉርድ አርገው መትረው እንዲህ አርገው ሊውጥ ሲሉ ጊዜ ኧረ ዋጣት

ሲሉ ምን ተባሉ ወይጦ አሁን ዛሬ ምን ተባሉ ነገደ ተባለ እንጂ የድሮ ስማችን ወይጦ ነው። (አቶ ብርሀን ነጋሽ፣ ካሴት ቁጥር 9(ለ)፣ ግንቦት 8 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)

### ተረክ ዘጠኝ

ስያሜው አንዳንዶቹ ምን ይላሉ መሰለሽ፣ ከግብፅ ሲመጡ መንገድ ላይ ግብጦ ሚባለውን ነገር መራራ ነው፤ እሱን ነገር መንገድ ላይ እየነከሩ፤ እየበሉ ይመጡ ነበር። እና ግብጦ ሚባለውን ነገር እዘው ከግብፅ ስለመጡ ወይጦ የሚለው ከዚህ መጣ የሚል መላምት ያስቀምጣሉ። (ሰለሞን አህመድ፣ ካሴት ቁጥር 11(ለ)፣ ግንቦት 9 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)

### ተረክ አስር

አንዳንዶቹ ደሞ ሥጋ ነገር ታርዶ እየበሉ እያለ ታርዶ በጣም ያድናሉ እና ትልቁን ስጋ ሲያነሳ አንተ እንዴት አድርገህ ልትበላው ነው? ሲሉት፣ እንደዚህ ብድግ አድርጎ ጎረሰውና ዋጠው ኧረ ዋጠው ሲሉት ወይጦ ተባለ ብለው ሚሉ አሉ። (ሰለሞን አህመድ፣ ካሴት ቁጥር 11(ለ)፣ ግንቦት 9 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)

### ተረክ አስራ አንድ

በፈርኦን ጦርነት ጊዜ በዛን ሰአት የታዘዙትን ቃል ሳይቀበሉ ጊዜ ከዛ አንዣር የመጣ ነገር አለ ብለው የሚሉት ነገርም አለ። ውሀ እንዳትጠጡ ተብለው አንዳንዶቹ በልካቸው ጠጡ ሌሎቹ ብዙ ጠጡ ብዙ የጠጡት ደክሟቸው ተኙ፤ ብዙ የጠጡት ደክሟቸው ስለነበር እንደተኙ ሲነሱ እነዛኞቹ የሄዱበት ጠፋቸው፤ የሄዱበት ስለጠፋቸው ውሀ ለውሀ እየሄዱ እነሱን ሲፈልጉ ቀሩ ይባላል እና ስለጠጡ ቀሩ በሚለው ነገር የመጣነው ወይጦ የሚሰው የሚሉ አሉ። (ሰለሞን አህመድ፣ ካሴት ቁጥር 11(ለ)፣ ግንቦት 9 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)

### ተረክ አስራ ሁለት

ግብጦ ይዘው መጥተው የአማራው ማህበረሰብ ምን እንደሆነ ሲጠይቋቸው፣ ግብጦ ብለው በቋንቋቸው ቢናገሩ ግብጦ ሲሉ ወይጦ በማለት ለብሄረሰቡ የስም ስያሜ ስጠዋል ሲባል በአባት የቃላት መረጃ በታረከ አቆይተውናል። (ሼህ ነጃት ሰላይሉ፣ ካሴት ቁጥር 15(ሀ) ግንቦት 15 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)

## ተረክ አስራ ሦስት

ፈርኦን መንግስት ነበር። በዛን ግዜ ጦርነት ነበር። ሲል ሲል እየተበታተን የቀረ የሞተም ሰመጠ ጣና ምናምን ሰምጦ ቀረ ይባላል። ተዚያ ተረፈና የተረፈው ወጣ። አሁን ሲባል ነገደ ዋቶ ነበር ሚለው ዋቶ ሲወርድ ሲዋረድ አሁን ወደ ነገደ ወይጦ መጣ ደሞ ሲያልፍ ሲያልፍ ደሞ ወደ ብሄር ተለወጠ። (አባ ስንታዬሁ አይኑ፣ ካሴት ቁጥር 16(ሀ) ግንቦት 22 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)

## ተረክ አስራ አራት

ያው እሄ ብሄረሰብ አመጣጡ ፈሪኦንና ሙሴ ሁለቱም ወንድማማቾች ሁነው እዛ በሚኖሩበት አገር ላይ በሚሰምጥ ባህር ላይ ውጊያ ይገጥማሉ። በሚሄዱበት ሰአት ላይ የፈሪኦን ዘሮች ነን ምንባለው፣ አሁን ከፈሪኦን ዘር ባህር ላይ እንደገባ ጎኑ ይሰምጣል። ሀይቅ ላይ ይሰምጥና ይወጣል። አሁን የወጡት ትንሾች ሲወጡ፣ አንድ እንስሳ አውሬ ያገኛሉ። ያን አውሬ በመብላት ከህብረተሰቡ ጋር ለመጠላላት ፈለጉ፤ እንደረሀብ አድርጎ ኸረ በላው ኸረ ዋጠው ዋጠው አለና ወይጦ ተባለ ተገለለ። እነዛ የተወሰኑ ብሄሮች ይገለላሉ። (ወለላው ቢሆነኝ፣ ካሴት ቁጥር 16(ሀ)፣ ግንቦት 22 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)።

## ተረክ አስራ አምስት

አያቶቻችን ሲሉ በሳይንስ የሰማነው ሦስት ሁነው የአንድ አገር ሰዎች ከግብጥ ተባረው ሲመጡ፣ እነዚያ ሦስት ሁነው የወጡት ሰዎች አሁን አንዱ በደጋ አዘማሪ ሁኗል። አዘማሪ ወይጦ ቅማንት የተባሉት ከአንድ ከግብጥ የመጡ ናቸው ነው ሲሉ እኔ ምሰማ። እነዛ ወደ ደጋ የሄዱት አዘማሪና ቅማንት ተባሉ። ከአገራቸው ወጠው ስለመጡ አዘማሪና ቅማንት ተባሉ። እሄ ደሞ ያው በአቅም ድክመት ይሁን በዚህ ባህር ለባህር እሂኛው ባህር ለባህር አንድኛው ተዘንጥሎ እሄው ባህር ለባህር ሲቀር፣ እሄ ምንድነው ሲባል ዋቶ ከአገሩ ወጦ ስለመጣ ዋቶ እንየተባለ ሲኖር፣ ያው ባህር ለባህር ባህር ያፈራቸውን የባህር ትላትሎችን እየተጠቀምን ባህር ለባህር ስለቀረን ያው ስማችን ዋቶ የተባለው፣ ሀይማኖት ተጠርቶለት ሲዞር ያው አሁን እየጠደቀ ወደማን መጣ ወይጦ ወደ ሚባለው እየተጠጋ መጨረሻ ስማችን ወይጦ ተብሎ ቀረ እንጂ የመጣን ተግብጥ ነው የሚሉን አያቶቻችን። ትውልድ ሀገራችን ግብጥ ነው። (ሰጡ የኔሁን፣ ካሴት ቁጥር 17(ለ)፣ ግንቦት 23 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)

## አመጣጥን በተመለከተ

### ተረክ አስራ ስድስት

ብሄረሰቡ የመጣው በነብዩ ሙሳ ዘመን ተግብጥ ነው ይባላል። ነብይ ሙሳ ከተከታዮቻቸው ጋር ተግብጥ ተነስተው ሲሄዱ ታንድ ወንዝ ደረሱ። ተወንዙ ሲደርሱም ህዝቡ ሁሳ ውሃ ስለጠማው በከፊል አርጋችሁ ጠጡ በብዛት ስትጠጡ ትደክማላችሁና በከፊል አርጋችሁ ጠጥታችሁ እንሻገር ሲሉ ያው ከፊሉ መሪው ያዘዘውን ጠጣና ሲሄድ፣ ከፊሉ የጠማው ሰው ዝም ብሎ የጠጣ ጊዜ በዚያ ወንዝ ቀረ ይላሉ። በዚያው እንደተለያዩ ግብጥን አርገው እንግዲህ ያው አባይ ሳባይ ሱዳንን አርገው ያገኙትን እየገደሉ አምባዛውን፣ አሳውን እየገደሉና እየበሉ ከዚህ የደረሱት ሰበቡ በዚህ ነው። (ሼህ ጅብሪል ሰማኸኝ፣ ካሴት ቁጥር 1(ሀ)፣ ሚያዝያ 30 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)

### ተረክ አስራ ሰባት

ተግብጥ ስንመጣ እኩሌቶች ቀሩ፣ እኩሌቶች መጡ። ስንመጣ ይኼው ያለን በባህር ዙሪያ ነው ያለ። እኩሌታው በባህር ዳር፣ እኩሌታው በጣቁሳ፣ እኩሌታው በዚህ በደምቢያ፣ በፎገራ አለ። ስለዚህ ይኸው ስንኖር ታለውም፣ የለለውም ይበልጣል። ደህው ይበልጣል። በባህር ዳር ያለው በቀን ስራ ነው ምንተዳደረው። (አባ ሰይዴ አለም፣ ካሴት ቁጥር 3(ለ) ግንቦት 03 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)

### ተረክ አስራ ስምንት

ነገደ ወይጦ በሁለት ገጥ ነው መጣ ሚለው። አንደኛው ያው በግብፅ ሲሆን፣ ተግብጥ እንደተነሱ በነብዩ ሙሀመድ ውጊያ ጊዜ ነው እንግዲህ የተነሱት። ከዚያ ነብዩ ሙሀመድ ከእስራኤል እና ከተለያዩ ከተሞች ተነስተው ወደ ግብፅ ውጊያ እያረጉ ሲሄዱ፣ ግብጥን ውጊያ ድል ካረጉ በኋላ የግብጥ ህዝብ ተደሙ በጣም መፋሰስ የተነሳ ርሀብና በሽታ ሲይዛቸው፣ እሄን አሁን መቋቋም ስላልቻሉ እራሳቸውን ወደ ሚያድኑበት አካባቢ መሸሸት አለብን የሚል ሽሽት ሲያርጉ፣ የመጀመሪያ የተነሱባት ጎጥ ሀናን ትባላለች፣ ከሀናን ተነስተው አረፉና አሁን ከዚያ ሚሄዱበትን ስንቅ ምናምን አመቻቹና ከያዙ በኋላ የአባይን ተፋሰስ ጎን ለጎን በማረግ እየሸሹ ሲመጡ፣ ከዚያ መነሻ ይዘዋቸው የመጡ የቀለብ አይነት እየዘሩ ሚጠቀሙባት፣ አንደኛ ግብጦ፣ ሁለተኛ ፌሾ የምትባል ጥቁር ጤፍ እሷን ከያዙ በኋላ ማስገሪያ ብለው የያዙት ደሞ መንጠቆ የሚባልና ፍላጣ የሚባል ይኼ የጦር መውጊያ ያኛው ፍላጣው ማደኛቸው ነው። ከዚህ በኋላ ያቺ መንጠቆዋ ግን አሳ የባህር ትላትል እያወጡ ሚጠቀሙበት ማለት ነው። እና አሁንም

ይህን ከያዙ በኋላ አሁንም የአባይን ወንዝ በመከተል ወደ ካርቱም ካርቱም ላይ ሲደርሱ ከባድ ውጊያ ገጠማቸው አሁን በዚያ ውጊያ ላይ እነሱም እየሞቱ እየገደሉ ከዚያ ሲነሱ፣ ወደ 3 ሺህ በላይ ሆነው የተነሱት ሰዎች አንድ ሺህ ያላነሰ ሲቀራቸው ወደ ኢትዮጵያ ገቡ። (አቶ ሙሀመድ አንተነህ፣ ካሴት ቁጥር 5(ሀ) ግንቦት 6 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)

### ተረክ አስራ ዘጠኝ

ሳባን የውጭ መንግስት መጦ ተዋውቋት ከሄደ በኋላ ወደዚያው እንድትሄድ ሲደረግ ሁለት ሆነው ነው የሄዱት። አንዷ እንደባሪያ ሁና የተከተለቻትና እራሷ ሳባ ማለት ነው። እና ከዚያ በኋላ ግብጥ ላይ ተሄደች በኋላ የግብጥ መንግስት ጋራ ልክ እንዲህ በጣም ተመቅየትና ተመግባባት የተነሳ እንዲፋቀሩ ተሆኑ በኋላ ያው ያቺኛዋ ነበረ ልትፈጥም የፈለገችው ግንኙነቱን፣ ግን ሳባ ላይ ሆንና ተፈጠመ። አሁን እዚያ ሳባ ላይ አንድ ልጅ በዚያ በመገናኘታቸው ተጠነሰሰና ያው እንዳረገዘች ወደ ሀገሯ ስትመለስ ያው ያ መንግስት አያውቀውም ነበረ፤ አሁን ከዚህ ከመጣ በኋላ ተዋወቀና ምን ሆነ ሳባ ላይ ከተዋወቀ በኋላ አዙራ ልጁ ታደገና ኸደረሰ በኋላ እንድትልክለት ተደረገ። አባትህን ተዋወቀው ብላ አሁን አባቱን ሊተዋወቅ ሲመለስ አብሮት አሁንም አንድ አደናጋሪ የሆነ ሰው ኸደ። አሁን አሰርቃ ያን ፎቶግራፍ ሰጣዋለች ለልጇ የዛን የአባቱን ፎቶግራፍ ማለት ነው። እዛው የመጣችን ያችን ፎቶግራፍ እዞ እያየ ነው የኸደው። ከዚያ በኋላ ግቡና እንዲህ ሁነው የሀበሻ ሰዎች መጠዋል፤ አባቱን በሚል መተዋወቅ እንፈልጋለን እና እስቲ ግቡ በሉት አባቱን ከለየው ትክክል ነው ካለየው ግን እስቲ እናያለን ብለው ሲሉ፣ የመጀመሪያው ሲገባ ሳይለየው ይቀራል። ያ ግን ልጅዬው ተገባ በኋላ ፎቶግራፏን እያየ ተጠቀመ፤ አባቱን ለየ። ያለው ሰው ተገረመ በጣም። እዚያ በኋላ አባቱን ከተዋወቀ በኋላ ምን ሆነ፤ ፋሲል ብሎ ስም አወጣለት። ፋሲል በሉት ብሎ ስም አወጣለት ይባላል። ከዚያ በኋላ መጣና ወደዚህ ያንን እንዲያ አርጎ ታባቱ ብዙ ነገሮች ግንኙነት አለ፤ በገንዘብም በሁሉም ነገር እንትን ብሎ ነው የላከው። መጣ ወደዚህ። ኸመጣ በኋላ ፋሲል ብዙ ልጆችን ወለደ። ከወለደ በኋላ ሴቶች ያው እንግዲህ በያገሩ ሲበተኑ፣ እነዚያ ልጆች ከኛ በሦስት ገጥ ገቡ ይላል። አንዱ በጣቁሳ አርገው በጎርጎራ ገቡ ይላል ሴቶቹ። አንድኛው ደሞ በጎንደር አርጎ እንዳለ እንፍራንዝ አርጎ ገቡ ይላል። ኸኛ እንደገና በዚህ ደሞ በጎጃም እንደዚሁ በባህር ዳር አርገው ገብተው እዚህ ኸኛ ሦስቶችም ሴቶች ተዋልደው ቀርተዋል ይላል። ፋሲል ጋር ያለው ግንኙነት እንዲህ ነው። ከግብፅ የተነሱትም አሉ፤ እሄም ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን የዘር ግንድ ትውልዱ

አብሮ እንደተቀላቀለ የሚያሳይ ነው። (አቶ ሙሀመድ እንተነህ፣ ካሴት ቁጥር 5(ለ)፣ ግንቦት 6 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)

### ተረክ ሃያ

የነገደ ወይጦ ማህበረሰብ አመጣጡ ግብፅ ውስጥ ነው። በአንድ ዘመን በግብፅ ጦርነት ይነሳል። በወቅቱም አንድ ላቂ ደምበል የሚባል ጎሳ እና ነገደ ወይጦ የሚባል ጎሳ ባንድ ላይ ሁነው ወደ ኢትዮጵያ ድንበር ይመጣሉ። ጦርነቱ እስኪያልፍም ሀገሩን ወደውት ኖሩ። ጦርነቱ እንደተጠናቀቀ ወደ ሀገራቸው ተመልሰው በሰላም መኖር ሲጀምሩ ደግሞ ሀገራቸው ትራባለች። እነሱም "ወደ ኢትዮጵያ ድንበር ሄደን ጊዜውን እናሳልፍ" በማለት ሁለቱ ጎሳዎች ያባይን ወንዝ ተከትለው ጉዞ ይጀምራሉ። በጉዟቸውም ጉማሬ፣ አምባዛ፣ ቀይ አሳና አሞራ እያደኑ ይበሉ ነበር። ዋናው መግደያቸውም እንጨት ነው፤ በጣም ጀግኖች ነበሩ። አዋሳ አካባቢ ሲደርሱ ላቂ ደምበል የሚባለው ጎሳ በዚያው ይቀራል። ነገደ ወይጦ ግን ማደን ሳይሰለቸው ወንዝ ለወንዝ ጉዞውን ቀጥሎ አባይ ራስ ድረስ ከተጓዘ በኋላ በዚያው ቦታ እያደነ መኖር ጀመረ (አቶ ሰሎሞን አህመድ፣ ካሴት ቁጥር 11(ለ)፣ ግንቦት 8 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)

### ተረክ ሃያ አንድ

የሆነ ሰውዬ ከየት እንደመጡ ስጠይቃቸው፣ እኛ የመጣነው የሆነ ሰውዬ ሲነግረን እስላም ሊሰግድ ጡሲ ይዞ ሊሰግድ እያለ ውሀ ጠምቶኛል ስጠኝ አለው። እና ምሰግድበት ነው አልሰጥህም አለው። እና ያ ሰውዬ አዝኖበት ሲሄድ፣ ውሀውን ሊያፈስ ሲል አልፈስ አለ። እንዴት ውሀ አይፈስም ብሎ ሲሰብረው ሰው ሁኖ ወጣ ኸረ ወጡ ተባለና እናንተ ከቅል ውስጥ ተፈቅፍቃችሁ ሰው ሆናችሁ ብሎ አለኝ አለ። አንዳንዶቹ ደሞ ከግንድ ነው የተፈጠራችሁ ይሉናል ይሉሻል። (አቶ ሰለሞን አህመድ፣ ካሴት ቁጥር 11(ለ)፣ ግንቦት 9 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)

### ተረክ ሃያ ሁለት

እንደሚያወሩን ከሆነ ምንድነው ሚሉት የአፄ ፋሲል ልጆች ናቸው ብለው ያስባሉ። እነሱን ማለት ነው እና ንግስት ሳባና ልጅ እያሱ የአፄ ፋሲል ልጆች ናቸው ብለው ይላሉ። አሁን እነዛ ሰዎች የመከራ ዘመን ሚባል ነበር። እና በዛን ሰአት የመከራ ዘመን ሚባለው በጣም ረሀብ የሆነበት ጫካ ምናምን ሁሉ በጣም የደረቀበት ምንድነው እንዲያ ያለበት ወቅት ነበር። እና በዛን ሰአት ሚበላ ምናምን አልነበረም። ሚበላ ስላልነበረ

እነዚህ ሰዎች በጣም አዳኞች ናቸው፤ በጣም ጀግናዎች ናቸው። ከዛ በቃ እየተዋጉ ወደዚህ እየመጡ ሳለ አጋጣሚ ልጅ እያሱ ሚባለው የአፄ ፋሲል ልጅ ሚባለው እህቱ እሱ ሁነው አብረው እየተዋጉ ነው ሚመጡት በአዋጊነት ማለት ነው። ተመቶ ይወድቃል፤ ተመቶ ወድቆ እያለ ጦሩ ሲዋጋ ምን ሲል በቃ የወደቀበት ጠፋቸው። ሙቶ ይሆናል ብለው ዝም ብለው አልፈው ነው የሄዱ ጫካ ውስጥ እና ወድቆ ምናምን አገኙት እና ወድቆ ሲያገኙት። እነዚህ ሰዎች ያ ሰውዬ ብቻውን ሲወድቅ እነሱ ጥለውት እንደሄዱ በቃ ሙቷል ምናምን ብለው አላዩትም የት እንደወደቀ አላዩትም። አሁን ያ ሰው የዚህ የማህበረሰብ ተወላጅ የሆነ ሰው አደን ሲሄድ ያገኘዋል እና አቦሸማኔም ምንም ሳይበላው ያገኘዋል እና ይህ ሰውዬ አውሬ ምናምን ሳይበላ ያገኘሁት በጣም ትልቅ ሰው ቢሆን ነው ይልና ያነሳዋል። አንስቶ ካመጣው በኋላ ሰውዬው ነፍሱን አያውቅም ወደ ቤት አምጠው ህክምና ያደርጉለታል የራሳቸውን እና ስሙን አላህሰጥ ይሉታል፤ ያድኑታል። ድኖ የመጣበትን አካባቢውን ስለማያቅ በቃ እዛው ቁጭ ይላል። ወቅቱም ጥሩ ስላልነበር ከዛ የበሉትን እየበላ ሚስት ያጋቡታል። ሁለት ልጆች ይወልዳል። አሁን ሁለት ልጆች ከወለደ በኋላ እነሱ አዳኞች ናቸው፤ እሱም በጣም ተኳሽ ነው። አብሮ እያደኑ እኔ ካደጉበት አገር ብዙ ሚታደን አውሬ አለ። ጉማሬ ምናምን አለ እና ከኛ አገር እንደዚህ አይነት አውሬ አለ እንግዲህ አገር ሰላም ሁኖ ጦርነቱ አልቆ እና እነዚህ ሰዎች እሺ ይሉታል፤ ይሄዳሉ። አሁን ይሄዳሉ ሌሊት ሌሊት ጫካ ውስጥ እየዋሉ ጥይት እየተኮሱ ይገላሉ እና የአካባቢው ሰዎች ይመጣሉ ተኩስ ይሰዋወጣሉ። ልክ ይተኩሳል ይገላል እና ማነው ምናምን ሲሉ የገና ገና ስመ ገናና ብለው ይፎክሩባቸዋል፤ እና እንዲህ ብሎ የገና ገና ስመ ገናና ብሎ ፎክሮብን የሄደው ሰው ከኛ በላይ መሆን አለበት። ያን ጊዜ የዘር ጉዳይ በጣም አጥባቂ ስለነበሩ እነሱ ይተኩሳሉ፤ እነዚህ ይተኩሳሉ ከትግራይ ተከዜ አካባቢ እንስተው እየተከተሏቸው ከእነዚህኞቹ አገር ይደርሳሉ። እንደዚህ ብሎ የፎከረብን ሰው ማነው ምንምን ሲሉ ይነገሯቸዋል፤ አልዳልሞተ ሚስት አግብቶ ልጆች መውለዱን ይነግሯቸዋል። በጣም ይደሰታሉ፤ ወንድማቸውን ይዘውት ይሄዳሉ። የተወለዱት ልጆች ከዚህ ይቀራሉ። (አቶ ሰለሞን አህመድ፣ ካሴት ቁጥር 14(ለ)፣ ግንቦት 12 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)።

### ተረክ ሃያ ሦስት

የኛ ብሄረሰብ ወደ ኢትዮጵያ ከውጭ ተሰደው የገቡበት ምክንያት ወይም ሰበብ ነብዩ ሙሀመድ ለእስልምና የሃይማኖት ውጊያ (ጅሀድ ሲገጥሙ በአፍሪካ በምድረ ግብፅ በሚስጥር ከተማ ከአውሮፓዎች ጋር በተደረገው የጅሀድ ውጊያ ምክንያት በጣም ደም

ስለተፋሰስ እስላሞች አሸንፈው የግብፅ ህዝብ የእስልምና ሀይማኖት አስይዘው ከተመለሱ በኂላ፣ በግብፅ ህዝብ ላይ ረሀብና በሽታ ስለገባ፣ ከናን ከምትባል ጎጥ ተነስተው የኛ ብሄሮች ህይወትን ለማትረፍ ሲሉ ከነጭ ባር ባጠገብ ተነሰተው፣ የአባይን ተፋሰስ በመከተል የባህል ምግቦችን እንደ አሳ የመሳሰሉትን በአባይ ውሀ ውስጥ እያጠመዱና እየገደሉ በመመገብ ወንዙን ተከትለው ሱዳን ሲደርሱ፣ ከፍተኛ የሆነ ውጊያ አጋጥሟቸው ሳይመለሱ እየሞቱና እየገደሉ ለምግብ ሲሉ ሱዳንን አቋርጠው አባይን በመከተል እንሆ ጎንደርና ጎጃም ከሚገኘው ከኢትዮጵያ ጣና ሀይቅ ዙሪያ ተሰማርተው በተለምዶ እንገኛለን። (ሼህ ነጃት ሰላይሉ፣ ካሴት ቁጥር 15(ሀ) ግንቦት 15 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)፡

## ተረክ ሃያ አራት

ነቢይ ሞሳ ናቸው ፈሪኦን እያባረራቸው ፈሪኦን ፈረሱ ብቻ አርባ ክንድ ነው። ወደ ባህር ግብጥ ሲወጣ የኛ ጦር እየተከተለ የኛ ጦር እየተከተለ ነብይ ሞሳን ለመግደል እየሮጠ እኛ ወደ ኂላ ሸሽተን ቀርተን ነው እንጅ የፈርኦን ዘር አይደለንም። የነብይ ሞሳ ዘር ነን። ፈሪኦንማ እርጉሟን ጠቅጥቂ እያለ በጭቃ የሚጠቀጥቅ ነው፤ የፈሪኦን አይደለንም የሙስሊም ዘር ነን። (አቶ የሱፍ እንየው፣ ካሴት ቁጥር 18(ለ)፣ ግንቦት 28 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)

## ስለሼህ ጅብሪል

## ተረክ ሃያ አምስት

ሼህ ጅብሪል ሰጭአላህ አሳቸው በኛ ብሄረሰብ ቅዱስ ቁርአን ያስገቡት እሳቸው ናቸው። እስተዚያ ድረስ የእስልምናን ሂደት ዝም ብሎ ነበር ሚካሄደው። ታዲያ እሳቸው በፈረንጅ ዘመን አንስተው የእስልምናን እንደዚህ ነው ብለው ቅዱስ ቁርአን ቀርተው፣ ብዙ እልም ቀድተው፣ ህብረተሰቡን ባህር ዙሪያ ብቻ እሳቸው ይሬስ አላ ይባላል እንዲህ ባለው ቀን ጦም ሚጦመው እንዲህ ባለው ቀን ነው ብለው ሲልኩ ባህር በዞረው በሳቸው ድምጥ ይጦም ነበር። እንዲህ ያለው ደሞ ክብረባላችን እንደዚ እንደዚ ባለ ቀን ነው ብለው እንዴው በመላክት እዚ አገር ተቀምጠው ደምቢያ፣ ጣቁሳ፣ ፎገራ ሁሉ ዝም ብለው በዚህ ያስተዳድሩት ነበር፤ አስተዳዳሪ ነበሩ። "እነዚህ ምንድናቸው?" ሲሉ ወይጦ ይባላሉ ይሏቸዋል። አቡነም ታዲያ እስላሙም ሆነ ክርስቲያኑ አያስጠጋቸውም፣ ከሁለቱም ካልሆኑ ክርስትና መነሳት አለባቸው ይላሉ። ሆኖም ሼህ ጅብሪል ቅዱስ ቁራንን ይዘው በሃይማኖቴ እፀናለሁ እንጂ ክርስትና አልነሳም ይላሉ። አቡነም

በሃይማኖትህ ተከራክረህ ብትሸነፍስ ሲሏቸው ሼህ ጅብሪል "ከተሸነፍኩ ክርስትና እነሳለሁ ሆኖም የማልሸነፍበት ቅዱስ ቁርአን አለኝ" አሉ። በኋላም ከአቡኑ ጋር ተከራክረው ባለመሸነፋቸው አቡኑ አድንቀዋቸው አዲስ አበባ ወስደው ሸልመውና አልብሰው ሰደዋቸዋል። (ሼህ ጅብሪል ሰማኸኝ፣ ካሴት ቁጥር 3(ለ)፣ ግንቦት 03 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)

### ተረክ ሃያ ስድስት

ሸህ ጅብሪል ቀደም ሲል ሲኖሩ ዋና ቃዲ የኛ ብሄር ሸህ ጅብሪል ናቸው። በስልምና ሀይማኖት ሀይማኖታቸውን እንኳን እሳቸው ለኛ አንድ ሰው ሳይቀየር ወደ ክርስትና ሳይለወጥ በእሳቸው አሳምነው አዲስአባ ድረስ ኼደው ተከራክረው ማህምሩ ጋር ጳጳሱ ጋር ተከራክረው አጥቅተው በሀይማኖታቸው አቸናፊ ሁነው የመጡ ሼህ ናቸው። እንኳንስ በክርስቲያን ለመቀየር በሙስሊሙም አንደኛ ተጠሪ ጦማችን በውነት የመሩ ቀኗ ሳትሳሳት ያመቱ ላመት ይገኛል በቁጥር ማንም ያውቀዋል እንኳን እሳቸው እንኳን የተማረው ያልተመረው ጥፎ ተያዘ በሳቸው ቀን ጦሙ ይያዛል። ሲገደፍ በሳቸው ይገደፋል። በጣም ተባህር ዳር ሙስሊም አንደኛ ተብለው ሚኖሩ እሳቸው ናቸው በኛ ብሄር። እና ሲኖሩ ደህና ነበሩ፤ ደህና መሪ ነበሩ፤ ተትንሹ ዝቅ ብለው ተትልቁ ዝቅ ብለው ነፍሳቸውን ሳያናንቁ ትልቁ ትንሽ መስለው የሚኖሩ ሼህ ነበሩ። እንኳንስ ክርስቲያኑ ሙስሊሙም ሳያቸንፋቸው በጦማቸው ቁጥር ቀጥ ብለው በሳቸው ይመሩ ነበር። የሞቱበት ቀን ይከበራል፤ አመታታቸው በዛው መውሊድ ይሆናል፤ ይከበራል። እንደዛሬው የሞቱበት ቀን ይከበራል እንደነገ መውሊዳቸው ይወጣል። በአመት በአመት ልጆች ያወጣሉ አገሩም ገንዘብ ይሰጣል ይለግሳል እስተ ጉልበቱ እስተ ገንዘቡ የሳቸው ጥሩ ስራ ስለሆነ አልተመለሰም፤ የሳቸው ውለታ። (አባ ሰይዴ አለም፣ ካሴት ቁጥር 4(ለ)፣ ግንቦት 5 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)

### ተረክ ሃያ ሰባት

አባ ሼህ ጅብሪል ሚባሉ ሰውዬ በዚህ በነገዴ ላይ ባህር በዞረ ነበር ሚያስተዳድሩት እና በዚያ ሲያስተዳድሩ አጤ ዮሀንስ እሱ ክፉና እያለ ከአዲስ አበባ ወደ መቀሌ ሲያልፉ ሙስሊሙን ሰው ክርስትና እያስነሱ ሲያስገድዱ የኛንም ሰው አስገድደውታል። በዚህ ላይ የኛ ሰው የተማረ ሀይል የለውም ነበር እሳቸው ናቸው እና አሁን በሚጠይቃቸው ጊዜ እኛማ አንከፍርም እምነታችን እስልምና ነውና ወደ ክርስትናም አንነሳም እኛ አንደዚሄ እምነታችን እሄ ነው እስልምና በሚል ሲጠይቋቸው መጥሀፎችን እዘው

ተከራክረው አቸንፈው ወደ ክርስትና ሀይማኖት ሳይገቡ የቀሩበት ሁኔታ ነው ያለ። እሄ አንዱ ሲሆን፣ ተጨማሪ እሮመዳን ጦም ሲሆን፣ በማን ነው ይጦም የነበረው በሳቸው ነው። እዚህ ባህር ዳር ሁነው ሁሉም ቦታ እያስተላለፉ ፣ በየጎጧ የተቀመጠውን ሰው ትዛዝ እያስተላለፉ ጦም እንዲጦ ትዛዝ ይሰጡት ነበር እና በጣም ሊቅ ሰው ናቸው። እስከዚህ ድረስ የሰሩ ሰው ናቸው። ጣሊያን መንግስት ድረስ በመፋለም አገራቸውን ሲገድፉ የኖሩ ናቸው። (አቶ ሙሀመድ አንተነህ፣ ካሴት ቁጥር 13(ሀ)፣ ግንቦት 12 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)

### ተረክ ሃያ ስምንት

በእስልምና ጉዳይ ላይ ትልቅ አባት ነበሩ። አላህ አፉ ይበለው ትልቅ አባታችን በኛ ማይነሱ ነበሩ፤ ትልቅ ነበሩ እና እኒያ ሰውዬ በእስልምና ጉዳይ ላይ አዲስ አበባ ሄደው በኦርቶዶክስ ሀይማኖት ላይ ሄደው አሸንፈው ተሸልመው የመጡ አባት ነበሩ። ሼህ ጅብሪል ሰጭአላህ ይባሉ ነበር። እሳቸው አሁን ትልቁ ወደ እስልምናችን ተጠግተናል። ታሪካቸው አለ አሁን ሼህ ጅብሪል ሰጭአላህ ሚባል ታሪክ አላቸው መፅሄት ሁሉ አውጠው በትልቅ ነገር ሽልማት ሁሉ አላቸው ነው ሚባል ብሄሩን በቃ የእስልምና ጉዳይን በአንደኝነት አሸንፈው መጠዋል። (ወለላው ቢሆነኝ፣ ካሴት ቁጥር 17(ሀ)፣ ግንቦት 22 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)

### ስለአቢናዝ
### ተረክ ሃያ ዘጠኝ

ኑር አቢናዝ ተአያት ተቅማንቶቻችን ይዘውት ሲወርድ ሲዋረድ የኖረ ስለሆነ እኛም ከደረስን ያልሸና ወይፈን በአመት ወይፈን ተገዝቶ እንኽዳለን አባይ። ተዚያ ላይ ይታረዳል፤ ያው ዱአ ይደረጋል፤ ስንበላ አድረን ዱአ ስናረግ አድረን እንመጣለን። አባይ ወንዝ ነው፤ ሰው አደለም ወንዝ ለወንዝ ስለሆነ ወንዝ ያከብሩታል። (እማ ሙሉ ልብሞኝ፣ ካሴት ቁጥር 1(ለ)፣ ሚያዝያ 30 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)

### ተረክ ሰላሳ

አንድ የነሱ የማህበረሰቡ ተወላጅ የሆነ በሌሊት ይጓዛል እና ሲጓዝ እንዲጋጣሚ እነዚህ ሰይጣኖቹ ውጭ ላይ አንድ ልጅ ጥለው ይሄዳሉ እና ያን ልጅ ሲያገኝ አዞት ይመጣና ከቤት ያስቀምጠዋል። ከዛ መጡባቸው ነው ሚሉት። መጡና ልጃችን እዚ ውስጥ አለ ካላወጣችሁ ሲባል የኛን ዘመዶች በቃ የኛን ተወላጅ የሆኑትን በሌሊትም በምንም

አደንም ሲወጡ ሲያንገዙ ምን ሲል የሆነ ቦታም ሲሄዱ ማትንኳቸው ከሆነ እንልቀቅላችሁ፤ አስዛ ግን ልጁን እንገለዋለን ሚል ነገር አነጋገሯቸው ነው ሚሉ። ከዛ በኋላ የናንተ ዘር የተባለ አንገልባችሁም ግን የሆነ ነገር አድርጉልን አሏቸው ይላል። ምን ነገር ሲለው ጥቁር የዳጉሳ ቂጣ በኑግ የተቀባ ጭብጦና ያልሸና ወይፈን እንደዛ እያደረጋችሁ በአመት አንዴ ጣሉልን ለእኛ እያመጣችሁ ለወንዙ እንደዚህ ትሰባብሩ ትጥሉና እናንተ ቀምሳችሁ ትሄዱና እንደዛ ይላቸዋል። በቃ እሄን እናደርጋለን እንደዛ እናንተ በያመቱ ይህን ካደረጋችሁልን እኛ ደግሞ የናንተ ሰዎች ውሀ ቢገባ ምን ቢል አንነካውም ሚል ነገር ቃል አስገቧቸውና ልጁን ለቀቁላቸው ይላሉ። (ሰሎሞን፣ ካሴት ቁጥር 10(ለ)፣ ግንቦት 8 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)።

### ተረክ ሰላሳ አንድ

አቢናዝ ጊወን ጋር ነው። ጊወን ሚል ጅኒ አለ። ትልቅ የጅኖች ሁሉ የበላይ የሆነ እና ቀንዱ ከዚህ ጎርገራ ከጎርጎራ እዚህ የሆነ ጣና ላይ አሳፍቶ የያዘ ጊወን የሚባል እውራ ጅን አለ ይላሉ እና እሱ ጋራ እንትን ሲሉ የኛ የሆኑ ትልቅ ሰውዬ ነበሩ፤ እሱን ሚያናግሩ እኝህ ሰው ያን ጊወን ጅኒዎችን እያወጡ ሲያናግሩ ጊወንን አናግረውታል ይባላል እና ድርድር አርገዋል። በቃ ተመቀራረባቸው የተነሳ ቃል ግባልኝ አላቸው። አንተ ላትለየኝ ምጠይቅህን ሁላ ነገር ልታረግልኝ አላቸው። አሁን ሚጠይቀውን ሁላ ነገር ሲያረጉ ሲያስደስቱት ይላል። እንግዲህ ስጦታ ነገር ለአቢናዝ ይሰጣል እያልን ያለነው ማለት ነው እና ያን ስጦታ እየሰጡ ሲያስደስቱት ለሳቸውም ቃል ገባላቸው ምን ብሎ፣ ምን ቃል ልግባ አላቸው፣ ቃል ሚገቡልህማ የኔን ሰው የሆነ ላትነካብኝ የኔን ሰው የሆነ ላትነካብኝ፤ ላትበላብኝ ምን ቢሆን ምን የኔን ሰው የሆነ ላትነካብኝ አሉት። አዎ ያንተን ዘርያ ወይም ያንተን ሰው ላልነካ ቃል ገብቻለሁ ይላል እና ድርድሩ እሂ ነው እና ያ ቃል ገባ እስካሁን እንግዲህ እኒ የኛን ሰው አይወስደውም። እኒያ ሰውዬ ያገዱት ማለት ነው፤ አግደውታል እና ያገዱት እስካሁን ድረስ የኛን ሰው እኒ በቃ አደጋ ነገር አግኝቶት አያውቅም። ለምን ቢሄድም እንኳ ራሱ እንትን ይለዋል። ቁርጥ አርጎ እንትን አይለውም፤ ይተፋዋል። እሄ ምንድነው ያ ድርድር ማለት ነው። (አቶ ሙሀመድ አንተነህ፣ ካሴት ቁጥር 14(ለ)፣ ግንቦት 12 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)

### ተረክ ሰላሳ ሁለት

ባህር ጋ እርቅ አለን። ጋኔን ጋር ጋኔንን በመረብ ያዙት የኛ አያት ቅማኖች በመረብ ሲይዙት፣ እዞ ላይነካ የኛ አሳ አስጋሪ አለን ልጁን እዘው በመረብ ሲሉት የኛን ላይነካ

ልጁን ልቀቅልኝ የናንተን ብሄር አልነካም ብሎ አሁን ውሀም አይበላኝ ምንም አይልም ልጁን እዞ ባህር ገባ ይባላል። ተዚያ በኋላ ከብት ይታረዳል ያልሸና ወይፈን በክርስቲያን ጦም ሲገባ ላትነካ ላትነካ ተብሎ ተማምለዋል። (አባ ስንታዬሁ አይኑ፣ ካሴት ቁጥር 16(ሀ)፣ ግንቦት 22 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)

### ተረክ ሰላሳ ሦስት

አቢናዝን በመክዳት አንድ ጊዜ የተፈፀመ ድርጊት አለ። በ1985 ዓ.ም በውሃ ወይም በአቢናዝ ማመን የለባችሁም ተብለን በአሉን ማክበር አቆምን፤ ሆኖም በሽታ ገባና በቀን ሦስት አራት መሞት ጀመረ። በኋላ ለትልልቅ ሰዎች በህልም ስላሳየ የማህበረሰቡ አባላት በግ አርደው በሽታውን እንዲያበርድላቸው በመለማመናችን በሽታው ቆሟል። ከዚያ በኋላ በዓሉን እንደገና ማክበር መጀመራቸውን ይናገራሉ (ወለላው ቢሆነኝ፣ ካሴት ቁጥር 17(ሀ)፣ ግንቦት 22 ቀን 2003 ባህር ዳር)።

### ተረክ ሰላሳ አራት

ተጎርጎራ አንድ ቀንድ ተዚህ አንድ ቀንድ አለው አሉ። ያ ቀንዳም ሚባለው ጊወን ነው። ጊወን አሁን እሱ ቢሞት አገሩ ይጠፋል ይባላል። ወጦ ታዬው አገሩት እልም ትላለች። (አቶ የሻነው አንዳርጌ፣ ካሴት ቁጥር 17(ሀ)፣ ግንቦት 22 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)

### ተረክ ሰላሳ አምስት

አንድ አሽከር ተወንዝ ማዶ ሁኖ ውሀው ቢገባ ሊበላው የጥንቶች አባይ እኛው በኛ ብትለው አሉ መንትጎ የወሰደውን የበላውን አሻግሮ አሉ ሰፈፈፍ አድርጎ አሉ ተነነፍሱ አምጦ ገች አረገው አሉ። እኛው በኛ እኛው በኛ አባይ አቢናዝ እኛው በኛ እኛው በኛ ቢሉት አውጦ ያ አሽከር ወጥቶ አሉ እስተእግሩ ቀጥ ብሎ ቆመ አሉ ተነነፍሱ ይባላል። (እማ ሙሉ ልብሞኝ፣ ካሴት ቁጥር 18(ሀ)፣ ግንቦት 23 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)

### ስለባህር ዳር አመሰራረት

### ተረክ ሰላሳ ስድስት

አዎ ነገደ የዛን ጊዜ ያው ሰው ባልነበረበት ወቅት ያው እንደምልሽ ሲወርዱ ሲዋረዱ ሲወርዱ ሲዋረዱ እዚህ ባህር ዳር ይደርሳሉ እዚህ ላይ አማድበው ሲኖሩ፣ ያው እንግዲህ እየተመቸው አንድ እያለ ሁለት እያለ እንግዲህ እየተባዛ ሲሄድ ፈረንጅም መጥቶ /ጣሊያን/ መጥቶ ገባ በዚያን ጊዜ የኛ ሰው አለ እና ባህር ዳር እኮ ሰው የለም

ሰው ክርስቲያን እኮ እስተዚህ የለም ቁጥር ነው ክርስቲያን የነበረው። የኛ ሰው ነው በጠቅላላ የነበረ ጀግና ነበር። የኛ ሰው ባህር ለባህር በታንኳ ይቀማል፣ ሽፍታ ነበር፣ ወንበዴ ነበር። ያን እየቀማ እያስቸገረ በቃ ሲኖር ሲኖር ይኸው ሲባዛ ሲባዛ ክርስቲያኑ ሲባዛ ሲባዛ ያው በነሱ ቁጥጥር አረጓት እንጂ ሲሰራ ሲሰማራማ ባህር ዳር የቆዩ ማነው ሲባል ነገደ ወይጦ ነው። (ሼህ ጅብሪል ሰማኸኝ፣ ካሴት ቁጥር 1(ሀ)፣ ሚያዝያ 30 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)

## ተረክ ሰላሳ ሰባት

የኛ ብሄር አመጣጡ ተግብጥ ነው። ባህር ዳር ከተማ ስንኖር መስራቾች ሲመሰረት ባህር ዳር በጃንሆይ እኛ ነን መስራቾች አሁን ግን ተጥሎ በጭቆና ምንኖር እኛ ነን። (አባ ሰይዱ አለም፣ ካሴት ቁጥር 3(ለ)፣ ግንቦት 03 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)

## ተረክ ሰላሳ ስምንት

የማህበረሰቡ አባላት መጀመሪያ የሰፈሩት ሹማቦ ፊት ለፊት ነው። በወቅቱ የአሁኑ የፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ የመምህራን መኖሪያ ቤት የተሰራበት የማህበረሰቡ የቀብር ቦታ ነበር። በዚያ ቦታ ለረጅም ጊዜ ከቆዩ በኋላ ለፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅና ለውሃ ስራዎች ተብሎ እንዲነሱ ተደርጓል። ከዚያም ሲያስለቅቋቸው ጊዮርጊስ አካባቢ ሰፈሩ። በኋላም ለጊዮርጊስ ተብሎ ልቀቁ ተባሉ። በመቀጠልም ስታዲዮሙ ላይ መጥተው ቢሰፍሩም ስታዲየሙ ሲገነባ አስነሷቸው። በመቀጠልም ፋሲሎና ራስ አገዝ አካባቢ ቢሰፍሩም በሂደት ቦታው ይፈለጋል ተብለው እንዲነሱ መደረጉንና አሁን ባሉበት ቦታ እንዲሰፍሩ ቢደረጉም የባህር ዳር መስራችና ባለቤት ነገደ ወይጦ ነው። (አቶ ሙሀመድ አንተነህ፣ ካሴት ቁጥር 14(ሀ)፣ ግንቦት 12 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)

## ተረክ ሰላሳ ዘጠኝ

ባህር ዳር ሲባል የነገደ ወይጦ ነው። እሄ ሁሉ ደን ነው መቀመጫ አይደለም። ተዚች አገር ላይ ሰው የለም ነበር። ጫካ ዱር ነበር። የጅብ የአውሬ መዋያ ነበር። እንደዛሬው ልብስ አለበስንም ራቁታችነን ነበርን። ተሹሎክልከን እንኖር ነበር። ማን ማን እንዳለ እንተዋወቃለን። ሰው ትንሽ ስለሆነ የባህርዳር ተወላጁ ትልቁ ነገደ ወይጦ ነው። (አባ ስንታየሁ አይኑ፣ ካሴት ቁጥር 17(ሀ)፣ ግንቦት 22 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)

ታንኳ እና የድንጋይ ወፍጮ ለመጀመሪያ ጊዜ የሰሩት እነርሱ ስለመሆናቸው

ተረክ አርባ

የቆዩ አባቶች ከአንዱ አካባቢ ወደ ሌላው አካባቢ ለመሄድ መጓጓዣ ነገር ለምን አንሰራም? እያሉ ሲያስቡ እያለ ደንገል ተነቅሎ በባህር ላይ ሲንሳፈፍ ያዩታል፤ አንዳንዴም እነሱ ሊያድኑ ሲሄዱ ወይም ደንጊያው ላይ ሆነው ሲቆሙ ያንሳፍፋቸዋል። ከዚያም ይህን ነገር በብዛት ብናስረው ሰው ሊይዝ ይችላል የሚል ሀሳብ ይመጣባቸዋል። በሂደትም በደንገል ታንኳ የመጀመሪያ ትራንስፖርታቸውን ጀመሩ፤ ሰው ሲሞትም በታንኳ መላላክ ጀመሩ፤ አደኑንም በእግር እየዞሩና ዳር ይዘው እየቆሙ ከማደን ይልቅ በታንኳ ማደኑ የተሻለ አማራጭ ሆነላቸው። ከሌላ ቦታ ያደኑትንም አውሬ ለማጓጓዝ ተጠቀሙበት። ሰውም ሲያጓጉዙና ሰውንም ሲድሩ በእግር መሄዳቸው ቀርቶ በታንኳ አደረጉት። በታንኳ ሲጓዙ ያያቸው የአካባቢው ማህበረሰብም "እንዴ እነዚህ ሰዎች እንዴት በውሃ ላይ ይሄዳሉ?" እነዚህ ሰዎችማ በቃ መላኮች እንጂ ሰዎች አይደሉም ይሉ ነበር። (አቶ ሰለሞን አህመድ፣ ካሴት ቁጥር 10(ሀ)፣ ግንቦት 8 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)

ተረክ አርባ አንድ

ብሄረሰቡ ቀደም ሲል በባህር ዳር ዙሪያ ምንም ነገር የለም ነበረ እና ይሄንን ፊልስፎ የሰራው ነገዶ ብሄረሰብ ነው። ታንኳንን የመጀመሪያ ጊዜ ከደንገል እና ወፍጮም ሳይመጣ ከገጠር ወፍጮ ሳይመጣ ከድንጊያይ ጠርበው አስተካክለው ወፍጮ ሰርተዋል። ምንም የእንጀራ ማስቀመጫ ሳይመጣ ሞሰብ ሰርተዋል ከደንገል። ባሪያም ይሸጡ ነበር። ነገዶ በሰራው ታንኳ ሰው ያሸጋግሩ ነበረ። በምድር ሚመደር ታንኳ ነበር። (አቶ የሻነው አንዳርጌ፣ ካሴት ቁጥር 17(ሀ)፣ ግንቦት 22 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)

ተረክ አርባ ሁለት

አባቶቻችን ታንኳ ስራ የጀመሩት እሄ ብሄር ነው። መርከብ ከመምጣቱ በፊት በየጎጡ ያሉትን ህብረተሰብ ለመገናኘት ጥበቡን የሰራው ነገዶ ብሄር ነው። ያን ደንገል ፊትሎ እንዴት እሄ ደንገል ተባህር ላይ ይንሳፈፋል ብሎ ተፈላስሞ ያንን ነገር ሰውን ያህል ግዙፍ ነገር እህል ከብትም የሚያሻግር ጥበብ የሰሩት ነገዶ ብሄር ነው። ሌላው ደሞ ድንጋይ ብረት እንዳሁኑ መደሻ ሳይመጣላቸው ደንጊያውን በድንጋይ ጠንካራውን ድንጊያይ ያኛውን ነገር በማደረግ እያጋጨ ያንን ነገር እህል ፈጭተው በልተው ለማደር

ያነን ስልት ያመጡትም ነገዴ ብሄረሰብ ነው፡፡ (አቶ ወለላው ቢሆነኝ፣ ካሴት ቁጥር 17(ሀ)፣ ግንቦት 22 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)

## እርግማን

### ተረክ አርባ ሦስት

በነብይ ሙሳ ጊዜ ዘመቻ ሲኼዱ እዚያ ወንዝ ደረሱ፡፡ እንደዚህ አርጉ በክፈል እንደዚህ አርጉ ቢኟቸው አናረግም ብለው ትዛዝ አፍርሰው እዚያ ወንዝ ላይ ቀሩ፡፡ ያኛው ትዛዝ ያከበረው ያው ሙሳን ተከትሎ ኸደ ሙስሊም የተባለው ክፍል፡፡ ይሂ እነዚህ ወዲህ ሲቀሩ አትብዙ አትነሱ አዎ ትዝነታችሁ ባህር ለባህር ይሁን ብለው እረገሟቸው ይባላል፤ ትዛዛቸውን ባለማክበራቸው፡፡ (ሼህ ጅብሪል ሰማኸኝ፣ ካሴት ቁጥር 4(ለ)፣ ግንቦት 3 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)

### ተረክ አርባ አራት

አሁን ድሮ እንደሚባለው ነገር ከድሮ አያቶቻችን እርግማን አለ ይባላል፡፡ ከላይ ማለት ነው፤ እርግማኑ አትጡ አትንጡ፤ አግኙ ግን አይባረክላችሁ፤ ምትይዙት ነገር ብትንትን ይበል፤ አግኙ እለታዊ ጥቅማችሁን ብሉ ጠጡ ግን እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ፤ ተፋቀሩ፤ ተባብራችሁ ብሉ እንደማንኛውም ሁኑ ተብለን ያው እርግማን አለን፡፡ (አቶ ወለላው ቢሆነኝ፣ ካሴት ቁጥር 17(ሀ)፣ ግንቦት 22 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)

### ተረክ አርባ አምስት

በጥንቶች ተግብጥ መጡ የተባሉት ኸረ ኸደ ኸረ ተሻገረው ዋጦ ተሻገረው የተባለበት ነው፡፡ ሦስት ሁነው ተማምለው ተወጡበት በተሻገሩበት ነው ተሻግሮታል የስላም ስጋ የሚሰባ ተካራው ተመርቆ ነው ይባላል፡፡ የኛ ያረድኸው አይስባልህ ተብሎ ነው ይባላል ያረድኸው አይስባልህ ተብሎ ነው ደሀ ሁነን የቀረንም ተረግመን ነው (አባ ስንታየሁ አይኑ፣ ካሴት ቁጥር 18(ሀ)፣ ግንቦት 23 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)

### ተረክ አርባ ስድስት

አባቶቻችን ሲያጫውቱነ የኛ ሰው እርግመት እኮ ኑሮት ነው፡፡ በምን ስንላቸው የስላሙ ያረድኸው ይስባልህ የኛውን ግና ተሻግሮ የሄደውን ያረድኸው አይስባልህ ብሎት ተካራችን ሁኖ ነው ያረድነው እማይሰባ ደሀም የሆነ እያሉ ያጫውቱናል፡፡ (ሙሉ ልብሞኝ፣ ካሴት ቁጥር 18(ሀ)፣ ግንቦት 23 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)

## ተረክ አርባ ሰባት

በነብይ ሙሳ ጊዜ ነው መነሻ ተግብጥ ሲኖሩ ያው በመኖር ላይ በነብይ ሙሳ ጊዜ ይላል። በነብይ ሙሳ ጊዜ እሄው እንዳሁኑ ጦር ዘመቻ ነበር። እዛ ዘመቻ ሲሄዱ ያው ተግብጥ አገር ተነስተው ፈልሰው እንደመጡ ያው ዘመቻ ሲሄዱ፤ ተወንዝ ላይ ደረሱ ይላል። ተትልቅ ወንዝ ላይ ሲደርሱ ሁሉም ውሀ ጠምቶት ነበር፤ ውሀ ጠምቷቸው ሲዞሩ፣ የኔ ተከታይ የሆናችሁ ከፊል ከፊል ውሀ ጠጥታችሁ ተከተሉኝ ብለው አላፊው ሲያዝዙ፣ ከፊሉ ህዝብ በጣም እንደጠማቸው ብዙ ጠጡ። ያ ትዛዝን ያከበረ ሲሄድ፤ እነዚያ ከበዳቸውና እዚያ ላይ ቀሩ። ከዚያ ሲቀሩ ተማደሪያ ቦታ ላይ ሲሄዱ በሉ ጦር ቁጠሩ ሲባል፣ እነዚያ ቢቆጠሩ እነዚያ ከፊሎች የሉም ወዴት ሄዱ ሲባል፤ እነሱማ እዚያ ወንዝ ላይ እኮነው እንደዚህ ብለው የቀሩ ሲባል አይ እረገሟቸው ይባላል። አትብዙ አትነሱ አታግኙ አትጡ እኔ ያዘዝኳቸውን ትዛዝ ሳያከብሩ ነው እንደዚህ ሁነው የቀሩ ብለው የዛን ግዜ ተገንጥለው እንደቀሩ እንግዲህ ሱዳንን አድርገው እሄው ወንዝ ለወንዝ ሲኖሩ ሲወርዱ ሲዋረዱ ሲወርዱ ሲዋረዱ ሲወርዱ ሲከተሉ እዚ ደረሱ ነው እኛ ምንሰማው ባባቶቻችን። (ሼህ ጅብሪል ስማኸኝ፣ ካሴት ቁጥር 18(ለ)፣ ግንቦት 28 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)

## ተረክ አርባ ስምንት

በነብይ ሙሳ ዘመን ጦርነት ተነስቶ ሲሄዱ፣ መንገድ ላይ ነብይ ሙሳ ውሃ በከፊል አርጋችሁ ጠጡ ብለው ቢያዝዟቸው ግማሾቹ ትዛዙን ፈፀሙ፤ ግማሾቹ ግን ብዙ ጠጥተው እዛው ቀሩ። ሆዳቸው ሞልቶ ቀሩ ኑሯችሁ አትብዙ አትነሱ አትክበሩ አትደህዩ ኑሯችሁ ውሀ ለውሀ ይሁን አሏቸው። እሄ እንግዲህ እሄው ባህር ለባህር የሄደ ይሄ ነው (አባ ሰይዴ አለም፣ ካሴት ቁጥር 18(ለ)፣ ግንቦት 28 ቀን 2003፣ ባህር ዳር)

# አባሪ ሁለት

## የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር

### ሀ. የቁልፍ መረጃ አቀባዮች

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ፆታ | ዕድሜ | የትምህርት ደረጃ | መኖሪያ | ስራ | አስተያየት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ሰሎሞን አህመድ | ወ | 33 | 10ኛ ክፍል | ባህር ዳር | የመንግስት | |
| 2 | አቶ ሙሀመድ አንተነህ | ወ | 49 | 4ኛ ክፍል | ባህር ዳር | የመንግስት | የመስጊድ አስተዳዳሪ |
| 3 | ሼህ ጅብሪል ሰማኸኝ | ወ | 74 | የሀይማኖት ትምህርት | ባህር ዳር | ኢየሩሳሌም ድርጅት | የአገር ሽማግሌ |
| 4 | አባ ሰይዱ አለም | ወ | 75 | ያልተማሩ | ባህር ዳር | የቀን ስራ | የአገር ሽማግሌ |
| 5 | አባ ስንታየሁ አይኑ | ወ | 65 | ያልተማሩ | ባህር ዳር | የቀን ስራ | |
| 6 | እማ ሙሉ ልብሞኝ | ሴ | 70 | ያልተማሩ | ባህር ዳር | የግል | |
| 7 | አቶ ወለላው ቢሆነኝ | ወ | 35 | 5ኛ ክፍል | ባህር ዳር | የቀን ስራ | |
| 8 | ወ/ሮ ሰጡ የኔሁን | ሴ | 50 | ያልተማሩ | ባህር ዳር | የግል | ማንበብና መፃፍ |
| 9 | አቶ የሻነው አንዳርጌ | ወ | 25 | 8ኛ ክፍል | ባህር ዳር | የቀን ስራ | |

ለ. ቁልፍ ያልሆኑ መረጃ አቀባዮች

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ፆታ | ዕድሜ | የትምህርት ደረጃ | መኖሪያ | ስራ | አስተያየት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሼህ ቸርነት ዘሪሁን | ወ | 96 | ያልተማሩ | ባህር ዳር | - | |
| 2 | ሼህ ይመር ሙጩዬ | ወ | 63 | ያልተማሩ | ባህር ዳር | የቀን ስራ | |
| 3 | አቶ የሱፍ እንየው | ወ | 60 | ያልተማሩ | ባህር ዳር | የቀን ስራ | |
| 4 | አቶ ኡስማን መሀመድ | ወ | 38 | 5ኛ ክፍል | ባህር ዳር | የቀን ስራ | |
| 5 | ሼህ ነጃት ሰላይኑ | ወ | 69 | የሀይማኖት ትምህርት | ደልጊ | የባህል ሀኪም | ለግል ጉዳይ ወደ ባ/ዳ መጥተው እያለ |
| 6 | ወ/ሮ ምሳዬ ያሲን | ሴ | 36 | ያልተማሩ | ባህር ዳር | የግል | |
| 7 | ወ/ሮ ዘይንዬ አንተነህ | ሴ | 58 | ያልተማሩ | ባህር ዳር | የግል | |
| 8 | እማ ይጋርዱ አየነው | ሴ | 90 | ያልተማሩ | ባህር ዳር | - | |
| 9 | ወ/ሮ አንሻ ያረጋል | ሴ | 51 | ያልተማሩ | ባህር ዳር | የግል | |

ሐ. ተተኳሪ የቡድን ውይይት ተሳታፊዎች

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ፆታ | ዕድሜ | የትምህርት ደረጃ | መኖሪያ | ስራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ሙሀመድ አንተነህ | ወ | 49 | 4ኛ ክፍል | ባህር ዳር | የመንግስት |
| 2 | ሼህ ጅብሪል ሰማኸኝ | ወ | 74 | የሀይማኖት ትምህርት | ባህር ዳር | ኢየሩሳሌም ድርጅት |
| 3 | አባ ሰይዴ አለም | ወ | 75 | ያልተማሩ | ባህር ዳር | የቀን ስራ |
| 4 | እማ ሙሉ ልብሞኝ | ሴ | 70 | ያልተማሩ | ባህር ዳር | የግል |
| 5 | አቶ ወለላው ቢሆነኝ | ወ | 35 | 5ኛ ክፍል | ባህር ዳር | የቀን ስራ |
| 6 | ወ/ሮ ሰጡ የኔሁን | ሴ | 50 | ያልተማሩ | ባህር ዳር | የግል |
| 7 | አቶ የሻነው አንዳርጌ | ወ | 25 | 8ኛ ክፍል | ባህር ዳር | የቀን ስራ |
| 8 | ሼህ ይመር ሙጩዬ | ወ | 63 | ያልተማሩ | ባህር ዳር | የቀን ስራ |
| 9 | አቶ ኡስማን መሀመድ | ወ | 38 | 5ኛ ክፍል | ባህር ዳር | የቀን ስራ |
| 10 | አቶ የሱፍ እንየው | ወ | 60 | ያልተማሩ | ባህር ዳር | የቀን ስራ |

ማስታወሻ፡- በተተኳሪ የቡድን ውይይቱ የተሳተፉት ከቁልፍ መረጃ አቀባዮችና ቁልፍ ካልሆኑ የመረጃ አቀባዮች በመምረጥ ነው፡፡

# አባሪ ሦስት

## የፎቶግራፎች ዝርዝር

### ሀ. የቁልፍና ቁልፍ ያልሆኑ መረጃ አቀባዮች ፎቶግራፍ በከፊል




ከአቶ ሰሎሞን አህመድ ጋር የተደረገ ቃለመጠይቅ



ከሼህ ጅብሪል ሰማኸኝ ጋር የተደረገ ቃለመጠይቅ



ከአባ ሰይዶ አለም ጋር የተደረገ ቃለመጠይቅ



ከግራ ወደ ቀኝ ሙሉ ልብሞኝ፣ አጥኚዋ፣ ሠጡ የኔሁን እና ዘይንዬ አንተነህ



ከግራ ወደ ቀኝ ወለላው ቢሆነኝ፣ የሻነው አንዳርጌ፣ አጥኚዋ እና ስንታዬሁ አይኑ



የቡድን ውይይት ሲካሄድ



ከአቶ ኡስማን መሀመድ ጋር የተደረገ ቃለመጠይቅ




ከእማ ይጋርዱ ጋር የተደረገ ቃለመጠይቅ

## ለ. የማህበረሰቡ አባላት የሚሰሯቸውን ስራዎች የሚያሳይ ፎቶግራፍ በከፊል



ሴቶች መሶብ እየሰፉ



ወንዶች የሚወቅሩት የድንጋይ ወፍጮ

# ማረጋገጫ

እኔ ከዚህ በታች ስሜንና ፊርማዬን ያስቀመጥኩ የድህረ ምረቃ ተማሪ፣ ይህ ጥናት የራሴ ስራና በጥናቱም ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን ፅሁፎችና ምንጮች በሙሉ በትክክል የጠቀስኩ መሆኔን አረጋግጣለሁ፡፡

ስም፡- ከሁሉም በላይ

ፊርማ፡-

አድራሻ፡- አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣

የኢትዮጵያ ስነፅሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

የማስረከቢያ ጊዜ፡- መስከረም 2004 ዓ.ም.